አማርኛ

# እንደ ሁለተኛ ቋንቋ የመምህር መምሪያ

## ስምንተኛ ክፍል

በደቡብ ብሔሮች ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልላዊ መንግስት

ትምህርት ቢሮ የተዘጋጀ


አዘጋጆች

ትእግስት ዳዊት /MA/

ማርቆስ በላቸው

መኮንን ሆርዶፋ

አርታኢ

ፍቅርተ መኮንን/MA/

ጥራት ተቆጣጣሪዎች

አወቀ ጸጋዬ / MA/

እንግዳ ዘውዴ (ዶ/ር)

የማጣሪያ ንባብ

ምስራቅ ጠና (ዶ/ር)

# ማውጫ

ምእራፍ ገጽ

መግቢያ………………………………………………………………ii

ምዕራፍ አንድ ፡- የሕይወት ቅመም……..………………………………1

ምዕራፍ ሁለት፡- የሕይወት መመሪያ………………………………….10

ምዕራፍ ሶስት፡- የሰው ልጆች አቅም…………………………………..18

ምዕራፍ አራት፡- የአካቶ ትምህርት…………………………………….32

ምዕራፍ አምስት፡- የተሰደዱ ስሞች…………………………………….45

ምራፍ ስድስት፡- ወዳጅ ሲከዳ……..…………….………………………60

ምዕራፍ ሰባት፡-ኮተት……………………………………………………...71

ምዕራፍ ስምንት፡- ወራሾቹ ………………………………………..83

ምዕራፍ ዘጠኝ፡- ግጥም…………………………………………………….96

ምዕራፍ አስር፡- ሀብታሙ ሰው…………….…………………………….104

## መግቢያ

ይህ የመምህር መምሪያና ከዚህ ጋር አብሮ የሚሄደው የተማሪ መጽሐፍ ስምንተኛ ክፍል አማርኛን በሁለተኛ ቋንቋነት የሚማሩ ተማሪዎች በቋንቋው በብቃት ማዳመጥ ፣ መናገር ፣ ማንበብና መጻፍ እንዲችሉ ለማድረግ ተሻሽሎ የተዘጋጀ የሁለተኛ ቋንቋ ሥርዓተ ትምህርት አካል ነው ።

የመምህር መምሪያው በሥርዓተ ትምህርት፣ በመርሐ ትምህርቱ፣ በይዘት ፍሰቱ አካሄድ ላይ በመመስረቱ የሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎችን የመማር አቅምን እንዲመጥንና ለመምህሩ ግልጽ የአቀራረብ ዘዴዎችን አካቶ በመያዝ የተሰናዳ በመሆኑ አጠቃቀሙን ቀላል ያደርገዋል ። ትምህርቱ ጥራትን በጠበቀ መልኩ ለመዘጋጀቱ ስርዓተ ትምህርቱ የተመሰረተባቸውን ስድስቱ ዋና ዋና ምሶሶዎች፡- የመጽሐፉ ዘግጅት ሽፋንና ትክክለኛነት፣ሰነ ትምህርታዊ አቀራረብ፣ ተደራሽነት ፣ አውድና ተያያዥነት ፣ ቴክኒካዊ ዝግጅትና ወቅታዊነት በጥናት የተረጋገጡና ትኩረት እንዲሰጥባቸው ሆኖ በይዘቱ ላይ በመካተታቸው ተማሪዎቹ ያገኙትን የቋንቋ እውቀት ወደውት ከሕይወታቸው ጋር እያዛመዱ እንዲጠቀሙበት መረጃ ይሰጣል። በዚህም መሠረት በአንድ ምዕራፍ ሥርም ለተሰናዱት የሦስት ሣምንታት ትምህርቶች ግልጽ መመሪያ ያቀርባል። በተጨማሪም ተማሪዎች የሚማሩትን ትምህርት ለመከታተልና አስፈላጊ በሆነበት ጊዜ ሁሉ ተገቢውን ድጋፍና ማጠናከሪያ ለመስጠት ተከታታይ ምዘናን መተግበር የሚቻልበትን መርሕ ይዟል። በትምህርቱ ሂደት ውስጥ የሥርዓተ ፆታንና አካቶ ትምህርትን እንዴት ማረጋገጥ እንደሚገባ ድጋፍ ይሰጣል ። በመጨረሻ ላይም ለስምንተኛ ክፍሎች የተዘጋጀው አማርኛ እንደ ሁለተኛ ቋንቋ መርሃ ትምህርት ተያይዟል ። ይህ መርሃ ትምህርት በየደረጃው በእያንዳንዱ ወሰነ ትምህርት ተማሪዎች ሊያዳብሯቸው ስለሚገቡ የቋንቋ ብቃቶች ያሳያል። ከመርሃ ትምህርቱ ቀጥሎም ለመምህራን አዲስ (እንግዳ) ለሆኑ ቋንቋ ከማንበብና ከመጻፍ ትምህርት ጋር በጥቅም ላይ የዋሉቃላትንና ሐረጋትንየያዘ ሙዳየ ቃላት (ሐረጋት) ተያይዞ

ቀርቧል ። የማንበብ / የመጻፍ አላባውያን ተማሪዎች ቀልጣፋ አንባቢና ጸሐፊ ይሆኑ ዘንድ ሊያዳብሯቸው የሚገቡ የማንበብና የመጻፍ አምስት አላባውያን መኖራቸውን በመስኩ የተደረጉ ምርምሮች ያመለክታሉ።ተማሪዎቹ ራሳቸውን የቻሉ አንባቢዎችና ጸሐፊዎች እንዲሆኑ ለመርዳት መምህራን ሥርዓት ባለውና ግልጽ በሆነ መንገድ እነዚህን አላባውያን ማስተማር ይጠበቅባቸዋል ። ግልጽ በሆነ መንገድ ሲባል ፣ መምህራን አርኣያ (ሞዴል) ሆነው እያሳዩ ፣ ለተማሪዎች ክሂሎቹንና ክሂሎቹ ስለሚዳብሩባቸው መንገዶች ማስተማርማለት ነው ። ትምህርቱ ሥርዓት ባለው ሁኔታ ይሰጣል ሲባልም፣ በትምህርቱሂደት በየምዕራፉ ያለ አንድም ተፈላጊ አላባ ሳይዘለል ፣ በየደረጃው ክሂሎችን ከቀላል ወደ ከባድ ማስተማር ማለት ነው ። እነዚህም አምስት አላባውያን የሚከተሉትናቸው፤

- የንግግር ድምጾች ግንዛቤ (በተወሰኑ የድምጽ አጠራር ደረጃዎች ላይ)
- ትእምርተ ድምጻዊ ግንዛቤ(በተወሰኑ ፊደላት ቅርጾች ላይ)
- አቀላጥፎ ማንበብ
- የቃላት ዕውቀት
- አንብቦ መረዳት

ወደፊት በሂደት እንደሚታየው ሌሎች አላባውያንም በጣም ጠቃሚ ቢሆኑም እነዚህ አምስት አላባውያን ግን የተማሪዎችን የማንበብና የመጻፍ ክሂሎች ለማጐልበት ልናስተምራቸው የሚገቡ ክሂሎች ናቸው።እነዚህን በአግባቡ ማስተር፣ ተማሪዎች ራሳቸውን ችለው እንዲያነቡና እንዲጽፉ የሚያስችሏቸውን መሠረታዊ ክሂሎች ማስገንዘብ ማለት ነው። በንግግርም ሆነ በጽሑፍ በግልጽ ማስተላለፍን ይጨምራል ። አቀላጥፎ ማንበብ ሊዳብር የሚችለው በርካታ ድምጽ በማሰማት የማንበብ ልምምዶችን ከተገቢ መልሶ ምገባ ጋር በመስጠት ነው። በመሆኑም የንግግርና የጽሑፍ ቅልጥፍና የሚዳብረው ተማሪዎች በተቻለ መጠን ራሳቸውን እንዲገልጹ በርካታ ዕድሎች ሲመቻቹላቸውና ወቅታዊ መልሶ ምገባ ሲያገኙ ነው።

የቃላት ዕውቀት ፡-ቃላትን የመለየት/የመረዳትና ፍቻቸውን የመገንዘብ ችሎታ ነው ። የተገደበ የቃላት ዕውቀት ያላቸው ተማሪዎች የሚያነቡትንም ሆነ

የሚያዳምጡትን ጽሑፍ መልዕክት ለመረዳትና በደረጃቸው ስለ ጽሑፉ ያላቸውን አስተያየት በንግግርም ሆነ በጽሑፍ ለመስጠት ይቸገራሉ ። ስለሆነም የቃላት ዕውቀት በጣም አስፈላጊ ነው፤ምክንያቱም ተማሪዎች፣

- ለአቀላጥፎ ማንበብ አስተዋጽዖ ያላቸውን ቃላት ወይም ሐረጋት ከጽሑፍ

  ውስጥ ለይተው ይረዳሉ።

- ስለምን እያነበቡ ወይም እያዳመጡ እንደሆነ ይረዳሉ።

- ሀሳባቸውን ለሌላሰው በንግግርም ሆነ በጽሑፍ ይገልጻሉ።

የቃላት ዕውቀት የሚዳብረው አዳዲስ ቃላትን ከነፍቻቸው በማስተማር ተማሪዎች እነዚህን ቃላት በንግግርም ሆነ በጽሑፍ እንዲ ጠቀሙባቸው በማበረታታ ከሚያነቡት ወይም ከሚያዳምጡት ጽሑፍ ውስጥ የቃላትን ፍቺ የሚያገኙበትን ብልሃት (ስልት)በማስተማር ነው።

(አዳምጦ/አንብቦ) መረዳት ፦ አንድን ጽሑፍ ወይም ንግግር የመረዳትና የመተርጐም ችሎታ ነው ። የማዳመጥና የማንበብ የመጨረሻ ግብም ነው። ይህ ክሂል ቀጥተኛ መረዳትን ወይም በጽሑፍ ውስጥ ያለን መረጃ ማስታወስን ፈልፍሎ / አንጠርጥሮ መረዳትን ወይም በቀጥታ ያልተገለጸን መረጃ መረዳትንና የመረዳት ስልቶችን ወይም ጽሑፉን ለመረዳት ወይም ለመተርጐም አንባቢዎች የሚጠቀሙባቸውን ብልሃቶች ያጠቃልላል ። ክሂሉ በጣም አስፈላጊ ነው፤

ምክንያቱም፣

- ተማሪዎች በሁሉም ትምህርቶች በማንበብ እንዲማሩ ብቁ ያደርጋል።

- ተማሪዎች ራሳቸውን ችለው የሚያነቡና የሚያዳምጡእንዲሆኑ ያስችላል፤ ከዚህም በላይ በሕይወት ዘመናቸው ለመማርና ከለተለያዩ ምንጮች መረጃ ለማግኘት ክሂሉን ይጠቀሙበታል።

አዳምጦ/አንብቦ መረዳት የሚዳብረው በቅድመ ማዳመጥ/ ማንበብ፣በማዳመጥ/ በማንበብ ሂደትና በድኅረ ማዳመጥ/ ማንበብ ተግባራት ነው ። ተማሪዎች ስለጽሑፉ ( በቅድመዳመጥ / ማንበብና በማዳመጥ / በማንበብ ሂደትወቅት) እንዴት መገመት እንደሚችሉ መረዳታቸውን (በራሳቸው)እንዴት መቆጣጠር

እንደሚችሉና ያዳመጡትን ወይም ያነበቡትን እንዴት መገምገም እንደሚችሉ መማር አለባቸው፡፡

የትምህርቱ ምዕራፎች

በእያንዳንዱ ምዕራፍ በሁሉም ክሂሎች (ማዳመጥ፣መናገር፣ማንበብና መጻፍ) የቀረቡት የትምህርት ይዘቶች የማንበብንና የመጻፍን ችሎታዎች በሚያዳብሩበት መልክ ተደራጅተዋል ፡፡ ይህም ማለት፡-

- የምንባብ ይዘቶችና ርዕሰ ጉዳዮች ማዳመጥን፣መናገርን፣ ማንበብንና መጻፍን ለማስተማር ለምናዘጋጃቸው የትምህርትይዘቶች በመሣሪያነት ወይም በዐውድነት ያገለግላሉ፡፡
- በሁሉም ምዕራፎች የትምህርት ይዘቶች፣ አራቱ የቋንቋ ክሂሎች ተዋህደው ቀርበዋል፡፡

የተማሪ መጽሐፍና የመምህር መምሪያ በእያንዳንዱ ምዕራፍ የሦስት ሳምንት የትምህርትይዘቶች እንዲይዙ ተደርገው ተደራጅተዋል ፡፡ እያንዳንዱም ሳምንት 40፣40 ደቂቃ ርዝማኔ ያላቸው ሦስት ክፍለ ጊዜያት ስላሉት፣ የትምህርት ይዘቶችም በዚሁ መሠረት ተዋቅረው ቀርበዋል ፡፡ምንም እንኳ በትምህርት ቤቶች የትምህርት ዓመት መርሃ ግብር (ካሌንደር)ላይ መመሥረት የግድ ቢሆንም፣በመጻሕፍቱ የተካተቱትን የየምዕራፉን ትምህርት ይዘቶች ለማጠናቀቅ ከሦስት ሳምንትም በላይ ጊዜ ሊያስፈልግ ይችላል ፡፡ በዚህ ጊዜ መምህራን ይዘቶቹን ለማጠናቀቅ አማራጭ ዘዴ መፈለግ ይጠበቅባቸዋል፡፡ እያንዳንዱ ሳምንት ቀጥሎ በዝርዝር የምንጠቅሳቸው ሰባት የትምህርት አላባውያን አሉት፡፡

1.የቃላት ጥናት ፡-በምንባቦች ውስጥ የሚገኙ በቀላሉ ለማንበብ አስቸጋሪ የሆኑ(ውስብስብ፣የተውሶና ተዘውታሪ ያልሆኑ)ቃላትን አቀላጥፎ በማንበብላይ ያተኩራል ፡፡ይህም በቃላቱ ውስጥ ያሉፊደላትን፣ቅጥያዎችንና ዋና ቃላትን በመነጠል፣እንዲሁም በማጣመር በተገቢ ሁኔታ እንዲያነቡ ያግዛቸዋል፡፡

2. አንብቦ መረዳት ፡-በእያንዳንዱ ምዕራፍሥር በተለያዩ ርዕሰ ጉዳዮች ላይ ተመሥርተው የቀረቡትንሦስት ምንባቦች በማንበብና በመረዳት ላይ ያተኩራል፡፡ አቀራረባቸውም ተማሪዎችን በተለያዩ የመናገርና የመጻፍ ተግባራት በሚያሳትፍ መልኩ ነው፡፡ተግባራቱም የሚከተሉትን ሊያካትቱ ይችላሉ፡፡

- የምንባቦች ርዕሰ ጉዳዮችን ወይም የምንባብ ይዘቶችን ከተማሪዎች የቀደመ ዕውቀት ጋር የሚያያይዙ ተግባራት፣
- ከንባብበፊት ስለምንባቦቹ ይዘት ምንነት የመገመት የቅድመ ንባብ ተግባራት፣
- በምንባብ ውስጥ ያሉ ቁልፍ ቃላትን መማርወይም በነሱ ላይ የመወያየት ተግባር፣
- ምንባቦችን የማንበብ ተግባር፣
- በማንበብ ሂደት ምን ያህል እንደተረዱ ራስን የመለካት ብልሃቶችን (self-checking strategies) የመጠቀም ተግባር፣
- በምንባቡ ላይ የተመሠረቱ ልዩ ልዩ የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎችን

  የመመለስ ተግባር፣
- በምንባቡ ይዘት ላይ በክፍል ወይም በአነስተኛ ቡድን የመወያየት ተግባር፣
- ስለምንባቡ ርዕሰ ጉዳይ ወይም ይዘት የመጻፍና የመናገር ተግባር፣
- የተለያዩ ክንዋኔዎችን ለማዘጋጀትና ለመከወን ምንባቡን (ግጥም ወይም አፈታሪክ ወይም ተውኔት) እንደናሙና የመጠቀም ተግባር፣

3. የቃላት ዕውቀት፡-በሚነበቡና በሚደመጡ ምንባቦች ውስጥ የሚገኙ አዳዲስ ቃላትን በመማርና በመጠቀም ላይ ያተኩራል።

በዚህ ሥር የሚዘጋጁ ተግባራት የሚከተሉትን ሊያካትቱይችላሉ፤

- የቃላቱን ንበት፣ፍቺ፣ክፍሎችና የተለያዩ አጠቃቀሞችን መማር፣
- ተመሣሣይ አወቃቀርና ፍቺ ያላቸውን ሌሎች ቃላትን መማር፣
- በሚነበቡና በሚደመጡ ምንባቦች ውስጥ ያሉ አዳዲስ ቃላትን መለየትና መረዳት፣
- ቃላቱን በመናገርና በመጻፍ ተግባራት ውስጥ መጠቀም፣

4. መጻፍ፡- በምዕራፉ የምንባብ ይዘቶች፣ ርዕሰ ጉዳዮችና የጽሑፍ ዓይነቶች ላይ በመመሥረት በርካታ ጽሑፎችን በመጻፍ ላይ ያተኩራል። መጻፍ፣

7. ድርሰት መጻፍንና የአጻጻፍ ሥርዓቶችን ያጠቃልላል።

ድርሰት የመጻፍ ተግባራት የሚከተሉትን ሊያካትቱ ይችላሉ፤

- ቅድመ መጻፍ፡- አንድን ጽሑፍ ወይም ጽሑፎች ካነበቡ በኋላ በምንባቡ ጭብጥ ወይም ርዕሰ ጉዳይ ላይ መወያየት፣የቢጋርሠንጠረዥ ማዘጋጀት፣ በዚህም ላይ ተመሥርቶ ቁልፍ ሀሳቦችን ማደራጀት፣
- ማርቀቅ፡-ሀሳብን አሰባስቦ መግቢያ፣አካል፣ መደምደሚያ ያለው ጽሑፍ መጻፍ፣
- መከለስ፡- የጽሑፉንሀሳብ አደረጃጀትና ሙሉነት፣ እንዲሁም ግልጽነት፣ ሳቢነትና ግጥምጥምነት ለማሳካት የመሸጋገሪያ ቃላትና ሐረጋት በአግባቡ በጥቅም ላይመዋላቸውን መልሶ በማንበብ ማረጋገጥ፣
- ማረም፡-የአጻጻፍ ሥርዓቶች(ፍደላ፣ሥርዓተ ነጥብ፣ሰዋስዋዊ ትክክለኛነት፣ የቃላት አጠቃቀም፣ የአንቀጽ አከፋፈል) በአግባቡ መከበራቸውን ለማረጋገጥ የአርትኦት ሥራ መሥራት፤

5. አቀላጥፎ ማንበብ፡-አንድን ምንባብ ለክፍል ደረጃውበተወሰነው የንባብ ፍጥነት፣ በትክክልና ለጽሑፉ ተስማሚ በሆነ አገላለጽ(አነባበብ)ድምጽ እያሰሙ በማንበብ ችሎታ ላይ ያተኩራል።

6. ቃላዊ ክሂሎች፣ማዳመጥና መናገር፡- በምዕራፉ የምንባብ ይዘትና ርዕሰ ጉዳይ ላይ ተመሥርቶ የቀረበን ምንባብ አዳምጦ በመረዳት፣ በምንባቡ መሠረት በቃልና በጽሑፍ ተግባራት ላይ በመሳተፍ ሀሳብን አደራጅቶ በንግግር በማቅረብ ላይ ያተኩራል። በዚህ ሥር ከሚካተቱት ተግባራት መካከል የሚከተሉት ይጠቀሳሉ፤

የማዳመጥ ምንባቦችን ርዕሰ ጉዳዮች ወይም የምንባብ ይዘቶችን ከተማሪዎች የቀደመ ዕውቀት ጋር የሚያያይዙ ተግባራት፣

- ከማዳመጥ በፊት ስለምንባቦቹ ይዘት ምንነት የመገመት የቅድመ ማዳመጥ ተግባራት፣
- በማዳመጥ ምንባብ ውስጥያሉ ቁልፍ ቃላትን መማር ወይም በነሱ ላይ የመወያየት ተግባር፣

7. ምንባቦችን የማዳመጥ ተግባር፣

- በማዳመጥ ምንባቦች ላይ የተመሠረቱ ልዩ ልዩ የአዳምጦ መረዳትና አመራማሪ ጥያቄዎችን የመመለስ ተግባር፣
- በማዳመጥ ምንባቡ ይዘት ላይ በክፍል ወይም በአነስተኛ በቡድን የመወያየት ተግባር፣
- ስለማዳመጥ ምንባቦች ይዘት/ስለርዕሰ ጉዳዮች ለሚደረጉ ውይይቶችና ክርክሮች የመዘጋጀትና በንቃት የመሳተፍ ተግባር፣
- በተለያዩ ጉዳዮች ላይ ተዘጋጅቶ ንግግር የማቅረብ ተግባር፣

ሰዋስው፡-በመርሃ ትምህርቱላይ ተመሥርቶ ለየደረጃው በተዘጋጀው የትምህርት ወሰንና ተከታታይነት ወይም ቅደም ተከተል (Scope and Sequence)መሠረት (ለምሳሌ፣ነጠላና ብዙ ቁጥር፣ የአሁንና የኃላፊ ጊዜያት ግሶች፣ ቅጽሎችና ተውሳከ ግሶች፣ ውስብስብ ዓረፍተ ነገሮች ወዘተ.) የተለያዩ ሰዋስዋዊ መዋቅሮችን በመማርና በትክክል በመጠቀም ላይ ያተኩራል።

በአጠቃላይ ከላይ የዘረዘርናቸው የትምህርት አላባውያን ማዕከልያደረጉት በምዕራፍ የምንባብ ይዘቶችና በርዕሰ ጉዳዮች ላይ ተመሥርተው በተዘጋጁት የማንብብና የማዳመጥ ምንባቦች ላይ ነው። ተግባራቱም ተማሪዎቹ ከ5ኛ ክፍል ጀምረው 8ኛ ክፍል እስከሚደርሱ ድረስ የውስብስብነት ደረጃቸውን ጠብቀው፣ አምስቱን የማንበብና የመጻፍ አላባውያንና አራቱን የቋንቋ ክሂሎች( ማዳመጥ፣ መናገር፣ ማንበብና መጻፍ )መማርንና ማስተማርን የሚያጠናክሩ ናቸው። የማስተማር መርሖች ልሥራ፣ እንሥራ፣ ሥሩ በዚህ ሥርዓተ ትምህርት ውስጥ ዋነኛው የማስተማሪያ ዘዴ በተለምዶ“ልሥራ፣እንሥራ፣ሥሩ” ወይም በትክክለኛ አጠራሩ “ሚናን ለተማሪዎች ቀስ በቀስ የማስተላለፍ የሞዴል” (gradual release model) ተብሎ ይታወቃል።ተማሪዎች በመጀመሪያ ጥያቄዎች ወይም ተግባራት በመምህር ሲሠሩ ያያሉ፤ቀጥሎም የክፍሉ ተማሪዎች ከመምህራቸው ጋር አብረው በጋራ ይሠራሉ፤ በመጨረሻም ተማሪዎችራሳቸውን ችለው በግላቸው እንዲሠሩ የሚደረግበት የማስተማር ዘዴ ነው። ምንምእንኳ ሁሉም ደረጃዎች በሁሉም ቦታ ተሟልተው የማይገኙበት ሁኔታ ቢኖርም፣ሞዴሉ ለአብዛኛዎቹ የትምህርት ክንውኖች ወይም ተግባራት በዚህ መምሪያ ውስጥ በግልጽ ተብራርቶ ቀርቧል።ዘዴው ተማሪዎች አዳዲስ ክንውኖችን ወይም ተግባራትን ለመሥራትና በራስ የመተማመን አቅማቸውን ለመገንባት ይረዳቸዋል።

በመተባበር መማር (Cooperative Learning)

በመተባበር መማር ተማሪዎች በብጤ ወይም በቡድን ተደራጅተው ከክፍል ጓደኞቻቸው ጋር በመደበኛነት ወይም ለአጭር ጊዜ ተወስነው የሚሰጧቸውን ተግባራት የመሥራት ዕድልን ይፈጥራል:: ከሌሎች ጓደኞቻቸው ጋር አዳዲስ መረጃዎችን የመለዋወጥ ዕድል ስለሚፈጥርየክፍል ውስጥ መማርን ያጠናክራል በመተባበር መማር ብዙ ተማሪዎች ባሉበት ክፍል ውስጥ በንቃት እንዲሳተፉ ዕድል ይፈጥራል::

መልሶምገባ መስጠት፡- አንዱ የማስተማር ዋነኛ አካል ተማሪዎች በተናገሯቸው፣ ባነበቧቸው፣ ባቀረቧቸው ወይም በጻፏቸው ነገሮች ላይ መልሶ ምገባ መስጠት ነው:: አንዳንድ ጊዜ መልሶ ምገባ ሳይሰጡ በሚሠሩ መለማመጃዎች ላይ ብቻ ማተኮር ጠቃሚ ሊመስል ይችላል:: ነገር ግን ተማሪዎች የተሰጣቸውን ተግባር እንዴት መሥራት እንዳለባቸውና የሠሩትም ትክክል መሆኑን ወይም አለመሆኑን ለመረዳት ስለሚጠቅማቸው መልሶ ምገባ መስጠት አስፈላጊ ነው:: መልሶምገባ የመስጠቱ ሂደት ውጤታማ ይሆን ዘንድ መምህራን የሚከተሉትን ማድረግ ይጠበቅባቸዋል::

- ተማሪዎች የሰጡት ምላሽ ትክክል ወይም ስህተት መሆኑን መንገር፤
- ተማሪዎቹ የሰጡት መልስ ለምን ትክክል ወይም ስህተት ሊሆን እንደቻለ ማብራራት፤
- በትክክል የተሠራውን ለተማሪዎች መንገር፤
- የሚጠበቅባቸውን ተግባር በትክክል እንዴት መሥራት እንዳለባቸው ወይም ምን ዓይነት ብልሃት መጠቀም እንዳለባቸው መንገር፤

ተማሪዎች የሚነገራቸውን ትክክለኛ መልስ ወይም አቀራረብ ከመስማት ይልቅ በራሳቸው ትክክለኛ መልስ ላይ እንዲደርሱ ወቅታዊ መልሶምገባ በመስጠት ይታገዛሉ:: ለምሳሌ አንድ ተማሪ አንድ አንቀጽ ሲያነብ/ስታነብ አንድ ቃል ሲጠራ / ስትጠራ ቢሳሳት/ ብትሳሳት በሚከተለው አኳኋን ሊነገረው/ራት ይገባል፤ አንቀጹን ጥሩ አንብበሃል / ሻል፤ግን የሁለተኛው ዓረፍተ ነገር ሁለተኛ ቃል “ቤቶች” ሳይሆን “ቤታችን” ነው፤ስለ “-ኣችን” መማራችንን ታሳታውሳለህ / ሻለሽ? ወይም አንድ ተማሪ ከምንባቡ ውስጥ ያሉትን ዋና ዋና ነጥቦች እንዲ ዘረዝር / እንድትዘረዝር ለቀረበለት /ላት ጥያቄ የሰጠውን /ሺውን ምላሽ በማጤን፣ ከምንባቡ ዋና ዋና ነጥቦች ውስጥ ሁለቱን በትክክል መልሰሃል/ሻል፤ ጥሩ ነው፤ሶስተኛው ነጥብ ምን እንደሆነ ልትነግረኝ/ሪኝ ትችላለህ/ቺያለሽ? ወዘተ.

የማስተማሪያ መርጃ፡- በብዙ አካባቢዎች የሚገኙ የመማሪያ ክፍሎች ለትምህርት አገልግሎት የሚውሉ ቁሳቁሶችየተሟሉላቸው ናቸው ማለት አዳጋች ነው፡፡ ስለዚህ በቀላሉ ባካባቢው ሊዘጋጁ የሚችሉ የትምህርትመርጃ መሣሪያዎችን ለማዘጋጀት ወይም ለመፍጠር ጥረት ማድረግ ተገቢ ነው፡፡ ስለሆነም ለዚህ ሥርዓተ ትምህርት ጠቃሚ ከሆኑት ቀላል የማስተማሪያ መርጃ መሣሪያዎች መካከል የሚከተሉት ይገኙባቸዋል፡፡

**ፍላሽ ካርዶች፡-** እነዚህ ተማሪዎች የሚማሯቸውን ቃላት የሚያሳዩ ተመጥነው የተዘጋጁ ካርዶች ናቸው፡፡ እነዚህ ካርዶች ቃላቱን ሰሌዳ ላይ እያጠፉ በመጻፍ ጊዜ ከማጥፋት በፍጥነት ካንዱ ፊደል ወይም ቃል ወደ ሌላው በቀላሉ እየለዋወጡ ለመጠቀም አመቺ ናቸው፡፡ ከርቀት ለማንበብም ቀላል ስለሆኑ፣ ለሁሉም የክፍል ተማሪዎች፣ ለአነስተኛ ቡድኖች ወይም ለግለሰቦችም በቀላሉ ለመጠቀም ያመቻሉ፡፡ በቀላሉም ቀደም ብሎ ለማዘጋጀትና እንደአስፈላጊነቱ ደጋግሞ ለመጠቀም አመቺ ናቸው፡፡

**ባዶ የመውጫ ካርዶች፡-** እነዚህ እንደ ፍላሽ ካርዶች ተቆራርጠው የተዘጋጁ ስለሆኑ፣ ተማሪዎች እየጻፉባቸው ለመምህራቸው የሚያሳዩባቸው ናቸው፡፡ ለምሳሌ የማንበብ ሂደት ተግባራት እነዚህን ክርታሶች በመጠቀም ቢመለሱ መልካም ነው፡፡

**ባለኪስ ሠንጠረዥ** (Pocket-Chart)፡ የፖስተር መጠን ያለውና ከሸራ ወይም ከጨርቅ የተዘጋጀ ባለኪስ ሠንጠረዥ ሲሆን፣ ተማሪዎች እንዲያዩዋቸው ፍላሽ ካርዶችን ሊይዝ የሚችል ነው፡፡ ይህ ሠንጠረዥ በአንድ ጊዜ በርካታ ፍላሽ ካርዶችን ለማቅረብና ለማሳየት እንዲሁም በማዘዋወር ለመጠቀም ያመቻል ዓረፍተ ነገሮችንም በአዳዲስ ቃላት ለመመሥረትና ስለ ቃላቱ ፍቺ ለመነጋገር ያስችላል፡፡

**ሥዕላዊ መግለጫ (ፖስተር)፡-** ለጭብጥና ለርዕሰ ጉዳይ የሚዘጋጁ ሥዕላዊ መግለጫዎች፣ (ለምሳሌ፣ በሥራቸው አርኣያ ስለሆኑ ሴቶችና በማኅበረሰቡ ውስጥ ስላላቸው ሚና፣ ስላካባቢ ጥበቃ ዕቅድ፣ በተውኔት ውስጥ ቀርቦ ስለነበረ ወይም ወደፊት ስለሚቀርብ ክፍል ወዘተ...የሚዘጋጁ) የተማሪዎችን ፍላጎትና ተሳትፎ ይጨምራሉ፡፡ መምህራን እነዚህን ሥዕላዊ መግለጫዎች እርስ በርስ ሊለዋወጡ ይችላሉ፤ተማሪዎችም አዳዲስ ሥዕላዊ መግለጫዎችን በመፍጠር ረገድ ሊሳተፉ ይችላሉ፡፡

**ተከታታይ ምዘናና ድጋፍ/ማበልፀግ**

ተከታታይ ምዘና ማለት ተማሪዎች እንዴት እየሠሩ እንደሆነና ትምህርቱን መረዳታቸውንና ክሂሎችን በሚፈለገው መጠን ማወቃቸውን ለመረዳት በተከታታይ መረጃ የሚሰበሰብበት ሂደት ነው፡፡ ይህ ምዘና ስለማስተማር ሂደት ወይምሊከለሱ ስለሚገባቸው ወይም በድጋሚ ማስተማር ስለሚያስፈልጋቸው ትምህርቶች ውሳኔ ለመስጠት ስለሚያስችል ለመምህራን በጣም ጠቃሚ ነው፡፡ በተጨማሪም መምህራን ተማሪዎች በየመንፈቀ ዓመቱውስጥ ከሚጠበቁባቸው ብቃቶች አንጻር የሚያሳዩትን ዕድገት በሚመለከት ያላቸውን ምልከታና የተከታታተይ ምዘና ወጤቶችን ለመመዝገብ ሊጠቀሙበትይችላሉ፡፡ መምህራን ተማሪዎች እንዴትእየሠሩ እንደሆነ በተከታታይ ምዘና ለመረዳት፣ በመማር ሂደት ውስጥ ችግር ያለባቸውን ተማሪዎች ለመርዳትና ጥሩ ለሚሠሩትም ዕውቀታቸውን ለማበልፀግ የሚከተሉት ሁለት ዓይነት አጠቃላይ የምዘና ስልቶች (ቴክኒኮች) ጠቃሚዎች ናቸው፡፡ ኢመደበኛ ተከታታይ ምዘና ይህ ምዘና የመማር- ማስተማሩን ሂደት የተማሪዎችን መማር እግር በእግር እየተከታተሉ፣ጉድለት ካለ ለመሙላትና ድጋፍ ለማድረግ ታልሞ የሚተገበር ምዘና ነው፡፡በዚህ ረገድ ከሚጠቀሱት ዘዴዎች ቀጥሎ የቀረቡትን መጠቀም ይቻላል፡፡

**ምልከታ**፡- መምህራን እንሥራ፣በተለይ ደግሞ ሥሩ በሚለው የትምህርቱ ሂደት ወቅት በክፍል ውስጥ መዘዋወርና ተማሪዎቻቸውን መከታተል አለባቸው፡፡ በዚህ ጊዜ መምህራን ተማሪዎቹ በግላቸው፣ ከብጤያቸው ወይም ከአነስተኛ ቡድን ጋር እንዴት እየሠሩ እንደሆነና የትኞቹ የተለየና ተጨማሪ ድጋፍ እንደሚሹ፣ የትኞቹ ደግሞ የተሻለ ለመሥራት ከአቅማቸው ጋር የሚሄድና የሚገዳደራቸው ተግባር እንደሚፈልጉ ለመለየት ይችላሉ፡፡ መደበኛ ተከታታይ ምዘና የዚህምዘና ዋና ዓላማ ተማሪዎች ትምህርቱን መረዳታቸውንና ክሂሎችን በሚፈለገው መጠን ማወቃቸውን በየደረጃውና በየምዕራፉ መጨረሻ መለካት ነው፡፡ የሚከተሉትን ዘዴዎች ለአብነት መጠቀም ይቻላል፡፡

o **የክፍል ልምምዶችና የቤት ሥራዎች፡-** መምህራን፣ ትምህርቱን መረዳታቸውንና ክሂሎች በተገቢው ሁኔታ መዳበራቸውን ለመረዳት ተማሪዎችበጽሑፍ የመለሷቸውን የክፍልና የቤት ሥራዎች ሰብስበው ይገመግማሉ፡፡

o **ሙከራዎችና ፈተናዎች፡-** ተማሪዎች አንድን የትምህርትይዘት ወይም ክሂል መረዳታቸውን ለማወቅ ሙከራዎችና ፈተናዎች ሊሰጡ ይችላሉ፡፡ ከ5ኛ-8ኛ ባሉ የክፍል ደረጃዎች የሚሰጡት ሥራዎችና ፈተናዎች በአብዛኛው

በጽሑፍ የሚመለሱ ናቸው፡፡ ይሁንና ፈተናዎች በቃል የሚመለሱም ሊሆኑ (ለምሳሌ፣ የአቀላጥፎ ማንበብ ችሎታቸውን ለመለካት ከአንድ ጽሑፍ የተወሰነውን ድምጽ በማሰማት እንዲያነቡ ወይም የአንብ የአዳምጦ መረዳት ችሎታቸውን ለማወቅ ጥያቄዎችን በቃላቸው እንዲመልሱ ወይም ስለአንድ ጉዳይ በቃላቸው እንዲያቀርቡ ማድረግ) ይችላሉ፡፡

ድጋፍ ምን ማለትነው? ድጋፍ ማለት መምህራንተማሪዎችን ለማበረታታት የሚፈጸሙት ተግባር ወይም የሚሰጡት የማበረታቻ ቃል ነው፡፡

አንዱ የተከታታይ ምዘና አስፈላጊነት ተጨማሪ ድጋፍ የሚፈልጉ ተማሪዎችን ለመለየት ነው፡፡ ይህም በእንሥራና በተለይ በልሥራ ልምድ ወቅት መምህራን ትምህርቱን ለመገምገምና ችግር ላለባቸው ተማሪዎች በወቅቱ ድጋፍ ለማድረግ ዕድል ይሰጣቸዋል፡፡ አንዳንድ ጊዜም ከክፍል ውጪ ድጋፍ የሚሹ የተወሰኑ ተማሪዎች ሊያጋጥሙ ይችላሉ፡፡

○ **ለክፍሉ፣ ለአነስተኛ** ቡድን ወይም ተማሪዎች (በግል) ድጋፍ የማድረጊያው አንዱ መንገድ ወደ ልሥራ ወይም ወደ እንሥራ ተመልሶ ለተማሩት ይዘት ወይም ክሂል ተጨማሪ ምሳሌዎች እየሰጡ ማለማመድ ነው፡፡

ማበልፀግ ምን ማለት ነው? አንዳንድ ተማሪዎች ፅንሰ ሃሳብን ቶሎ ሊረዱ ስለሚችሉ ትኩረታቸውን ለመያዝ ጠንከር ያለና የሚገዳደራቸው ነገር ይሻሉ፡፡ ማበልፀግ የሚያመለክተው ለእንደነዚህ ያሉ ተማሪዎች ተጨማሪ መረጃ በማቅረብ ያላቸውን ዕውቀት የሚያሰፉ የሚያዳብርተግባር መስጠትን ነው፡፡ በዚህም ተማሪዎች በአዲስ መልክ የቀረቡላቸውን መረጃዎች እንዲጠቀሙባቸው በማድረግ ዕውቀታቸውን እንዲያሰፉ መገዳደር ይቻላል፡፡

በተከታታይ ምዘና ሂደት የቀረበው ተግባር ወይም ክሂል የሚቀላቸውንና ከበድ ያለ ተግባር ወይም ክሂል የሚያስፈልጋቸውን ተማሪዎች ለይቶ ማወቅ ይቻላል፡፡ የነዚህን ተማሪዎች ዕውቀት ማበልፀግ ካልተቻለ በትምህርቱ ሊሰላቹና ፍላጎት ሊያጡ ወይም የተለየ ባሕሪ ሊያሳዩና ችግር ሊፈጥሩ ይችላሉ፡፡ ለእነዚህ ተማሪዎች የማበልፀጊያ ተግባር የሚሰጠው በሁለት ዓይነት መንገድ ነው፤ አንደኛው፣ ተጨማሪ የማንበብ ተግባር ( ከመጽሐፋቸው ሌላ ተጨማሪ ንባብ እንዲያቡ) እና ሁለተኛው ተጨማሪ የመጻፍ ተግባር ( በመጽሐፋቸው ውስጥ የሌለ ሌላ የመጻፍ ሥራ) መስጠት ናቸው፡፡ምናልባትበተጨማሪ የሚነበቡ ጽሑፎች ወይም መጻሕፍት ከሌሉ፣መምህራን በተማሪዎች መማሪያ መጽሐፍ ውስጥያሉትን የሚመሥሉ የመጻፍ ተግባራት ሊፈጥሩ ይችላሉ ፡፡ ከዚያም ላቅ ያለ ችሎታ ያላቸው ተማሪዎች አንዳቸው የአንዳቸውን ሥራ እንዲያነቡና

መልሶ ምገባ እንዲሰጡ ፣አርትኦት እንዲያደርጉ ፣ በሥራዎቻቸው ላይ እንዲወያዩ ወዘተ. ማድረግ ይቻላል ። ይህም ተጨማሪ ንባብ ሆኖ ሊያገለግል ይችላል። አንዳንድ ጊዜ መምህራን ተማሪዎችን በማቧደን ችግር ያለባቸው ተማሪዎች ከጎበዞቹ የሚማሩበትንም መንገድ ሊያመቻቹ ይችላሉ።

# ምዕራፍ አንድ

# የሕይወት ቅመም

## ለተግባሩ የተመደበው ጊዜ፡- 9 ክ/ጊዜ

1. ርዕስ የሕይወት ቅመም

2. የሚጠበቁ ውጤቶች

ተማሪዎች ይህን ትምህርት ከተማሩ በኋላ፡-

- ምንባብ አዳምጠው አስተያየት ይሰጣሉ፡፡
- በቀረበላችው ርዕሰ ጉዳይ ላይ ውይይት ያደርጋሉ ፡፡
- የቃላትን ፍቺ በቃል ይገልጻሉ፡፡
- በምንባቡ መሠረት ጥያቄዎችን ይመልሳሉ፡፡
- የምንባቡን ዋና ሃሳብ ይገልጻሉ፡፡
- የዐ.ነሮችን ክፍሎችን ለይተው ዐ.ነገር ይጽፋሉ፡፡
- አንቀጽ ይጽፋሉ፡፡

3.ዝርዝር ይዘቶች

ሀ ማዳመጥና መናገር

ትምህርት አንድ ፡- ማዳመጥ

- ለማዳመጥ ዝግጁ የሚያደርጓቸውን  የቅድመ ማዳመጥ ጥያቄዎችን ይሞክራሉ፡፡
- የሚቀርብላቸውን ምንባብ በትኩረት ያዳምጣሉ፡፡
- ባዳመጡት ምንባብ መሠረት ልዩልዩ ጥያቄዎችን ይመልሳሉ፡፡

ትምህርት ሁለት፡- የንግግር ክሂል ማዳበር

- ታክስን የተመለከቱ መረጃዎችን መሰረት በማድረግ ይናገራሉ፡፡

ለ.ማንበብ

ትምህርት ሶስት፡-

- ለማንበብ ዝግጁ የሚያደርጓቸውን ቅድመ ንባብ ጥያቄዎችን በቃል ይመልሳሉ፡፡
- የቀረበላቸውን ምንባብ አስተካክለው ያነባሉ፡፡
- ባነበቡት ምንባብ መሠረት የድህረ ንባብ ጥያቄዎችን ይመልሳሉ፡፡

ሐ. መጻፍ

ትምህርት አራት፡- የዐ.ነገር ክፍሎች

- የአረፍተነገር ክፍሎችን ይለያሉ፡፡
- አረፍተነገር ያዋቅራሉ፡፡
- አንቀጽ ይጽፋሉ፡፡

የምዕራፉ ማበልጸጊያ ጥያቄዎች፡-

- የዓ.ነገር ክፍሎችን ይገልጻሉ፡፡
- የራሳቸውን ዓ.ነገር ይመሰርታሉ፡፡
- አንቀጽ ይጽፋሉ፡፡

4. የትምህርቱ አቀራረብ

ትምህርት አንድ፤ማዳመጥና መናገር

መምህር/ት

ከዚህ በታች አበይት በሆኑ ጉዳዮች ዙሪያ ብቻ አጠቃለይ የአቀራረብ ብልሃቶች ቀርበዋል፡፡ ቢመለከቷቸው ትምህርቱን ከሞላ ጎደል በተሳካ ሁኔታ ለመምራት ያስችሎዎታል፡፡ ነገር ግን እነዚህ ብልሀቶች ብቸኛ ናቸው ብለው ራስዎን በእነሱ ብቻ እንዳያጥሩ፡፡ እንደ ሁኔታዎች ጋባዥነት ወይም እስገዳጅነት እየተመለከቱ፣ የራስዎን ፈጠራዎችና የተሻሉ ዘዴዎችን በመጠቀም ተማሪዎቹን ሊያግዟቸው ይችላሉ፡፡

የምዕራፉ የመጀመሪያ ትምህርት በማዳመጥ ዙሪያ የሚያጠነጥን ነው፡፡ ለክሂሉ አተገባበር እንዲረዳ ተብሎ ከዚህ በታች አንድ ምንባብ ቀርቧል፡፡ ምንባቡም የተማሪዎችን የማዳመጥ ክሂል ግብ አድርጎ የተመረጠ ነው፡፡ መጀመሪያ ተማሪዎች ማዳመጥ እንዲጀምሩ በተለያየ መንገድ ያነቃቋቸው፡፡ በመቀጠል

ለማዳመጥ ዝግጁ የሚያደርጓቸውን የቅድመ ማዳመጥ ጥያቄዎችን በመጠየቅ የቀደመ እውቀታቸውን ተጠቅመው የቁልፍ ቃላትን ፍች እንዲናገሩ ያድርጓቸው፡፡ ከዚያም ምንባቡን ያንብቡላቸው፡፡ ምናልባትም ምንባቡን ቶሎ ላይረዱት ስለሚችሉ ደግመው ያንብቡላቸው፡፡ ከዚያም ምንባቡን አስመልክቶ በተማሪዎች መጽሃፍ ላይ በቀረቡት ጥያቄዎች ዙሪያ ያወያዩዋቸው፡፡

የማዳመጡ ምንባብ ርእስ፡ ታክስ/ግብር

ለ.ትምህርት ሁለት፡- መናገር

ትምህርት ሁለት የንግግር ክሂል የሚዳብርበት ይዘት ነው፡፡ አስቀድሞ ሲነበብ ያዳመጡትን (ስለ ታክስ የሚያወራውን ምንባብ) መነሻ በማድረግ በታክስ ጉዳይ ላይ ያስተዋሉትን በቡድን ሆነው እንዲወያዩበት ያድርጓቸው ፡፡ በዚህ ወቅት በየቡድኑ ያሉ ተማሪዎች ሁሉም በጥንድ እንዲሳተፉ ክትትል በማድረግ ያበረታቷቸው ፡፡ ለውይይት የተሰጣቸው ጊዜ ሲያልቅ እያንዳንዱ ቡድን በተወካዩ አማካይነት በክፍል ጓደኞቻቸው ፊት እንዳመቺነቱ እየተነሱ የንግግር ክሂል ልምምድ እንዲያደርጉ ይርዷቸው፡፡

ሐ.ትምህርት ሶስት፡- ማንበብ

መምህር/ት

ተማሪዎች በመማሪያ መጽሀፋቸው ላይ የሕይወት ቅመም በሚል ርእስ ስለ ጥቁር አዝሙድ የተጻፈውን ምንባብ ከማንበባቸው በፊት ቅድመ ንባብ ጥያቄዎችን እንዲመልሱ ያበረታቷቸው ፡፡ በመቀጠል ምንባቡን በግል እንዲያነቡ ያድርጓቸው፡፡ ከዚያም ማንበባቸውን ገታ አድርገው በማንበብ ሂደት የሚመለሱ ጥያቄዎችን አንዲመልሱ ይጠይቋቸው፡፡ለቀረቡላቸው ጥያቄዎች ምላሽ ከሰጡ በኋላ ቀሪውን የንባብ ክፍል እንዲያጠናቅቁ ይንገሯቸው፡፡ማንበቡን ሲያጠናቅቁ ከምንባብ የወጡ ጥያቄዎችን ያሰሯቸው፡፡

መ. መጻፍ

ትምህርት አራት ፡- ዐ.ነገር ፣ አንቀጽ መመሥረት

ተማሪዎች በመማሪያ መጽሐፋቸው ላይ ስለ ዐ.ነገር ክፍሎች፣ የሰዋሰው ሕግን መሠረት በማድረግ ዐ.ነገር ስለመመስረት የተሰጡ ምሳሌዎች አሉ፡፡ እነዚህን ምሳሌዎች ለተማሪዎች በመግለጽ ማብራሪያ ይስጧቸው፡፡ በመቀጠል ሌሎች ምሳሌዎችን ከእርሶ ጋር አብረው እንዲሰሩ ያበረታቷቸው፡፡ በመጨረሻም በተሰጣቸው ምሳሌ መሠረት ያቀረቡላቸውን ጥያቄዎች አንዲሰሩ ያድርጓቸው፡፡

ትምህርት አምስት፡- አንቀጽ መጻፍ

- አስቀድመው ስለ አንቀጽ ምንነት የቀረበላቸውን ማስታወሻ አንብበው የአንቀጽን ምንነት ያስረዷቸው፡፡
- የተሰጣቸውን ማስታወሻ ተጠቅመው የግል ገጠመኞቻቸውን አስመልክተው አንቀጽ እንዲጽፉ ያድርጓቸውና የጻፉትን በጥንድ ሆነው እንዲያነቡና አስተያየት እንዲሰጣጡ በማድረግ እየዞሩ ይመልከቷቸው፡፡

1. መርጃ መሳሪያዎች ፡-
   የቅመም ዓይነቶችን በአካል ማሳየት ወይም እነሱን የሚያሳይ ምስል መጠቀም (ጥቁር አዝሙድ፣ ነጭ አዝሙድ፣ ኮረሪማ፣አብሽ ወዘተ...)
2. ግምገማ ፡-
   - የማዳመጥ ጥያቄዎችን በትክክል መመለሳቸውን ማረጋገጥ
   - በተሠጣቸው ርእስ ላይ በንቃት መወያየታቸውንና ተሳትፎ ማድረጋቸውን መከታተልና ግብረ መልስ መስጠት፡፡
   - ስላነበቡት ነገር የተረዱትን በመጠየቅ መረዳታቸውን ማረጋገጥ
   - የአረፍተ ነገር ክፍሎችን ለይተው መረዳታቸውን ዐአረፍተነገርና አንቀጽ መመስረታቸውን ማረጋገጥ፡፡
3. በናሙናነት ለተመረጡ ጥያቄዎች መልስ፡-
   ለተማሪዎች ለሚቀርቡ ጥያቄዎች መልስ የምእራፉ ትምህርቶች ተጠቃለው ሲያልቁ በመጨረሻው ላይ በቅደም ተከተል ይገለጻሉ፡፡

አንደኛ ሣምንት፤ አንደኛ ቀን

ትምህርት አንድ፡- ማዳመጥ

መምህር የሚከተለውን አጭር ምንባብ ለተማሪዎችዎ ድምጽዎን ከፍ በማድረግ ያንብቡላቸው፡፡

ግብር(ታክስ)

ለሰው ልጅ በልቶ ማደር፣መጠለያ ማግኘት፣በአልባሳት አካልን መሸፈን ለመኖር የሚያስፈልጉ መሠረታዊ ጉዳዮች በመሆናቸው እነዚህን ለሟሟላት መስራትና ገቢ ማግኘት አስፈላጊ ነው ፡፡ ገቢ ማግኘት የተዘረዘሩትን መሠረታዊ ፍላጎቶች ለሟሟላት የሚያስችል ቢሆንም እንኳን ሁሉም በተሟላ ሁኔታ በአንድ አካባቢ የማይገኙ በመሆናቸው ሰው ባላበት አካባቢ ለማድረስና ለማቅረብ የመንገድና የማመላለሻ ተሽርካሪዎች መሰረተ ልማት መኖር ግድ ይሆናል፡፡

ሰው የእለት ምግቡን፣መጠለያውንና ልብሱን በግሉ ሰርቶ በሚያገኘው ገቢ ለመሸፈን አይከብደው ይሆናል፡፡እንደ መንገድ፣መብራት፣የመጓጓዣ ተሽርካሪዎች፣ትምህርት ቤቶችንና የመሳሰሉትን መሠረተ ልማቶች ለሟሟላት ግን የሚቻለው አይሆንም፡፡ ስለዚህ ይህን ሀላፊነት የሚወጣ ትልቅ አቅም ያለው ተቋም ያስፈልጋል፡፡ ይህ ተቋም በሕዝብ ፈቃድ የተመሠረተ በሕዝብ አገልግሎት ሰጪ ተቋማት የተደራጀ መንግስት የሚባል አካል ነው፡፡

ለሕዝብ አገልግሎት የሚሰጡ ተቋማት የሚባሉት፡ የመብራት፣የውሃ፣የስልክ፣የንግድ፣የመጓጓዣ፣የገንዘብ ወዘተ. አቅርቦቶች የሚያመቻቹና የሚመሩ አካላት ናቸው፡፡ መንግስት እነዚህን አቅርቦቶች ለሟሟላት ወጪ የሚያደርገው ገንዘብ ያስፈልገዋል፡፡

**ተማሪዎች፤ መንግስት ወጪ የሚያደርገውን ገንዘብ ከየት የሚሰበሰብ ይመስላችኋል?**

መንግስት ለደመወዝ፣ለመሰረተ ልማቶች ግንባታ የሚያውለውን ገቢ የሚሰበስበው ከሚያስተዳድረው ሕዝብ ነው ፡፡ ሰርቶ ያገኘ ፣ ነግዶ ያተረፈ ከሚያገኘው አገልገሎት ቀንሶ በሚከፍለው አነስተኛ መዋጮ ግብር ይከፍላል፡፡ ከውጭ ሸቀጥ አስመጪዎች ከሚያቀርቡትና ከሚያገኙት ገቢ ፣ የኢንዱስትሪው ባለ ሐብት ከሚያመርተው ምርት ሽያጭ ገቢ ውስጥ ቀንሶ ወጪ በማድረግ ቀረጥ ይከፍላል ፡፡ከነዚህ አካላት ተቀንሶ የሚከፈለው የዜግነት መዋጮ በእንግሊዝኛው አጠራር ታክስ በአማርኛው አጠራር ቀረጥ ወይም ግብር በመባል የሚታወቀው ነው፡፡

ከበራሪ ጽሑፍ ላይ ተቀንጭቦ የተወሰደ

አንደኛ ሣምንት፤ ሁለተኛ ቀን

ትምህርት ሁለት ፡- መናገር

በታክስ ጉዳይ ላይ ለተማሪዎች ተጨማሪ አጭር ማብራሪያ ይስጡና በሚከተሉት ጥያቄዎች ላይ ያወያዩ፡፡

1. ቀደም ሲል ስለ ታክስ የነበራችሁ ግንዘቤ ምን እንደነበር አስታውሳችሁ ለጓደኞቻችሁ ንገሩ፡፡
2. ምንበቡን ካደመጣችሁ በኋላ ያገኛችሁት አዲስ ነገር ካለ በቡድናችሁ ተወያዩ፡፡

- በሶስተኛው ቀን ትምህርት ላይ የተጠቀሱትን ጥያቄዎች ጠይቀው ማስታወሻ ይዘው በመምጣት ለቡድን አባሎቻቸው እንዲያስረዱ የቤት ስራ ይስጧቸው፡፡

አንደኛ ሣምንት ፡- ሶስተኛ ቀን

1. በግብርና በታክስ ጉዳይ ላይ ወላጆቻቸውን ጠይቀው የሚነግሯቸውን ሃሳብ ለቡድን ጓደኞቻቸው እንዲያስረዱ ይጠይቋቸው ፡፡
2. በአካባቢያችሁ የምታገኟቸውን ነጋዴዎቸና የመንግስት ሠራተኞች ስለሚከፍሉት ግብር የሚሰማቸውን ስሜት ጠይቃችሁ ለክፍል ጓደኞቻችሁ አጋሩ፡፡

ሁለተኛ ሣምንት፡ አንደኛ ቀን

ትምህርት ሶስት ፡ አንብቦ መረዳት

ቅድመ ንባብ ጥያቄዎች

**ተግባር አንድ፡** በመማሪያ መጽሐፋቸው ላይ የቀረበላችሁን ምንባብ ከማንበባቸው በፊት በቅድመ ንባብ ጥያቄዎች ላይ ያወያዩዋቸው ፡፡

ሀ.በገቢያ ውስጥ ካያችኋቸው ማጣፈጫዎች መካከል ምን ምን ታስታውሳላችሁ?

ለ.በሽታን ለማዳን የሚያገለግሉ በአካባቢያችሁ የተለመዱ መድሐኒቶች ታውቃላችሁ?

ተግባር ሁለት፡- የግል ንባብ

የግል ንባቡን ሲያስነብቡ የማንበቢያ ጊዜ ይወስኑ፡፡ እያነበቡ መሆናቸውን ለመከታተል የንባቡን አማካይ ይወስኑና እንዲያቆሙ ይንገሯቸው፡፡ የቆሙበትን ቦታ እንዲነገርዎት ያድርጉ፡፡ ጥቂት ተማሪዎችን ከጠየቁ በኋላ ንባቡን እንዲቀጥሉ ያድርጓቸው፡፡

ድህረ ንባብ ጥያቄዎች

ተግባር ሶስት ፡-ከምንባቡ ቀጥሎ ለቀረቡት ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት መልስ እንደሰጡ ያድርጓቸው፡፡

ሁለተኛ ሣምንት ፤ ሁለተኛ ቀን

ትምህርት አራት ፡-መጻፍ

የስራ ክፍፍል የሚለውን አጭር ምንባብ ተማሪዎቹ ካነበቡ በኋላ ከምንባቡ ባገኙት ሃሳብ ላይ በመነሳት የቀረቡትን ምሳሌዎች አይተው በጽሁፍ መልስ እንዲሰጡ ያድርጓቸው፡፡

ሁለተኛ ሳምንት ፤ ሶስተኛ ቀን
አንቀጽ መጻፍ

ተግባር አንድ፡-
በመጀመሪያ ስለ አንቀጽ የተጻፈውን መመሪያ እንዲያነቡ ያድርጉ፡፡ በመቀጠል ያልገባቸውን ሃሳብ እንዲጠይቁ ያበረታቱ ፡፡የተማሪዎችዎን ሃሳብ ካዳመጡ በኋላ ስለአንቀጽ ሀይለ ቃልና መዘርዝር አረፍተነገር ያስረዷቸው፡፡ ያልገባቸው ተማሪዎች ካሉ ደግመው በማስረዳት መደገፍ እንደሚያስፈልግ አይዘንጉ፡፡በመጨረሻም የሚፈልጉትን ርእስ ያስመርጧቸው፤ ዋና አረፍተ ነገር ይመስርቱ፤ እሱን የሚያብራሩ ተጨማሪ አረፍተ ነገር እንዲሰሩ ይንገሯቸው፡፡

ሶስተኛ ሳምንት፤ አንደኛ ቀን
ተግባር ሁለት
የእኔና የቤተሰቤ ገጠመኝ የሚለውን አንቀጽ አንብበው በምንባቡ መሰረት ለቀረቡ ጥያቄዎች በጽሁፍ መልስ እንዲሰጡ ያድርጉ፡፡ በመልሱ ላይ የጋራ ውይይት ከተደረገ በኋላ የራሳቸውን ገጠመኝ በተመለከተ አንድ አንቀጽ ጽፈው እንዲመጡ ይንገሯቸው፡፡

ሶስተኛ ሳምንት ፤ ሁለተኛ ቀን

- በየቡደናችዉ ለሚገኙ ጓደኞቻቸው ገጠመኞቻችውን ተራ በመውሰድ እንዲያነቡላቸው በማድረግ በየቡድኑ እየዞሩ ይከተታሉ፡፡

ሶስተኛ ሳምንት፡ ሶስተኛ ቀን

- ተማሪዎች የጻፉትን አንቀጽ በክፍሉ ተማሪዎች ፊት ተራ በመስጠት እንዲያነቡ ያድርጓቸውና ገንቢ ግብረ መልስ ይስጧቸው፡፡

በናሙናነት የቀረቡ ጥያቄዎች መልስ
ሁለተኛ ሳምንት፡ አንደኛ ቀን
ማዳመጥ
ተግባር ሶስት

የቅድመ ማዳመጥ መልሶች

1. ጥቁር አዝሙድ
2. ነቀርሳ
3. ለፕሮስቴት፣ ለጡት፣ለደም፣ለጉበት፣ለኩላሊትና ለሳንባ ካንሰር
4. ይስማማሉ
5. የራሳቸውን መልስ ሊሰጡ ይችላሉ፡፡

የቤት ስራ ሰርተው እንዲመጡ የቃላት አውዳዊ ፍች እንዲፈልጉ ያድርጉ

| | | |
|---|---|---|
| 1. ፍቱን = አዳኝ<br>2. ንጥረ ቅመም= ዘይት<br>3. በለገሳቸው =በሰጣችው<br>4. ይፋ = ግልጽ | 5.<br>6.<br>7. | ደዌ = ሕመም<br>**እያማተሩ =እያዩ**<br>**ፋይዳ = ጥቅም** |

ሁለተኛ ሳምንት ፤ሁለተኛ ቀን

መጻፍ

1. አህመድ ከብት ያግዳል፡፡
   ባለቤት አህመድ
   ተሳቢ ከብት
   ማሰሪያ አንቀጽ ያግዳል
2. ኩሊቴ ውሃ ቀዳች፡፡
   ባለቤት ኩሊቴ
   ተሳቢ ውሃ
   ማሰሪያ አንቀጽ ቀዳች
3. ፋዮ ጎመን ቀቀለች፡፡
   ባለቤት ፋዮ
   ተሳቢ ጎመን
   ማሰሪያ አንቀጽ ቀቀለች
   የሚከተሉትን አያያዞች

ሶስተኛ ሳምንት፡ አንደኛ ቀን
የቤተሰብ ገጠመኝ

1. ታሪኩ ገመዶ

2. የገጠር መንደር
3. የአርሶ አደር
4. ገጠመኝ
5. የራሱን ገጠመኝ
6. አይጥ፣ድመትና ውሻ

ከዚህ ልምምድ በኋላ የራሳቸውን ገጠመኝ ጽፈው እንዲመጡ የቤት ስራ ይስጧቸው ።

ሶስተኛ ሳምንት፡ ሁለተኛ ቀን

- ጽፈው ያመጡትን ገጠመኝ በጥንድ ሆነው እንዲያነቡ ያድርጉ

ሶስተኛ ሳምንት፡ ሶስተኛ ቀን

- አንዳንድ ከየቡድኑ በክፍል ፊት አንዲያነቡ እድል ይስጡ።

ምዕራፍ ሁለት

የህይወት መመሪያ

ለምእራፉ የተመደበው 9 ክ/ጊዜ

1. ርዕስ  የህይወት መመሪያ
2. የሚጠበቁ ውጤቶች

ተማሪዎች ከዚህ ትምህርት በኂላ  ፡-

- ጠንክሮ መስራት የሚለውን ምንባብ አዳምጠው አስተያየት ይሰጣሉ፡፡
- በመማሪያ መጽሀፋቸው የቀረበውን የሚና ጨዋታ መሰረት በማድረግ ምልልስ ያደርጋሉ፡፡
- ከቀረበላቸው ጽሁፍ ውስጥ የህይወት መመሪያዎችን አንብበው በጽሁፍ ይዘረዝራሉ፡፡
- የዕለት ውሎ ዘገባ ይጽፋሉ፡፡
- ለቃላት ተመሳሳይ ፍች ይጽፋሉ፡፡
- ለቃላት ተቃራኒ ፍች ይጽፋሉ፡፡

**3. ዝርዝር ይዘቶች**

**ሀ.ትምህርት አንድ - ማዳመጥ**

- ቅድመ ማዳመጥ ጥያቄዎችን ይሞክራሉ፡፡
- የሚነበብላችውን ምንባብ በትኩረት ያዳምጣሉ፡፤
- ጽሁፍን ካዳመጡ በኂላ የተለያዩ ጥያቄዎችን ይመልሳሉ፡፡

**ለ.ትምህርት ሁለት፡ መናገር**

በመማሪ መጽሀፋቸው ላይ የቀረበላቸውን የሚና ጨዋታ አንብበው ቀጣዩን ታሪክ በመፍጠር የእናት፣ የአባት፣ የእህትና የወንድም ሚና ይጫወታሉ፡፡

**ሐ. ትምህርት ሶስት፡ አንብቦ መረዳት**

ተግባር አንድ

ቅድመ ንባብ ጥያቄዎች

- የቁልፍ ቃላትን ፍቺ ይገምታሉ፡፡
- የቀረበላቸውን ምንባብ ከማንበባቸው በፊት ርዕሱን በማየት ስለ ምን እንደሚገልጽ ይገምታሉ፡፡

ተግባር ሁለት፡- የግል ንባብ

- የህይወት መመሪያ በሚል ርእስ የቀረበላቸውን ምንባብ በግል ያነባሉ፡፡
- የንባብ ጊዜ ጥያቄዎችን ይመልሳሉ፡፡
- ቀድመው ባነበቡት ምንባብ መሰረት የህይወት መመሪያዎችን ለይተው ይዘረዝራሉ፡፡
- ከምንባቡ ለወጡ ሌሎች ጥያቄዎች ምላሽ ይሰጣሉ፡፡

**መ. ትምህርት አራት፡ መጻፍ**

በቀበረበላቸው ርዕሰ ጉዳይ ላይ በቡድን ተወያይተው በጽሁፍ ምላሽ ይሰጣሉ፡፡

**ሠ. ትምህርት አምስት፡ የቃላትን ተቃራኒ ፍች መጻፍ**

ተግባር አንድ፡- ጽሁፍ ማንበብ

ተግባር-ሁለት፡- ከጽሁፉ ውስጥ ለወጡ ቃላት ተቃራኒ ፍች ከዚያው ጽሁፍ ውስጥ በመፈለግ ይጽፋሉ፡፡

**ረ.ትምህርት ስድስት የቃላትን ተመሳሳይ ፍች መጻፍ**

ተግባር አንድ፡-በመማሪያ መጽሀፋቸው ላይ የሚገኘውን ጽሁፍ ያነባሉ፡፡

ተግባር ሁለት፡- ከጽሁፉ ውስጥ የተወሰዱትን ቃላት ተመሳሳይ ፍች ካላቸው ቃላት ጋር ያዛምዳሉ፡፡

**ሰ. ትምህርት ሰባት፡- ዘገባ መፃፍ**

ተግባር አንድ

ስለ ዘገባ የተፃፈውን አጭር ማብራሪያ እና የእለት ውሎ ዘገባ ናሙና ያነባሉ፡፡

ተግባር ሁለት፡- የእለት ውሏቸውን የተመለከተ ዘገባ በግል ይጽፍሉ፡፡

**ትምህርት ስምንት ፡- ዘገባ**

ባለው ክፍለ ጊዜ ጽፈው እንዲመጡ የታዘዙትን ዘገባ በየተራ ለመምህራቸው በማሳየት አስተያየት ይቀበላሉ፡፡

**ትምህርት ዘጠኝ፡ ዘገባ**

በቡድን በመቀመጥ ስለጻፉት ዘገባ እየተወያዩ የአጻጻፍ ልምድ ይለዋወጣሉ

የምዕራፉ ማበልፀጊያ ጥያቄዎች

ሀ. የዘገባን ምንነት አስረዱ፡፡

ለ. በትጋት መስራትና በብልሃት መስራት መካከል ያለውን ልዩነት አብራሩ፡፡

ሐ. የህይወት መመሪያዎችን ዘርዝሩ

**4. የትምህርቱ አቀራረብ**

**አንደኛ ሳምንት፡ አንደኛ ቀን**

**ሀ/ትምህርት አንድ ማዳመጥ**

የምዕራፉ የመጀሪያ ትምህርት የሚጀምረው በማዳመጥ ነው፡፡ ቀጥሎ ለክሂሉ አተገባበር የሚረዳ ምንባብ ቀርቧል፡፡ ምንባቡን ለተማሪዎች ከማንበብዎ በፊት የቀደመ እውቀታቸውን ተጠቅመው የቁልፍ ቃላትን ፍቺ እንዲገምቱ ያበረታቷቸው፡፡ በመቀጠል ተማሪዎች በትኩረት እንዲያዳምጡ በማሳሰብ ጽምጾን ከፍ አድርገው “ጠንክሮ መስራት” የተሰኘውን ምንባብ ያንብቡላቸው፡፡ ከዚያም ምንባቡን አስመልክቶ በተማሪዎች መጽሐፍ ላይ በቀረቡት ጥያቄዎች ላይ በቡድን ያወያዩ፡፡

ጠንክሮ መስራት

በማንኛውም የሥራ መስክ ወይም ተግባር ላይ የተሰማራ ሰው ውጤታማ ሊሆን የሚችለው ጠንክሮ በመስራት ነው፡፡ጠንክሮ መስራት ማለት ቀኑን ሙሉ ያለ እረፍት ዝም ብሎ መልፋት ሳይሆን የተለያየ ብልሃትና ጥበብ በመጠቀም ጊዜን ሳያባክኑ ስራ ላይ ማዋል ማለት ነው፡፡ አንድ ሰው በህይወቱ ስኬታማ ለመሆን በቅድሚያ ዝንባሌውን ማወቅና ምን መስራት እንደሚፈልግ መገንዘብ አለበት፡፡

**ጥያቄ፡ በጽሁፉ ውስጥ እስካሁን ምን ምን ነጥቦች ተነስተዋል?**

ተማሪው በትምህርቱ፣ ገበሬው በግብርናው፣ነጋዴው በንግዱ፣ የመንግስት ሰራተኛውም በስራው ውጤታማ ለመሆን አላማ ይዞ ከተነሳ ምንም ያህል ጊዜ ቢፈጅ ከግብ መድረሱ አይቀርም፡፡ ዋናው ነገር የውስጥ ዝንባሌን ማወቅ፣ ብስራ ይሳካልኛል ብሎ ማመን እቅድ ማቀድና ተግቶ መስራት ነው፡፡ወደ ተግባር ከተገባ በኂላም ብዙ ርቀት ሳይጓዙ ቆም በማለት ይህ አካሄድ ስኬታማ ያደርገኛል? ምን ያህል ውጤት አገኘሁበት? ብሎ መገምገምና የተለያየ ጥበብ እንደ አስፈላጊነቱ በመጠቀም የአሰራር ለውጥ ማድረግ መልካም ነው፡፡

**አንደኛ ሳምንት፡ ሁለተኛ ቀን**

**ለ/ ትምህርት ሁለት፡ መናገር**

**ሚና ጨዋታ**

እንደ ትምህርት ሁለት የተማሪዎችን የንግግር ክህሎት ለማዳበር የተዘጋጀ ነው፡፡ በዚህ ክፍለ ጊዜ ተማሪዎች በመማሪያ መጽሀፋቸው ላይ የቀረበውን የሚና ጨዋታ በትኩረት እንዲያነቡና የታሪኩን ቀጣይ ክፍል ከራሳቸው በማፍለቅ የአባት፣ እናት፣ የእህትና የወንድም ሚና ለመጫወት ሴትና ወንድ ተማሪዎችን በማቀላቀል አምስት አባላትን የያዘ ቡድን ይመስርቱ፡፡ ተማሪዎች ድምጻቸውን ዝቅ አድርገው ሳይረባበሹ ታሪክ ፈጥረው እንዲለማመዱ

ያበረታቷቸው፡፡ በዚህ ሂደት በተማሪዎቹ መካከል በመዘዋወር ሌላ ስራ የሚሰሩ ተማሪዎች ካሉ መቆጣጠር ይኖርቦታል፡፡ ለአስር ደቂቃ ያህል ከተለማመዱ በኋላ በየተራ እየተነሱ በክፍል ጓደኞቻቸው ፊት ምልልስ እንዲያደርጉ ያግዟቸው፡፡ በዚህ ጊዜ ለአይናፋር ተማሪዎች የበለጠ ሞራል በመስጠት እንዳይፈሩ ማደፋፈር ያስፈልጋል፡፡

**ሐ/ አንደኛ ሳምንት፡ ሶስተኛ ቀን**

**ትምህርት ሶስት፤ አንብቦ መረዳት**

ተማሪዎች በመማሪያ መጽሀፋቸው ላይ ‹የህይወት መመሪያ› በሚል ርዕስ የቀረበላችሁን ምንባብ ከማንበባቸው የምንባቡን ርዕስ በመመልከት ስለምን እንደሚያወራ እንዲገምቱ የሚጠይቀውን ቅድመ  ንባብ ጥያቄ ምላሽ ለመስጠት እንዲሞክሩ ያበረታቷቸው፡፡ ከዚያም ምንባቡን በጥሞና እንዲያነቡ ይዘዟቸው፡፡ ሁሉም ተማሪዎች አንቀጽ ሁለት ድረስ አንብበው ሊጨርሱ የሚችሉበትን ደቂቃ በመገመት ማንበባቸውን እንዲያቆሙና የንባብ ጊዜ ጥያቄዎችን በቃል እንዲመልሱ ያደርጓቸው፡፡ በመቀጠል ጽሁፉን አንብበው ሲጨርሱ የድህረ ንባብ ጥያቄዎችን በጽሁፍ እንዲመልሱ ያበረታቷቸው፡፡ በመጨረሻም ሁሉም ተማሪዎች እጅ በማንሳት በቃል እንዲመልሱ በማድረግ የእለቱን ትምህርት ያጠናቅቁ፡፡

**መ/ ሁለተኛ ሳምንት፡ አንደኛ ቀን**

**ትምህርት አራት ፡ መፃፍ**

ተማሪዎችን ለአምስት በመሆን በቡድን እንዲቀመጡና ለቡድናቸው አወያይና ጸሀፊ እንዲመርጡ ያድርጓቸው፡፡ በመቀጠል “ባለፈው ክፍለ ጊዜ ባነበባችሁት ጽሁፍ ውስጥ ያሉት መመሪያዎች ተግባራዊ ለማድረግ ከባድ ናቸው? ለምን?” በሚል ለቀረቡት ጥያቄዎች በቡድን ተወያይተው በጸሃፊያቸው አማካይነት ምላሻቸውን በጽሁፍ እንዲገልጹ ያድጓዋቸው፡፡

## ሠ. ሁለተኛ ሳምንት፡ ሁለተኛ ቀን

### ትምህርት አምስት፡ ለቃላት ተቃራኒ ፍች መጻፍ

በቅድሚያ ተማሪዎች በቡድን እንዲቀመጡ ይዘዟቸው፡፡ በመቀጠል ከዚህ ቀደም ካነበቡት ምንባብ ለወጡ ቃለት በቡድን እየተወያዩ ተቃራኒ ፍቺ እንዲጽፉ ያድርጓቸው፡፡ ከዚያም፡- ሰርተው መጨረሳቸውን በማረጋገጥና ያንዱን ቡድን ስራ ለሌላው በመስጠት በቡድን እየተወያዩ እርማት እንዲሰጣጡ ይዘዟቸው፡፡ በመጨረሻም በደብተራቸው ለየቡድኑ እንዲመልሱ በማድረግና እርስዎ ትክክለኛውን ምላሽ በመስጠት እርማቱ ትክክል መሆኑን እንዲፈትሹ ያግዟቸው፡፡

## ረ. ሁለተኛ ሳምንት፡ ሶስተኛ ቀን

### ትምህርት ስድስት፡ ቃላትን ከተመሳሳይ ፍቺያቸው ጋር ማዛመድ

ተማሪዎች የቀረበላቸውን የአዛምድ ጥያቄ በደብተራቸው ላይ እንዲጽፉና መልሱን በግል እንዲሰሩ ትዕዛዝ በመስጠት ያበረታቷቸው፡፡ ሰርተው ሲጨርሱ ደብተራቸውን ያርሙላቸው፡፡ በእርማት ጊዜ ተማሪዎችን ለማበረታታት ባገኙት ውጤት መሰረት እጅግ በጣም ጥሩ፣ በጣም ጥሩ፣ ጥሩ ነው በማለት ያበረታቷቸው፡፡

## ሰ. ሶስተኛ ሳምንት፡ አንደኛ ቀን

### ትምህርት ሰባት፡ ዘገባ መጻፍ

በቅድሚያ ተማሪዎች ስለ ዘገባ የቀረበላቸውን አጭር ማስታወሻና የእለት ውሎ ዘገባን የሚያሳይ ናሙና ከመማሪያ መፃህፋቸው ላይ በግል እንዲያነቡ ያድርጓቸው፡፡ በመቀጠል ሲያነቡ ግልጽ ያልሆነላቸው ሀሳብ ካለ እንዲጠይቁ በመጋበዝ ማብራሪያ ይስጧቸው፡፡ ከዚያም የእለት ውሏቸውን የሚገልጽ ዘገባ

በየግላቸው እንዲጽፉ ያድርጓቸው። በዚህ ሂደት በክፍል ውስጥ በመዘዋወር ተማሪዎች ሌላ ስራ እንዳይሰሩ የቆጣጠሯቸው።

**ሸ. ሶስተኛ ሳምንት፡ ሁለተኛ ቀን**

**ትምህርት ስምንት፡ ዘገባ**

በቀደመው ክፍለ ጊዜ የጻፉትን የዕለት ውሎ ዘገባ በየተራ እየተነሱ እንዲያነቡ ያድርጓቸው። ተማሪዎቹ ሲያነቡ ለእያንዳንዳቸው አስተያየት ይስጧቸው።

**ቀ. ሶሰተኛ ሳምንት፡ ሶስተኛ ቀን**

**ትምህርት ዘጠኝ፡ ዘገባ**

ባለፈው ክፍለ ጊዜ ተማሪዎቹ ዘገባቸውን በየተራ ሲያነቡ ሰምተው አስተያየት በሰጡት መሰረት ጥሩ ዘገባ የጻፉትን ተማሪዎችን ከሌሎች ጋር በመቀላቀል አምስት አባላትን የያዘ ቡድን መስርተው ያስቀምጧቸው። በመቀጠል ስለጻፉት ዘገባ እየተነጋገሩ የአጻጻፍ ልምዱ እንዲለዋወጥ ያድርጉ እርስዎም እየተዘዋወሩ የልምድ ልውውጣቸውን ይከታተሉ።

4/ **<u>የመረጃ መሳሪያዎች</u>**

- በወረቀት ላይ ተጽፈው ለናሙናነት የቀረቡ የሚና ጨዋታዎች
- በተለያዩ አጋጣሚዎች የተደረጉና በወረቀት ላይ የተፃፉ ዘገባዎች

**5/ ግምገማ**

- ጠንክሮ መስራት የሚለውን ጽንሰ ሀሳብ አዳምጠው መረዳታቸውን ማረጋገጥ፣
- ሰዎች በተሰማሩበት የሥራ መስክ ውጤታማ ለመሆን ምን ማድረግ እንደሚገባቸው አዳምጠው መገንዘባቸውን መገምገም፣
- በሚና ጫዋታ ምልልስ ማድረግ መቻላቸውን መፈተሽ፣
- የህይወት መመሪያዎችን መዘርዘር መቻላቸውን ማወቅ፣

- የእለት ውሏቸውን በዘገባ መልክ መፃፍ እንዲቻሉ ማረጋገጥ፣
- ለሚቀርቡላቸው ጥያቄዎች በማስረጃ የተደገፍ ምላሾችን መስጠት መቻላቸውን መገምገም፣
- የቃላትን ተመሳሳይና ተቃራኒ ፍቺ ለይተው መረዳታቸውን መፈተሸ

<u>በናሙናነት ለተመረጡ ጥያቄዎች መልስ</u>

አንደኛ ሳምንት ፡ ሶስተኛ ቀን

ትምህርት ሶስት- ሶስት

ሀ/ ሰዎች እንዲወዱህ ውደዳቸው፡፡

ለ/ ሰዎች እንዲያከብሩህ አክብራቸው፡፡

ሐ/ ሰዎች እንዲያዳምጡህ አዳምጣቸው፡፡

መ/ ሰዎች እንዲፈልጉህ ፈልጋቸው፡፡

ሠ/ ሰዎች እንዲያደርጉልህ የምትሻውን መልካም ነገር አንተም አድርግላቸው፡፡

ሁለተኛ ሳምንት፤ ሁለተኛ ቀን

ትምህርት አምስት፡ ተመሳሳይ ቃላትን ማዛመድ

1. <u>ሐ</u> 2.<u>መ</u> 3.<u>ለ</u> 4.<u>ረ</u> 5.<u>ሀ</u> 6. <u>ሠ</u>

## ምዕራፍ ሦስት

## የሰው ልጆች አቅም

(12 ክፍለ ጊዜያት)

1. ርዕስ ፡- የሰው ልጆች አቅም
2. <u>የሚጠበቁ ውጤቶች</u>

ተማሪዎች ይህንን ትምህርት ከተማሩ በኋላ፦

- ስለ ስርአተ ፆታ የተፃፈ ምንባብ አዳምጠው ለጥያቄው ምላሽ ይሰጣሉ፡፡
- በችግር ፍቺ ክርክር ይሳተፋሉ፡፡
- በችግሩ ዙሪያ የመፍትሄ ሀሳብ ያቀርባሉ፡፡
- የምንባቡን ዋና ሀሳብ ይገልጻሉ
- ለመስሪያ ቤት ማመልከቻ ይጽፋሉ፡፡
- የቃላትን መዝገባ ቃላዊ ፍች ይለያሉ፡፡
- ምዕላዶችን በመነጠልና ማጣመር ይጽፋሉ፡፡
- ስርአተ ነጥቦችን በተገቢው ቦታ ይጠቀማሉ፡፡

3. ዝርዝር ይዘቶች

### ትምህርት አንድ ፡- ማዳመጥ

- የቅድመ ማዳመጥ ጥያቄዎችን በቃል ይመልሳሉ
- መምህሩ/ቷ ስለ ስረአተ ፆታ የተፃፈ ምንባብ ሲያነቡ ተማሪዎች በጥሞና ያዳምጣሉ
- የጊዜ ማዳመጥ ጥያቄዎች በቃላቸው ይመለሳሉ
- የድህረ ማዳመጥ ጥያቄዎችን በቃላቸው ይመልሳሉ

**ትምህርት ሁለት ፧መናገር**

- በትምህርት አንድ ስለ ስርአተ ፆታ ያገኙትን ግንዛቤ ያስታውሳሉ
- መምህሩ /ሯ የሚነግሯችሁን ማብራሪያ በጥሞና ያዳምጣሉ
- በሚኖሩበት አካባቢ ማህበረሰብ ውስጥ ስለ ስርአተ ፆታ ያለውን አመለካከትና ለሴት /ለወንድ የሚሰጠውን ሚና በተመለከተ በቡድን ይወያያሉ፡፡

**ትምህርት ሦስት ፡ የንግግር ክህሎት ማዳበር**

- ስለ ስርአተ ፆታ በማህበረሰባቸው ውስጥ ያለውን የተዛባ አመለካከትና ለወንድ/ ለሴት የሚሰጡትን ሚና በተመለከተ ያደረጉትን ውይይት አጭር ማስታወሻ ያዘጋጃሉ፡፡
- ያዘጋጁትን አጭር ማስታወሻ በመያዝ የደረሱበትን ድምዳሜ ለክፍል ጓደኞቻችሁ ያቀርባሉ

**ትምህርት አራት ፡ ችግር ፈቺ ክርክር**

- ተማሪዎች የአቶ ኤርጎጎንና የአቶ ላጲሶን በተፃራሪ ሀሳብ ላይ ያደረጉትን ክርክር ያስተውላሉ ፡፡
- ተማሪዎች ስለ ክስተቶቹ የአቶ ኤርጎጎን ወይንም የአቶ ላጲሶን ሀሳብ በመደገፍ የራሳቸውን ሀሳብ እያቀረቡ ይከራከራሉ

**ትምህርት አምስት፡- በአየር ንብረት ለውጥ ላይ መነጋገር**

- በትምህርት አራት ያደረጉትን ክርክር አስታውሰው አጭር ማስታወሻ ያዘጋጃሉ፡፡
- ያዘጋጁትን ማስታወሻ በመያዝ ለክፍል ጓደኞቻቸው በቃል ያቀርባሉ ፡፡

**ትምህርት ስድስት ፧- ዋና ሀሳብ ለማግኘት ማንበብ**

- የቅድመ ማንበብ ጥያቄዎችን በቃላቸው ይመልሳሉ፡፡
- ዋና ሀሳብ ለማግኘት የሚነበበውን ምንባብ ትኩርት ሰጥተው ያነባሉ፡፤
- የጊዜ ማንበብ ጥያቄዎችን በማስተዋል ይመልሳሉ
- የአንብቦ መረዳት/ የድህረ ንባብ ጥያቄዎችን ይሰራሉ፡፡

## ትምህርት ሰባት፡- የምንባቡን ዋና ሀሳብ መንገር

- በቡድን ተከፋፍለው "የሰው ልጆች አቅም " በሚለው ምንባብ ዋና ሀሳብ ዙሪያ ይነጋገራሉ፡፡
- የቡድኑን ሀሳብ ማስታወሻ ይይዛሉ
- የቡድኑን ሀሳብ በተወካዮቻቸው አማካኝነት ለክፍል ጓደኞቻቸው ያቀርባሉ፡፡

## ትምህርት ስምንት ፡-ማመልከቻ መፃፍ

- መ/ር ሉቦቴ ሎንግርች የደረጃ እድገት እንዲሰራለት ለደቡብ ኦሞ ዞን ትምህርት መምሪያ የፃፈውን ማመልከቻ በትኩረት ያነባሉ፡፡
- የማመልከቻውን ልዩ ልዩ አካሎች ባስተውሎት ያጠናሉ፡፡
- ማመልከቻ ሲፃፍ ማስታወስ ያለባቸውን ፍሬ ነገሮች ያነባሉ፡፡
- እነሱም በተመሳሳይ ሁኔታ የጠፋባቸውን የልደት /የወሳኝ ኩነት የምዝገባ የምስክር ወረቀት በድጋሚ ተሰርቶ እንዲሰጣቸው ለቀበሌያቸው አስተዳደር ጽ/ቤት ማመልከቻ ይጽፋሉ፡፡

## ትምህርት ዘጠኝ ፡- የጥሪ ደብዳቤ መፃፍ

- ለምሳሌነት የተሰጣቸውን የሰርግ ጥሪ ደብዳቤ አስተውለው ያነባሉ
- እነሱም የምረቃ የጥሪ ደብዳቤ ጽፈው ለመምህራቸው ያቀርባሉ፡፡

## ትምህርት አስር ፡- የቃላትን መዝገበ ቃላዊ ፍች መፈለግ

- መዝገበ  ቃላትን ተጠቅመው የቃላትን ፍች እንዴት መፈለግ እንደሚችሉ መምህር/ት ያሳያቸዋል/ ታሳያቸዋለች፡፡
- በምሳሌነት የተሰጣቸውን ቃል መዝገብ ቃላዊ ፍች ያመለከታሉ፡፡
- ለተሰጣቸው ቃላት ከመዝገብ ቃላት በመፈለግ ፍቻቸውን ይጽፋሉ፡፡

**ትምህርት አስራ አንድ፤- ምዕላዶችን መነጠልና ማጣመር**

- የተሰጣቸውን ምዕላድ የመነጠልና የማጣመር ምሳሌዎች ያስተውላሉ
- በምሳሌው መሰረት ምዕላዶችን ይነጥላሉ፡፡
- በምሳሌው መሰረት ምዕላዶችን ያጣምራሉ፡፡

**ትምህርት አስራ ሁለት፡- ስርአተ ነጥብ**

- የተሰጣቸውን ማስታወሻ  በትኩረት ያነባሉ፡፡
- መግለጫ  ያዳምጣሉ፡፡
- መልመጃዎችን ይሰራሉ፡፡

<u>**የምዕራፍ ማበልፀጊያ ጥያቄዎች**</u>

1. ስለ ስርአተ ፆታ የተፃፉ ልየ ልዩ ጽሁፎችን በማንበብ ፤ አጭር ማስታወሻ በመፃፍ፤ በክፍል ውስጥ ለጓደኞቻቸው ያቀርባሉ
2. በአካባቢያችሁ የሚገኙ አምስት ሰዎችን አነጋግረው፤ስለ ስርዓተ ፀታ ያላቸውን ግንዛቤና ስለ ሴትና ስለ ወንድ ስራ ( ሚና ) ያላቸውን አመለካከት ሁለት ገጽ ዘገባ ጽፈው ያቀርባሉ፡፡
3. የአየር ንብረት ለውጥን ምንነት፣ምክንያት፣የሚያስከትለውን ችግርና የመፍትሄ ሀሳብ የሚገልጽ ከሁለት ገጽ ያልበለጠ ድርሰት ይጽፋሉ፡፡
4. መታወቂያ  እንዲሰጣቸው ለቀበሌ አስተዳደር ማመልከቻ ይጽፋሉ፡፡

4. **የትምህርቱ አቀራረብ**

*መምህር*

ከዚህ በታች ዐበይት በሆኑ ጉዳዮች ዙሪያ ብቻ አጠቃላይ የአቀራረብ ብልሃቶች ቀርበዋል፡፡የቀረቡት ብልሃቶች ትምህርቱን ከሞላ ጎደል በተሳካ ሁኔታ ለመምህርት ያስችሎታል፡፡ነገር ግን እነዚህ ብልሃቶች ብቸኛ ናቸው ብለው ራስዎን በእነሱ ብቻ እንዳያጣሩ፡፡ እንደ ሁኔታዎች ጋባዥነት ወይም አስገዳጅነት ፤እንደ ትምህርት ቤትዎስዎ ተጨባጭ ሁኔታ የራስዎን ፈጠራዎችና የተሻሉ ዘዴዎችን በመጠቀም ተማሪዎችዎን ሊያግዟቸው ይችላሉ፡፡

## አንደኛ ሳምንት፤ አንደኛ ቀን

## ትምህርት አንድ ፡- ማዳመጥ

የምዕራፉ የመጀመሪያ ትምህርት በማዳመጥ ክህሎት ዙሪያ የሚያጠነጥን ነው፡፡ ለክህሎት አተገባበር እንዲረዳ ተብሎ ከዚህ በታች አንድ የሚደመጥ ምንባብ ቀርቧል ፡፡እሱም የተማሪዎቹን የማዳመጥ ክህሎት ግብ  አድርጉ የተመረጠ ነው፡፡ መጀመሪያ ተማሪዎቹ ለማዳመጥ እንዲዘጋጁ በልዩ ልዩ መንገድ ያነቃቋቸው፡፡የማዳመጥ ፍላጎታቸውን ሊያነቃቃ የሚችል አጭር ታሪክ /ተረት ቢጤ ሊያወጓቸው ይችላሉ፡፡የቅደመ ማዳመጥ ጥያቄዎችንም እንዲመልሱ ጊዜ ይስጧቸው፡፡

*የቅድመ ማዳመጥ ጥያቄዎች*

1. ስርአተ ፆታ ምንድነው?
2. በፆታና በስርአተ ፆታ መካከል ያለውን ልዩነት ግለፁ፡፡

መምህር የተማሪዎችዎ የማዳመጥ ፍላጎት መቀስቀሱን አረጋግጠው ከዚህ ቀጥሎ የቀረበውን ምንባብ ሁለት ጊዜ ወይም ሦስት ጊዜ ያንብቡላቸው፡፡

### ስርአተ ፆታ

ስርአተ ፆታ ማለት ሴቶችን ወይም ወንዶችን ብቻ  የሚመለከት ሳይሆን በመካከላቸው ያለውን ግንኙነትና ግኑኝነቱ ምን ያህል ማህበራዊ እውቅና

እንዲሚሰጠው የሚገለጽበት ጽንስ ሀሳብ ነው፡፡ሥርአተ ፆታ ማህበረሰቡ ለሴቶች እና ለወንዶች በፆታቸው ምክንያት የሚሰጣቸው ቦታ እንዲሁም የሚወስንላቸውን ሚና ይመለከታል፡፡ ፆታ ግን ሰዎች ሁሉ በተፈጥሮ የሚላበሱት ስብዕና ሲሆን ወንድ ሆኖ መወለድ እና ሴት ሆኖ መወለድ ነው፡፡

ሰዎች ሴት ወይም ወንድ ሆነው ከተወለዱ በኂላ እንደማህበረሰሁ ባህልና አመለካከት የሴቶችና የወንዶች ሚና ይለያያል፡፡ ያደጉበት ማህበረሰብ እንደ ፆታቸው ተገቢና ተስማሚ ነው ብሎ የሚያምንበትን ባህሪ፣አመለካከት፣ ሚናቸውንና እራሳቸውን ከሌሎች ጋር እንዴት ማግባባት እንደሚችሉ ትምህርት ይሰጣቸዋል፡፡

በስርአተ ፆታ ላይ የተመሰረተ የሴቶችና የወንዶች ሚና እንደየባህሉ፣ በአንድ ባህልም ውስጥ እንደየማህበራዊ ቡድኖች ይለያያል፡፡ ኢኮኖሚያዊ ሁኔታዎችና እድሜ የሴትና የወንድ ሚና ምን መሆን እንደሚገባቸው ይወስናሉ፡፡ እንደሚታወቀው ሁሉ ባህል፣ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ሁኔታዎች ይለዋወጣሉ፡፡ በዚህ የለውጥ ሂደት ውስጥ የስርአተ ፆታ ገጽታም ይለወጣል፡፡

በአጠቃላይ ስርአተ ፆታ ከህብረተሰቡ አባላት የሚጠበቁ የሴትነትና የወንድነት መለያዎች የሚገነቡበት በሰዎች ማህበራዊ ግንኙነት ሂደት ውስጥ የሚገኝ ትምህርት ነው፡፡

በእኛ ህብረተሰብ ውስጥ ያለውን ተጨባጭ ሁኔታ ስንመለከት ስናራምድ የቆየነው የስርአተ ፆታ ግንኙነት ለወንዱ ያደላ መሆኑን እንገነዘባለን፡፡ የነበረው የስርአተ ፆታ ግንኙነት ውጤትም የሴቶች ቁጥር በውሳኔ ሰጪነት ቦታ፣ ኢኮኖሚን በመቆጣጠር ረገድ፣ በትምህርት ተሳትፎ ወዘተ. በጣም አንሶ እንዲገኝ አድርጎታል፡፡

መምህር አንድ አፍታ ማንበብዎን ቆም ያድርጉና የሚከተሉትን የማድመጥ ጊዜ ጥያቄዎችን ለተማሪዎችዎ ያንብቡላቸው፡፡

1. የስርአተ ፆታ ገጽታ ይለውጣል ሲባል ምን ማለት ነው?
2. ስናራምደው የቆየነው የስርአተ ፆታ ግንኙነት ለወንድ ያደላ መሆኑን አመልካች ነገሮችን ጥቀሱ፡፡

አሁን በአለንበት ስርዓት መንግስት የህብረተሰቡ ግማሽ አካል የሆኑትን ሴቶች ሳያሳትፍ የተፈለገውን ልማት ማምጣት እንደማይቻል በመረዳት የሴቶችን ኢኮኖሚያዊ፣ማህበራዊና ፖለቲካዊ ተሳትፎ ለማሳደግና የፆታ እኩልነትን ለማረጋገጥ የህጎች ሁሉ የበላይ በሆነው ህገ መንግስት ውስጥ የሴቶችን ጉዳይ በስፋት ማካተቱና ብሔራዊ የሴቶች ጉዳይ ፖሊሲን ማውጣቱ ጉዳዩ በሁሉም አካል ትኩረት ሊሰጠው የሚገባ መሆኑን ያመላክታል፡፡

ከተዛባው የስርአተ ፆታ ሚናና አድሎአዊ የሥራ ክፍፍል የተነሳ በሴቶች ላይ የሥራ ጫናውና ጭቆናው ስለሚበዛ ግንኙነታቸውም አንዱ የበላይ ሌላው የበታች እንዲሆን በማድረግ ሴቶችን ለፆታዊ ጥቃት፣ለሥነ-ተዋልዶ ጤና ችግር ለኤች አይ ቪ ኤድስና ለድህነት ሰለባ እንዲሆኑ አድርጓል፡፡ ይህ ሁኔታ ደግሞ የእኩልነትና የሰብአዊ መብት ጥያቄን የሚያስነሳ ከመሆኑም ባሻገር ሴቶች ከወንዶች እኩል በሀገር ልማት (እድገት) ሊኖራቸው የሚገባውን ንቁ ተሳትፎ የሚያሳንስ መሆኑን ግልጽ ነው፡፡

የስርአተ ፆታ እኩልነት ለአንድ አገር ልማት ወሳኝ ሚና አለው፡፡ የልማት ዋነኛ ግብ የዜጎች ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ሁኔታ/ደረጃ/ በዘላቂነት ማሻሻልና ሁሉንም ዜጎች ተጠቃሚ ማድረግ ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የአንድ አገር የእድገት ደረጃ የሚወሰነው በተፈጥሮ የተገኙትን ሰብአዊ መብቶች ለሁሉም ዜጎች (ወንድ እና ሴት) ያለምንም መሸራረፍና ልዩነት በእኩልነት ሲከበሩና ሲጠበቁ ነው፡፡ ስለዚህ የስርዓተ ፆታ ጥያቄ የሀገር ልማት ጉዳይ በመሆኑ ትኩረት ያሻዋል፡፡

ስርአተ ፆታን ማካተት ማለት ማንኛውንም መርሃ-ግብር፣ ሕጎች ፣ፖሊሲዎች ወይም ኘሮግራሞች በሴቶችና በወንዶች ላይ ያላቸውን ተጽዕኖ በየትኛውም ደረጃ መፈተሽ ነው፡፡ ይህ ስልት የሁለቱንም ፆታ ሚናና አስተዋጽኦ በሁሉም የኘሮጀክት ደረጃዎች ማለትም በዕቅድ፣ በአፈፃፀም እንዲሁም በክትትልና ግምገማ ላይ እኩል በማሳተፍ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ያደርጋል፡፡ ስርዓተ ፆታን በልማት ማካተት ዋንኛው ግብ የፆታ እኩልነትን እውን ማድረግ ነው፡፡

ምንጭ፡-ጀስቲስ ፎር ኦል-ኘሪዝን ፌሎሺፕ ከጌዴኦ ዞን ምክር ቤት ጋር በመተባበር ለስልጠና ካዘጋጀው ሰነድ የተወሰደ፡፡

የድህረ ማዳመጥ ጥያቄዎች

1. ፆታና ስርአተ ፆታን በማነፃፀር በቡድን ተወያዩና የደረሳችሁበትን ድምዳሜ ለክፍል ጓደኞቻችሁ ተናገሩ፡፡
2. ስርአተ ፆታን የማካተት ግብ በምንባቡ መሰረት ግለፁ፡፡

መምህር/ት ተማሪዎች የድህረ ማድመጥ ጥያቄዎችን በሚሰሩበት ጊዜ ሁሉም መሳተፋቸውን የመከታተል ፣የማገዝና የማበረታታት ሚና ይጫወቱ፡፡

## አንደኛ ሳምንት፤ ሁለተኛ ቀን

## ትምህርት ሁለት ፡- መናገር

መምህር ተማሪዎችን በቡድን ሆነው ባለፈው ክፍለ ትምህርት ያገኙትን ግንዛቤ እንዲያስታውሱ ይንገሯቸው፡፡ እርስዎም አጭር ማብራሪያ ይስጧቸው፡፡ ተማሪዎች በሚኖሩበት ማህበረሰብ ውስጥ ስለ ስርአተ ፆታ ያለውን አመለካከትና ለወንድና ለሴት የሚሰጠውን ሚና በአምስት፣አምስት አደራጅተው እንዲወያዩበት ያድርጉ፡፡ የእርስዎ ክትትልና ድጋፍ አይለያቸው፡፡

## አንደኛ ሳምንት፤ ሶስተኛ ቀን

## ትምህርት ሦስት ፡- የንግግር ክህሎትን ማዳበር

መምህር ባለፈው ክፍለ ጊዜ የተመሰረተው ቡድን እንደተጠበቀ ይሁን፡፡ ተማሪዎች ባለፈው ክፍለጊዜ ያደረጉትን ውይይት እንዲያስታውሱና አጭር ማስታወሻ እንዲጽፉ ያድርጓቸው፡፡በማስታወሻ የተፃፈው ሃሳብ የቡድኑ የጋራ ሃሳብ መሆኑን ለማረጋገጥ በጋራ አንብበው ያጽድቁት፡፡ የየቡድኑ ተወካዮች አጭሩን ማስታወሻቸውን እያዩ ለክፍል ጓደኞቻቸው ሀሳባቸውን በንግግር ያቅርቡ፡፡ በመጨረሻም እርስዎ ያጠቃልሉላቸው፡፡

## ሁለተኛ ሳምንት፤ አንደኛ ሳምንት

## ትምህርት አራት፡- ችግር ፈች ክርክር

መምህር ተማሪዎችዎ በአነስተኛ ቡድን ይደራጁ፡፡ በቡድን ከተደራጁ በኋላ የአቶ ኤርጎንና የአቶ ላጺሶን ሀሳብ ያንብቡ፡፡ እያንዳንዱ ቡድን ሁለት ቦታ ተክፍለው ስርአት ባለው ሁኔታ እርስ በርስ ይከራከሩ፡፡ የእያንዳንዱን ቡድን ክርክር የሚመራ አንድ ሰው ቢኖር ጥሩ ነው፡፡ ሁሉም ተማሪዎች በክርክሩ መሳተፋቸውንና ሀሳባቸውን በማስረጃ እያስደገፉ መከራከራቸውን እየተዟዟሩ ይከታተሉ፡፡

## ሁለተኛ ሳምንት፤ ሁለተኛ ቀን

## ትምህርት አምስት፡- በአየር ንብረት ለውጥ ላይ መነጋገር

መምህር ተማሪዎችዎ ባለፈው ክፍለ ትምህርት በተሳተፉበት ቡድን እንዲገኙ ያድርጉ፡፡ ባለፈው ክፍለ ትምህርት ያደረጉትን ክርክር በማስታወስ አጭር ማስታወሻ ያዘጋጁ፡፡ እንዲሁም ስለመፍትሄው በጋራ ይነጋገሩ እና የደረሱበትን ድምዳሜ በማስታወሻ ያስፍሩ፡፡ በመጨረሻም ሃሳባቸውን ከየቡድኑ አንድ አንድ ተወካይ ለክፍል ጓደኞቻቸው በቃል ያቅርቡ፡፡ በተቻለ መጠን አቅርቢዎቹ በየጊዜው እንዲቀያየሩ ቢደረግ የሁሉንም ተማሪዎች ተሳትፎ የበለጠ ማረጋገጥ ይቻላል፡፡

**ሁለተኛ ሳምንት፤ ሶስተኛ ቀን**

**ትምህርት ስድስት፡- ዋና ሀሳብ ለማግኘት ማንበብ**

መምህር ተማሪዎችዎ አምስት አምስት ሆነው በቡድን ይደራጁ፡፡ ከምንባብ ለወጡ ቃላት የራሳቸውን ፍች ይስጡ፡፡ "የሰው ልጆች አቅም" የሚለውን ምንባብ ዋና ሀሳብ ለማግኘት ያንብቡ፡፡ እያነበቡ የማንበብ ጊዜ ጥያቄዎችንም ለመመለስ ይሞክሩ፡፡ ጥያቄዎቹ ምን ያህል ምንባቡን እየተረዱ እንደሆነ ያሳያሉ፡፡ምንባቡን አንብበው ከጨረሱ በኋላ የድህረ ንባብ /አንብቦ የመረዳት ጥያቄዎችን ይስሩ፡፡ አስፈላጊ ከሆነ ምንባቡን በከፊል ወይም ሙሉ በሙሉ ደግመው እያነበቡ መሞከር ይችላሉ፡፡

**ሶስተኛ ሳምንት፤ አንደኛ ቀን**

**ትምህርት ሰባት ፡- የምንባቡን ዋና ሀሳብ መናገር**

መምህር ተማሪዎችዎ ባለፈው ክፍለ ትምህርት በነበሩበት ቡድን መደራጀታቸውን ያረጋግጣሉ፡፡ "የሰው ልጆች አቅም" የሚለውን ምንባብ ዋና ሀሳብ ምንነት በተመለከተ ተነጋግረው የደረሱበትን ሀሳብ በአጭር ማስታወሻ ያስፍሩ፡፡ የደረሱበትን የመጨረሻ ሀሳብ በተወካያቸው አማካይነት ለክፍል ጓደኞቻቸው በቃል ያቅርቡ፡፡

**ሶስተኛ ሳምንት፤ ሁለተኛ ቀን**

**ትምህርት ዘጠኝ ፡- ማመልከቻ መፃፍ**

መምህር ተማሪዎችዎ በምሳሌነት የቀረበውን ማመልከቻ በጥሞና እንዲያነቡና ማመልከቻ ሲጽፉ ማስታወስ ያለባቸውን ፍሬ ነገር እንዲያነቡ ያድርጓቸው፡፡ ከዚያ በኋላ የጠፋባቸውን የልደት የወሳኝ ኩነት ምዝገባ ሰነድ በድጋሚ

እንዲሰጣቸው ለቀበሌያቸው ማመልከቻ ይፃፉ፡፡ እርስዎ ተማሪዎችዎ የፃፉትን በማየት ማረሚያ ይስጧቸው፡፡

**ሶስተኛ ሳምንት፤ ሶስተኛ ቀን**

**ትምህርት ዘጠኝ ፡- የጥሪ ደብዳቤ መፃፍ**

መምህር ተማሪዎችዎ የሰርግ የጥሪ ደብዳቤውን አስተውለው ያንብቡ፡፡ የጥሪ ደብዳቤው ምን ምን ነገሮችን እንደያዘ ያስተውሉ፡፡ የሰርግ ጥሪ ደብዳቤውን ምሳሌነት በከታተል የምረቃ ጥሪ ደብዳቤ በየግላቸው ጽፈው ጥንድ ጥንድ ሆነው ለጓደኞቻቸው ካነበቡና ካስተካከሉ በኋላ ለእርስዎ ያቅርቡ፡፡

**አራተኛ ሳምንት፤ አንደኛ ቀን**

**ትምህርት አስር ፡- የቃላትን መዝገበ ቃላዊ ፍች መፈለገ**

መምህር በትምህርት መዝገበ ቃላት በትምህርት ቤትዎ ቤተ መፃህፍት ካለ ተማሪዎቹዎን ወደ ቤተ መፃህፍቱ ይዘው በመሄድ ወይንም በርከት ያሉ መዝገበ ቃላትን ወደ ክፍል እንዲያመጡ በማድረግ በመዝገበ ቃላት እንዴት መጠቀም እንደሚቻል ለተማሪዎችዎ ያሳዩ፤ ያለማምዷቸው፡፡ ይህ ልምምድ የተሳካ መሆኑን ካረጋገጡ በኋላ ተማሪዎች ለተሰጡአቸው ቃላት መዝገበ ቃላዊ ፍች እንዲፈልጉ ያድርጉ፡፡ እርስዎም በየጠኤዛው እየሄድ ስራቸውን ያግዟቸው፡፡

**አራተኛ ሳምንት፤ ሁለተኛ ቀን**

**ትምህርት አስራ አንድ፡- ምዕላዶችን መነጠልና ማጣመር**

በሰባተኛ ክፍል ትምህርት ስለ ምዕላድ የተማሩትን እንዲያስታውሱ ይንገሯቸው፡፡

እርስዎም ስለ ምእላድ ዋና ሀሳቦች የሚገልጽ መግቢያ ይስጧቸው፡፡ ምዕላዶችን የመነጠልና የማጣመር ልዩ ልዩ ምሳሌዎችን እየሰጡ ያሳዩዋቸው፡፡ አሳታፊ በሆነ ዘዴ ተማሪዎችን መነጠልና ማጣመርን እንዲለማመዱ እድል ይስጧቸው፡፡ እርስዎም ያግዟቸው፡፡ በመጨረሻም ተማሪዎች እራሳቸውን ችለው መነጠልና ማጣመርን እንዲሰሩ ይተዋቸው፡፡ በትክክል መፈፀማቸውን ተከታትለው እርማት ይስጧቸው፡፡

**አራተኛ ሳምንት፤ ሶስተኛ ቀን**

**ትምህርት አስራ ሁለት፡- ስርአተ ነጥብ**

መምህር ተማሪዎችዎ በማስታወሻው የቀረቡትን የስርአተ ነጥብ አይነቶች እና አገልግሎታቸውን በትኩረት እንዲነቡ ያድርጓቸው፡፡ እርስዎም ገለፃና ምሳሌ ያድርጉላቸው፡፡ መልመጃዎችን ያስሰሯቸው፡፡

**የምዕራፉ ማበልጸጊያ ጥያቄዎች**

በምዕራፉ ውስጥ ተማሪዎችዎ በዋናነት ማዳበር ያለባቸውን ክህሎቶችና እውቀቶችን የያዙ ስለሆነ የእርስዎ ድጋፍ ሳይለያቸው እንዲሰሯቸው ያድርጉ፡፡

**5.ግምገማ**

- ምንባብ ሲነበብላቸው አዳምጠው መረዳታቸውን ለማረጋገጥ ጥያቄዎችን እየጠየቁ ማረጋገጥ

- በቀረበላቸው ርዕስ ጉዳይ ላይ ንቁ ተሳትፎ አድርገው መከራከራቸውን መከታተል እና በመጨረሻ የመፍትሄ ሀሳቦችን እንዲያቀርቡ በማድረግ የንግግር ችሎታቸውን ማጤን
- የምንባብ ዋና ሀሳብ መረዳታቸውን ማረጋገጥ
- ማመልከቻ መፃፍ መቻላቸውን መከታተል
- የጥሪ ደብዳቤ መፃፍ መቻላቸውን መከታተል
- የቃላትን መዝገበ ቃላዊ ፍች መፈለግ መቻላቸውን ማረጋገጥ
- ምዕላዶችን መነጠልና ማጣመር መቻላቸውን ማረጋገጥ

7. **በናሙናነት የተመረጡ ጥያቄዎች መልስ**

**ትምህርት ስድስት**

**መልመጃ አንድ ፡- እውነት/ ሀሰት**

1. እውነት 2. እውነት 3. እውነት 4. እውነት 5. እውነት

**ትምህርት አስራ አንድ ፡- ለቃላት መዝገበ ቃላዊ ፍች መፈለግ**

1. ወገን (የእንስት ወይም የተባዕት)
2. - አንድ ነገር የሚሰራበት ወይም የሚከናወንበት ደንብ፣ ህግ
   - ወግ፣ ባህል
3. - ቦታ፣ ጎራ
   - የስራ ድርሻ
4. - ዕጣ ክፍል፣ ግንባር
   - ድርሻ

5 - ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ እድገት፣ ብልጽግና፣ ግንባታ

- ጥሩ፣ መልካም ተግባር

**ትምህርት አስራ ሁለት፡- ስርአተ ነጥብ**

1. ሆዴ ባዶ ነው፤ የመመገብ ፍላጎት ግን የለኝም፡፡
2. ‹‹ ተግባርና ሳይንስ፣ ከእነዚህ ሁለት ሀይላት የሚልቅ ነገር በምድር ላይ የለም፡፡ ›› ማክሲም ጎርኪ፡፡
3. እማዬ ! እባቡ መጣብኝ ! ፡፡
4. ወንድሜ ጃኬት ፣ ሱሪ ፣ ሸሚዝና ጫማ ገዛልኝ፡፡

## ምዕራፍ አራት

## አካቶ ትምህርት

9 ክ/ጊዜ

1. ርዕስ ፡ አካቶ ትምህርት

2. የሚጠበቁ ውጤቶች

ተማሪዎች ይህን ትምህርት ከተማሩ በኋላ

- ሳይንስና ቴክኖሎጂን ያካተተ መረጃ የያዘ ጽሑፍ አዳምጠው አስተያየት ይሰጣሉ፡፡
- ስእሎችንና ሁነቶችን በመተንተን የተጓደሉ ሃሳቦችን ያሟላሉ፡፡
- በማህበራዊ ጉዳዮች ላይ ውይይት በማድረግ ይሳተፋሉ፡፡
- ያልተሟሉ አረፍተ ነገሮችን የያዘ አንቀጽ ያሟላሉ፡፡
- የቃላትን መሰረት በመለየት ቃላትን ይመሰርታሉ፡፡
- ቃላትን በቃል ክፍሎቻቸው መሰረት ይመድባሉ፡፡

3.ዝርዝር ይዘቶች

ሀ ማዳመጥ

ትምህርት አንድ ፡- ማዳመጥ

- ለማዳመጥ ዝግጁ የሚያደርጓቸውን የቅድመ ማዳመጥ ጥያቂዎችን ይሞክራሉ፡፡
- የሚቀርብላቸውን ምንባብ በትኩረት ያዳምጣሉ፡፡
- በዳመጡት ምንባብ መሠረት ልዩ ልዩ ጥያቄዎችን ይመልሳሉ፡፡

ትምህርት ሁለት፡- የንግግር ክሂልን ማዳበር

- **በቴክኖሎጂ መሰረተ ልማት** ጉዳይ ላይ የተመለከቱ መረጃዎችን መሰረት በማድረግ ይናገራሉ፡፡

ለ.ማንበብ

ትምህርት ሶስት፡-

- ለማንበብ ዝግጁ የሚደርጓቸውን ቅድመ ንበብ ጥያቄዎችን በቃል ይመልሳሉ፡፡
- የቀረበላቸውን ምንባብ አስተካክለው ያነባሉ፡፡
- ባነበቡት ምንባብ መሠረት የድህረ ንባብ ጥያቄዎችን ይመልሳሉ፡፡

ሐ. መጻፍ

ትምህርት አራት፡- ጅምር አንቀጾችን ማጠናቀቅ(ማሟላት)

- ጅምር አንቀጾችን ያጠናቅቃሉ፡፡
- አንቀጽ ይጽፋሉ፡፡

4. የትምህርቱ አቀራረብ

ትምህርት አንድ፤ማዳመጥ

መምህር/ት

ከዚህ በታች አበይት በሆኑ ጉዳዮች ዙሪያ ብቻ አጠቃለይ የአቀራረብ ብልሃቶች ቀርበዋል፡፡ ቢመለከቷቸው ትምህርቱን ከሞላ ጎደል በተሳካ ሁኔታ ለመምራት ያስችሉዎታል፡፡ ነገር ግን እነዚህ ብልሀቶች ብቸኛ ናቸው ብለው ራስዎን በእነሱ ብቻ እንዳያጥሩ፡፡ እንደሁኔታዎች ጋባዥነት ወይም አስገዳጅነት እየተመለከቱ፣ የራስዎን ፈጠራዎችንና የተሻሉ ዘዴዎችን በመጠቀም ተማሪዎቹን ሊያግዟቸው ይችላሉ፡፡

የምዕራፍ የመጀመሪያ ትምህርት በማዳመጥ ዙሪያ የሚያጠነጥን ነው፡፡ ለክሂሉ አተገባበር እንዲረዳ ተብሎ ከዚህ በታች አንድ ምንባብ ቀርቧል፡፡ ምንባቡም የተማሪዎችን የማዳመጥ ክሂል ግብ አድርጎ የተመረጠ ነው፡፡ መጀመሪያ ተማሪዎች ማዳመጥ እንዲጀምሩ በተለያየ መንገድ ያነቃቋቸው፡፡ በመቀጠል ለማዳመጥ ዝግጁ የሚያደርጓቸውን የቅድመ ማዳመጥ ጥያቄዎችን በመጠየቅ የቀደመ እውቀታቸውን ተጠቅመው የቁልፍ ቃላትን ፍች እንዲናገሩ ያድርጓቸው፡፡ ከዚያም ምንባቡን ያንብቡላቸው፡፡ ምናልባትም ምንባቡን ቶሎ ላይረዱት ስለሚችሉ ደግመው ያንብቡላቸው፡፡ ከዚያም ምንባቡን አስመልክቶ በተማሪዎች መጽሃፍ ላይ በቀረቡት ጥያቄዎች ዙሪያ ያወያዩዋቸው፡፡

ለማዳመጥ የቀረበው ምንባብ ‹‹በቴክኖሎጂ ታግዞ መማር››የሚል ነው፡፡

ለ.ትምህርት ሁለት፡- መናገር

ትምህርት ሁለት የንግግር ክሂል የሚዳብርበት ይዘት ነው፡፡ አስቀድሞ ሲነበብ ያዳመጡትን (ስለ ቴክኖሎጂ ታግዞ መማር የሚያወራውን ምንባብ) መነሻ በማድረግ ባዳመጡት ጉዳይ ላይ ያስተዋሉትን በቡድን ሆነው እንዲወያዩበት ያደርጓቸው ፡፡ በዚህ ወቅት በየቡድኑ ያሉ ተማሪዎች ሁሉም እንዲሳተፉ ክትትል በማድረግ ያበረታቷቸው፡፡ለውይይት የተሰጣቸው ጊዜ ሲያልቅ የአንዳንዱ ቡድን በተወካዩ ዓማካይነት በክፍል ጋደኞቻቸው ፊት እየተነሱ የንግግር ክሂል ልምምድ አንዲያደርጉ ይርዷቸው፡፡

ሐ.ትምህርት ሶስት፡- ማንበብ

መምህር/ት

ተማሪዎች በመማሪያ መጻህፋቸው ላይ በአካቶ ትምህርት ላይ የተጻፈውን ምንባብ ከማንበባቸው በፊት ቅድመ ንባብ ጥያቄዎችን እንዲመልሱ ያበረታቷቸው፡፡ በመቀጠል ምንብቡን በግል እንዲያነቡ ያድርጓቸው፡፡ ከዚያም ማንበባቸውን ገታ አድርገው የንባብ ጊዜ ጥያቄዎችን አንዲመልሱ ይጠይቋቸው፡፡ ለቀረቡላቸው ጥያቄዎች ምላሽ ከሰጡ በኋላ ቀሪውን የንባብ ክፍል እንዲያጠናቅቁ ይንገሯቸው ፡፡ ማንበቡን ሲያጠናቅቁ ከምንባብ የወጡ ጥያቄዎችን ያሰሯቸው፡፡

መ. መጻፍ

ትምህርት አራት ፡- አንቀጽ ማጠናቀቅ

ተማሪዎች በመማሪያ መጽሐፋቸው ላይ ተጀምሮ የቀረ አንቀጽ አለ ፡፡ ይህን ጅምር አንቀጽ አንብበው ቀሪውን ሃሳብ ሲያሟሉ የአንቀጽ አረፍተ ነገሮች ተያያዥነትን ይማሩበታል፡፡ የተወሰኑ ምሳሌዎችን በመሳየት ማብራሪያ ይስጧቸው ፡፡ በመቀጠል ጥቂት አረፍተ ነገሮችን በመጨመር ምሳሌዎችን ከእርሶ ጋር አብረው እንዲሰሩ ያበረታቷቸው፡፡ በመጨረሻም በተሰጣቸው ምሳሌ መሠረት አንዲሰሩ ያድርጓቸው ፡፡

ትምህርት አምስት፡- ቃላት ምስረታ

ተማሪዎች ከሌሎች ቃላት አዳዲስ ቃላትን ይመሰርታሉ፡፡ በቃል ምስረታ ሂደቱ ቃሉ የተገኘበትን የቃል ክፍል ይጠቁማሉ፡፡

ትምህርት ስድስት፤ ስዋስው

- ቃላትን በቃል ክፍሎች መመደብ

ተማሪዎች ቃላትን በቃል ክፍሎቻቸው ይመድባሉ። ለዚህ ተግባር አስፈላጊ የሆኑ ስም፣ተውላጠ ስሞች፣ግስና የግስ ምሳሌዎች ሰርተው ያሳዩ።

5. መርጃ መሳሪያዎች :-
   የድረ ገጽ መረጃዎች፣የእጅ ስልክ ፣የሬዲዮ ትምህርት፣

6. ግምገማ :-

   - የማዳመጥ ጥያቄዎችን በትክክል መመለሳቸውን ማረጋገጥ
   - በተሠጣቸው ርእስ ላይ በንቃት መወያየታቸውንና ተሳትፎ ማድረጋቸውን መከታተልና ግብረ መልስ መስጠት።
   - ስላነበቡት ነገር የተረዱትን በመጠየቅ መረዳታቸውን ማረጋገጥ
   - የአንቀጽ ቀሪ ክፍሎችን ለይተው መረዳታቸውን አንቀጽ መመስረታቸውን ማረጋገጥ።

7.በናሙናነት ለተመረጡ ጥያቄዎች መልስ

በምእራፉ የመጨረሻ ገጽ ላይ ያገኙታል።

አንደኛ ሳምንት አንደኛ ቀን

ትምህርት አንድ ፤ ማዳመጥ

ሀ.ማዳመጥ

ቅድመ ማዳመጥ ጥያቄዎች

ተግባር አንድ :<u>ከዚህ በታች የሚገኘውን ምንባብ ድምጽን ከፍ አደርገው ያንብቡላቸው። የቅድመ ማዳመጥ ጥያቄዎችን በማንሳት ለማዳመጥ ትምህርት ያዘጋጇቸው።</u>

1. ማሕበራዊ ተስስር /ፌስ ቡክ/፣ድረ ገጽ /ዌብ ሳይት/ ፤ በይነ መረብ /ኢንተርኔት/ሲባል ሰምታችኋል?

ምን ማለት ይምስላችኋል?
እንደ ልጆቹ ግምት መልሳቸው ሊለያይ ይችላል፡፡

## በቴክኖሎጂ ታግዞ መማር

የሰው ልጅ ተፈጥሮ በሰጠው አእምሮና ጉልበት ተጠቅሞ ኑሮውን ምቹ ለማድረግ ሲጥር ቆይቷል፡፡ ለዚህም የሚኖርበትን፣ የሚሰራበትን፣የሚጠቀምበትን ሁሉ በየጊዜው ለማዘመን ሲል በስራ ደክሟል፣ያለውን ሐብት አሟጦ፣የጥበብ ተሰጦውንና ችሎታውን ተጠቅሞ ድንቅ የሆኑ ፈጠራዎችን አግኝቷል፡፡

ያገኛቸው የፈጠራ ስራዎች ባሉበት ቆመው አልቀሩም ፡፡ እነዚህ ፈጠራዎች በየጊዘው እየተሻሻሉ በመምጣታቸው ተአምራዊና በሰው እጅ የተሰሩ እስከማይመስሉ ድረስ አስደናቂ ሆነዋል፡፡በጉልበቱ ሊሞክረው የማይችለውን አቅም ፈጥረውለት የማይናደውን ግዙፍ ተራራ እንኳን ሜዳ ለማድረግ እስኪችል ድረስ ቀላል አደርገውለታል፡፡

በሰለጠኑት አገሮች የቴክኖሎጂ ምጥቀት ለሰው ልጅ ያስገኘው ትሩፋት ከመኖሪያ ቤት ጥቃቅን ተግባራት በመሳተፍ አገልግሎት ከመስጠት ጀምሮ እስከ ከባድ ኢንዱስትሪዎች ድረስ ይዘልቃል፡፡ ቤት ማጽዳት፣ መላላክ፣ቤት መገንባት፣ትልልቅ ማሽኖችን በአስደናቂ ቅልጥፍና፣ በታቀደ ጊዜና በሚፈለግ የአግልገሎት መጠን ስራን መከናወን መቻሉ ደግሞ ምቾትን በመስጠት እርካታን አጎናጽፏል፡፡

በ 21ኛው ክ / ዘመን የቴክኖሎጂ ስርጸት መዳበር የተነሳ የሰው ልጅ ፍላጎቱን ለመፈጸም የሚጠቀምባቸው መሳሪያዎች በሁሉም የሙያ ዘርፎች በአልግሎት ላይ እየዋሉ መምጣቸው ተፈላጊነታቸውን ጨምሯል፡፡ የአገልግሎት እርካታ ፍላጎትን በመጨመሩ በዚያው መጠን የቴክኖሎጂ ፈጠራውም አድጓል፡፡ ይህ አሰራር በሰለጠነው አለም ብቻ ተወስኖ አልቀረም፡፡በታዳጊ አገሮችም ቢሆን ባንዳንድ ተቋማት ላይ በጥቅም ላይ ውለዋል፡፡

**እስካሁን ባደመጣችሁት ጽሑፍ ምን ተገነዘባችሁ?**

በታዳጊ አገሮች የቴክኖሎጂ መሰረተ ልማት ያደገ ባይሆንም በመረጃ ልውውጥ ሂደት ላይ ባላቸው ፍጥነት፣ ቅለትና አመቺነት ምክንያት መሳሪያዎቹ ተወዳጅነትን አትርፈዋል፡፡

ቴክኖሎጆን በመጠቀም ከልማዳዊ፣ አዝጋሚና  አድካሚ አሰራር ወጥቶ ፈጣን ቀልጣፋና አርኪ አሰራር የሚከተል ተቋም መፍጠር እንዲቻል መሰረተ ልማቱን ማዘመን ያስፈልጋል፡፡በዚህ ዘርፍ መልማት ከሚገባቸው ተቋማት አንዱ ትምህርት ነው፡፡

ትምህርት ዘመኑ የሚጠይቀውን ቴክኖሎጂ ታጥቆ የመማር ማስተማሩን ሂደት ለማሳደግ አንዲችል የሰለጠነ የሰው ሐይልና የተሟላ ግብአት መፍጠር ከፍተኛ ወጪን ይጠይቃል፡፡ ወጪ የሚጠይቅ ቢሆንም ከጊዜው ጋር አብሮ የሚሄድ ትምህርትና የትምህርት መሳሪያዎችን ቀስ በቀስ ኢያሳደጉ መሄድ ያስፈልጋል፡፡

ከኖራ ዱቄት የተሰራ ጠመኔ ተጠቅሞ በተቆራረሰ ሰሌዳ ላይ ከሚጽፍ መምህር፣ ከአቅማቸው በላይ የሆኑ መጽሐፍትን ተሸክመው ከሚንገላቱ ተማሪዎች ድካም የሚገላግል በቴክኖሎጂ የታገዘ  ዘመናዊ የመማር ማስተማር አሰራር ያስፈልጋል፡፡ጥቂትም ቢሆን በአንዳንድ ተቋማት መተግበር ተጀምሯል፡፡ ይህ አሰራር ተጠናክሮ ሊቀጥል ይገባል፡፡ እኛም የአጠቃቀም ስልቱን ለመማርና በተግበር ለማዋል መዘጋጀት ይጠበቅብናል፡፡

ከእጅ ስልካችን ጅምሮ አስከ ፕላዝማ ቴለቪዥን በመጠቀም ትምህርታዊ መረጃዎችን በቀላሉ ተደራሽ በማድረግና መምህራንና ተማሪዎችን ከልማዳዊ አሰራር ነጻ ለመውጣት የሚቻልበትን ድረ ገጽ /ዌብ ሳይት / ማሕበራዊ ትስስር ገጽ/ ፌስ ቡክ/ በይነ መረብ /ኢንተርኔት /አገልግሎት ማስፋፋት ያስፈልጋል፡፡

በአዘጋጆቹ

ድህረ ማዳመጥ

1. ባዳመጣችሁት ንባብ ውስጥ ቴክኖለጂ ከምን ጋር ተያይዞ ቀርቧል፡፡
2. ልማዳዊ አሰራር የተባለው ምንድነው?
3. የእጅ ስልካችንና ፕላዝማዎች ምን እንዲደረግባቸው የንባቡ ሃሳብ ይጠቁመናል፡፡

አንደኛ ሳምንት፡ሁለተኛ ቀን

ትምህርት ሁለት፡ መናገር

በሚከተሉት ርእሶች ላይ በቡድን ከፍለው ያወያዩ፡፡

- ቴክኖሎጂን ለሀገር ልማት እንዴት መጠቀም ይቻላል?

- የአጅ ስልክን ለምን ለምን አገልግሎት ሲውሉ ታዝባችኋል?
- ኢንተርኔት ለምን የሚያገለግል ይመስላችኋል? ሀገርን ለመገንባት የሚውልበት መንገድ አለ ብላችሁ ታስባላችሁ?

አንደኛ ሳምንት፤ሶስተኛ ቀን

ትምህርት ሶስት፣ማንበብ (የግል ንባብ)

በዚህ ትምህርት የአካቶ መማር ምንባብ በግል እንዲያነቡ ከማድረግዎ በፊት የተማሪዎችዎን የቀደመ አውቀት በቅድመ ንባብ ጥያቄዎች ይፈትሹ፡፡ ምንባቡን ሰአት ወስነው በመስጠት አንበው ሲጨርሱ የድሕረ ንባብ ጥያቄዎችን በጽሑፍ እንዲመልሱ በመጠየቅ ግብረ መልስ ይስጡ፡፡

ሁለተኛ ሳምንት ፤አንደኛ ቀን

ትምህርት አራት፤ያልተሟላ አንቀጽን ማጠናቀቅ

በዚህ ተግባር ስር በጅምር የቀረ ያልተሟላ አንቀጽ አለ ፡፡ይህን አንቀጽ ያንብቡላቸውና ያልተሟላና የቀረው ክፍል አንዳለ ይንገሯቸው፡፡ አንድ አረፍተነገር ጨምረው ምሳሌ ይስጧቸው፡፡ በመቀጠል ተማሪዎቹ የራሳቸውን አረፍተ ነገር ጨምረው እንዲያሟሉ ያድርጓቸው፡፡ የሚቸገሩ ተማሪዎች ስለሚኖሩ እየተዘዋወሩ በመመልከት እገዛ ያድርጉላቸው፡፡

የመጓጓዣ ዓይነቶች

የመጓጓዣ መሳሪያዎች ሸቀጦችንና ምርቶችን ከአምራቹ ለተጠቀሚ የሚያጓጉዙና የሚያደርሱ መሳሪያዎች ናቸው፡፡ሰዎችም በአነዚህ መሳሪያዎች አማካይነት ከአንድ ስፍራ ወደ ሌላ ስፍራ ይጓጓዛሉ፡፡እነዚህ የመጓጓዣ አይነቶች እንደሚሰጡት አገልግለት ተግባር ይለያያሉ፡፡ አነሱም…

ሁለተኛ ሳምንት ፤ ሁለተኛ ቀን

ትምህርት አምስት፡- ቃል ምስረታ

በመጀመሪያ ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ምሳሌዎች ያስረዷቸው፡፡በመቀጠል በምሳሌው መሰረት ተማሪዎቹ መልመጃዎችን ይስሩ፡፡

| | ዋና ቃል /ግስ/ | ቃሉ/ ስም/ |
|---|---|---|
| 1 | ሄደ | መሄጃ |
| 2 | ጫነ | መጫኛ |
| 3 | ደረሰ | መድረሻ |

በቀረበው ምሳሌ መሰረት የሚከተሉትን ስሞች መገኛ /ግስ/ይጻፉና መልስ

ሲሰሩ ይከታተሏቸው

1. ማስታወሻ ________
2. ማጠበያ ________
3. መጻፊያ ________
4. መግረፊያ ________
5. መማሪያ __

ሁለተኛ ሳምንት፡ሶስተኛ ቀን

ትምህርት ሰድስት፡የቃል ክፍሎች (ስዋሰው)

የቃል ክፍሎች (ስምና ፣ተውላጠ ስሞች)

ምሳሌዎቹን ሰርተው የሳዩዋቸው፡፡

ሀ.መኪና መጓጓዣ ነው፡፡

- **መኪና** የቃል ክፍሉ ስም ነው፡፡
- **መጓጓዣ** የቃል ክፍሉ ስም ነው፡፡
- **ነው** የቃል ክፍሉ ግስ ነው፡፡

ለ. ተውላጠ ስሞች ጠቋሚዎች ናቸው፡፡

የሚከተለውን ምሳሌ ተመልከቱ፡፡

ምሳሌ፡ **እኔ** ተማሪ **ጠንከር** አባላለሁ፡፡ ወንድሜ **ዘርጋ** ይባላል ፡፡**እሱ** ወታደር ነው፡፡ አህቴ ደግሞ **ቆንጂት** ትባላለች፡፡ **እሷ** ባለትዳር ነች፡፡ **እኛ** ሁላችንም የኖርነው በመተጋጋዝ ነው፡፡

| አንደኛ መደብ | ሁለተኛ መደብ | ሶስተኛ መደብ |
|---|---|---|
| እኔ (ነጠላ ቁጥር)<br>እኛ (ብዙ ቁጥር) | አንተ (ነጠላ ቁጥር)<br>አንቺ (ነጠላ ቁጥር)<br>አናንተ(ብዙ ቁጥር) | እሱ(ነጠላ ቁጥር)<br>እሷ (ነጠላ ቁጥር)<br>እነሱ (ብዙ ቁጥር) |

ከላይ የተመለከቱትን ተወለጠ ስሞች  በመምረጥ ከእያንዳንዱ መደብ አንዳንድ ተውላጠ ስም በመጠቀም አረፍተ ነገሮች እንዲጽፉ ያድርጉ፡፡

እየተዟዟሩ ግብረ መልስና ድጋፍ ይስጡ፡፡

ሶስተኛ ሳምንት፡ አንደኛ ቀን

ትምህርት ሰባት :የቃል ክፍሎች ተውሳከ ግስና ግስ)

በዚህ ትምህርት ደግሞ ስለ ግስ ገላጮችና /ተውሳከ ግሶች/

በተማሪው መጽሐፍ ውስጥ ተውሳከ ግስን አጠቃቀም በአውድ ለማሳየት የተዘጋጀ ነው፡፡እርሶም ተጨማሪ ማብራሪያ ይስጧቸው፡፡

አውሮፕላን የአየር መጓጓዣ ነው፡፡በአየር መጓዝ **ክፉኛ** ያሚያስፈራቸው ሰዎች እንዳሉ ሲነገር እንሰማለን ፡፡ በመኪና መጓዝ ደግሞ በጣም የሚያስደስታቸው ሰዎች እንዳሉ ሁሉ፣ የሚያስፈራቸውም ሰዎች መኖራቸውን ስናስብ **ምንኛ** ይገረመን ይሆን፡፡ እናም እናንተስ በጣም የሚያስደስታችሁ ምን አይነት መጓጓዣ ነው፡፡

የሚከተሉትን ተውሳከ ግሶች ተጠቅመው የራሳችውን አረፍተ ነገሮች ይመስርቱ

1. ቶሎ
2. ገና
3. ክፉኛ
4. ምንኛ

ሶስተኛ ሳምንት፡ሁለተኛ ቀን

ትምህርት ስምንት፡ግስ /ማሰሪያ አንቀጽ

ስለ ግስ ያስረዷቸው በመቀጠል በምሳሌ መልክ የተቀመጠውን ጽሁፍ አስነብቧቸውና የከፍል ሰራ ይስጧቸው፡፡

ከላይ የተሰጣቸውን ጽሑፍና የቢጋር ሰንጠረዥ አይተዋል፡፡ እነሱም ከመሆን ግሶች ሁለቱን፣ ከድርጊት ግሶች ሁለቱን በመጠቀም የራሳችሁን አረፍተ ነገር እንዲጽፉ ያድርጉ፡፡

1. ______________________________
2. ______________________________
3. ______________________________
4. ______________________________

በመቀጠል የክፍል ስራ ያሰሯቸው፡፡ ድጋፍ ለሚፈልጉ ተማሪዎች እየተዟዟሩ ያግዟቸው፡፡

ሶስተኛ ሳምንት፡ሶስተኛ ቀን

ትምህርት ዘጠኝ፡ቃላትን በቃል ክፍሎች መመደብ

ቃላትን ለመመደብ ከሚያስችለን መስፈርት አንዱ አገባብ ሲሆን ሌላው ደግሞ ቅርጽ ነው፡፡ አረፍተ ነገር ስትመሰርቱ አስተውላችኋል፡፡

- ስሞች በአረፍተ ነገሮች ውስጥ በባለቤትና በተሳቢ ቦታ ይገኛሉ፡፡
- ተውለጠ ስሞች በአረፍተ ነገሮች ውሰጥ ጠቋሚ ሆነው ያገለግላሉ፡፡
- ተውሳከ ግሶች ከግስ ቀድመው በመገኘት ግሱን ይገልጻሉ፡፡
- ግሶች በአረፍተ ነገር መጨረሻ ይገባሉ፡፡

በመቀጠል በክፍል ውስጥ የሚሰራ ስራ ይስጡና ያርሙላቸውና ግብረመልስ ይስጧቸው፡፡

<u>ከዚህ በታች በተመለከቱት አረፈተ ነገሮች ውስጥ ያሉ ቃላትን በቃል ክፍላቸው መድቡ</u>

ሳንቴ ቀሚሷን ለብሳለች፡፡ጸሐይዋ ገና መውጣቷ ነው፡፡ እሷ ቶሎ መጣች፡፡

| ስም | ተውላጠ ስም | ተውሳከ ግስ | ግስ |
|---|---|---|---|
| | | | |
| | | | |

**የምእራፍ አራት የግምገማ መልሶች**

አንደኛ ሳምንት:ሶስተኛ ቀን

ትምህርት ሶስት:ማንበብ (የግል ንባብ)

የአካቶ ትምህርት

ቅድመ ንባብ ጥያቄዎች፡ ልጆች ግምታቸውን ሲሰጡ ማድነቅ ጥሩ ነው፡፡መልሱ በልጆቹ ግምት ላይ የተመሰረተ ስለሆነ ትክክለኛውን መልስ መለየት አይቻልም

ሀ. የአካል ጉዳት የሚደርሰው በምን ምክንያት ይመስላችኋል?

ለ. የአካል ጉዳት ከሌሎች ጋር አብሮ መማር ይከለክላል የሚል አስተሳሰብን ትደግፋላችሁ?

ሐ. 1/ድንጋጌ /ሕግ

2/ የስነ ልቦና ጫና /ጭንቀት

3/ ጾታ/ወንድ ወይም ሴት መሆን

4/ አለም አቀፍ/ሁሉንም ሀገሮች የያዘ ስብስብ

5/ ከሞላ ጎደል/ከብዙ በጥቂቱ

ድህረ ንባብ ጥያቄዎች

1/ ሀ. እውነት

ለ. ሐሰት

ሐ. ሐሰት

2/ መልሱ እንደ ልጆቹ ልምድና ሃሳብ ሊለያይ ይችላል፡፡

ሁለተኛ ሳምንት፡ ሁለተኛ ቀን

ትምህርት አምስት፡- ቃል ምስረታ

6. አስታወሰ ___ማስታወሻ___
7. አጠበ ___ማጠቢያ___

8. ጻፈ *መጻፊያ*
9. ገረፈ *መግረፊያ*
10. ተማረ *መማሪያ*

ሁለተኛ ሳምንት፡ሶስተኛ ቀን

ትምህርት ሰድስት፡የቃል ክፍሎች (ስዋስው)

1. እሷ
2. እኛ
3. ወንበር
4. ቶሎ
5. ሰበረች

ሶስተኛ ሳምንት፡ሁለተኛ ቀን

ትምህርት ስምንት፡ተውለጠ ስሞች

1. አንቺ
2. እኛ
3. እሱ
4. በሶስት መደቦች አንዳንድ ተውለጠ ስም ተጠቅመው ስምንት አረፍተ ነገሮች እንዲመስርቱ ይጠበቃል፡፡

ሶስተኛ ሳምንት፡ሶስተኛ ቀን

ትምህርት ዘጠኝ፡ ግሶች

መሆንና መገኘትን የሚሳዩ ግሶች ያሏቸው አራት አረፍተ ነገሮች እንዲመሰርቱ ይጠበቃል፡፡

# ምእራፍ አምስት

## የተሰደዱ ስሞች ክ/ጊዜ 9

1. ርዕስ ፡ የተሰደዱ ስሞች

2. የሚጠበቁ ውጤቶች

ተማሪዎች ይህን ትምህርት ከተማሩ በኋላ

- በተላላፊ በሽታዎች ጉዳይ ላይ አዳምጠው አስተያየት ይሰጣሉ፡፡
- የራሳቸውን የሕይወት ተሞክሮ ለአቻዎቻቸው ይናገራሉ፡፡
- በምንባቡ መሰረት አውዳዊ ፍች ይሰጣሉ፡፡
- የሕይወት ታሪካቸውን ይጽፋሉ፡፡
- ለአዳዲስ ቃላት ፍቺ ይሰጣሉ፡፡
- ቁጥር፣ ጾታና ጊዜ አመልካች ቅጥያዎችን ይለያሉ፡፡

3.ዝርዝር ይዘቶች

ሀ ማዳመጥ

ትምህርት አንድ ፡- ማዳመጥ

- ለማዳመጥ ዝግጁ የሚያደርጓቸውን የቅድመ ማዳመጥ ጥያቄዎችን ይሞክራሉ፡፡
- የሚቀርብላቸውን ምንባብ በትኩረት ያዳምጣሉ፡፡
- በዳመጡት ምንባብ መሠረት ልዩ ልዩ ጥያቄዎችን ይመልሳሉ፡፡

ትምህርት ሁለት፡- የንግግር ክሂል ማዳበር

- የሕይወት ተሞክሯቸውን መሰረት በማድረግ ይናገራሉ፡፡

ለ.ማንበብ

ትምህርት ሶስት፡-

- ለማንበብ ዝግጁ የሚደርጓቸውን ቅድመ ንብብ ጥያቄዎችን በቃል ይመልሳሉ፡፡

- የቀረበላቸውን ምንባብ አስተካክለው ያነባሉ፡፡
- ባነበቡት ምንባብ መሠረት የድህረ ንባብ ጥያቄዎችን ይመልሳሉ፡፡

ሐ. መጻፍ

ትምህርት አራት፡- የአንድን ሰው የሕይወት ታሪክ ይጽፋሉ

4. የትምህርቱ አቀራረብ

ትምህርት አንድ፤ማዳመጥ

መምህር/ት

ከዚህ በታች አበይት በሆኑ ጉዳዮች ዙሪያ ብቻ አጠቃለይ የአቀራረብ ብልሃቶች ቀርበዋል፡፡ ቢመለከቷቸው ትምህርቱን ከሞላ ጎደል በተሳካ ሁኔታ ለመምራት ያስችሉዎታል፡፡ ነገር ግን እነዚህ ብልሀቶች ብቸኛ ናቸው ብለው ራስዎን በእነሱ ብቻ እንዳያጥሩ፡፡ እንደሁኔታዎች ጋባዥነት ወይም እስገዳጅነት እየተመለከቱ፣ የራስዎን ፈጠራዎችንና የተሻሉ ዘዴዎችን በመጠቀም ተማሪዎቹን ሊያግዟቸው ይችላሉ፡፡

የምዕራፍ የመጀመሪያ ትምህርት በማዳመጥ ዙሪያ የሚያጠነጥን ነው፡፡ ለክሂሉ አተገባበር እንዲረዳ ተብሎ ከዚህ በታች አንድ ምንባብ ቀርቧል፡፡ ምንባቡም የተማሪዎችን የማዳመጥ ክሂል ግብ አድርጎ የተመረጠ ነው፡፡ መጀመሪያ ተማሪዎች ማዳመጥ እንዲጀምሩ በተለያየ መንገድ ያነቃቋቸው፡፡ በመቀጠል ለማዳመጥ ዝግጁ የሚያደርጓቸውን የቅድመ ማዳመጥ ጥያቄዎችን በመጠየቅ የቀደመ እውቀታቸውን ተጠቅመው የቁልፍ ቃላትን ፍች እንዲናገሩ ያድርጓቸው፡፡ ከዚያም ምንባቡን ያንብቡላቸው፡፡ ምናልባትም ምንባቡን ቶሎ ላይረዱት ስለሚችሉ ደግመው ያንብቡላቸው፡፡ ከዚያም ምንባቡን አስመልክቶ በተማሪዎች መጽሃፍ ላይ በቀረቡት ጥያቄዎች ዙሪያ ያወያዩዋቸው፡፡

ለ.ትምህርት ሁለት፡- መናገር

ትምህርት ሁለት የንግግር ክሂል የሚዳብርበት ይዘት ነው፡፡ አስቀድሞ ሲነበብ ያዳመጡትን (ተለላፊ ያልሆኑ በሽታዎች)መነሻ በማድረግ ባዳመጡት ጉዳይ ላይ ያስተዋሉትን በቡድን ሆነው እንዲወያዩበት ያድርጓቸው ፡፡ በዚህ ወቅት በየቡድኑ ያሉ ተማሪዎች ሁሉም እንዲሳተፉ ክትትል በማድረግ ያበረታቷቸው፡፡ ለውይይት የተሰጣቸው ጊዜ ሲያልቅ የአንዳንዱ ቡድን በተወካዩ

አማካይነት በክፍል ጓደኞቻቸው ፊት እየተነሱ የንግግር ክሂል ልምምድ እንዲያደርጉ ይርዷቸው፡፡

ሐ.ትምህርት ሶስት፡- ማንበብ

መምህር/ት

ተማሪዎች በመማሪያ መጻህፋቸው ላይ ተላላፊ ያልሆኑ በሽተዎች ላይ የተጻፈውን ምንባብ ከማንበባቸው በፊት ቅድመ ንባብ ጥያቄዎችን እንዲመልሱ ያበረታቷቸው፡፡ በመቀጠል ምንብቡን በግል እንዲያነቡ ያድርጓቸው፡፡ ከዚያም ማንበባቸውን ገታ አድርገው የንባብ ጊዜ ጥያቄዎችን እንዲመልሱ ይጠይቋቸው፡፡ ለቀረቡላቸው ጥያቄዎች ምላሽ ከሰጡ በኋላ ቀሪውን የንባብ ክፍል እንዲያጠናቅቁ ይንገሯቸው ፡፡ ማንበቡን ሲያጠናቅቁ ከምንባብ የወጡ ጥያቄዎችን ያሰሯቸው፡፡ የዚህ ምንባብ ትኩረት አውዳዊ ፍችን ለማግኘት ስለሆነ ጥያቄዎቹ በዚህ ላይ ያተኮሩ ይሆናሉ፡፡

መ. መጻፍ

ትምህርት አራት ፡- የሕይወት ታሪክ መጻፍ

ተማሪዎች የሕይወት ታሪክ አጻጻፍ መመሪያን አንብበው የአንድ ሰው የሕይወት ታሪክ ይጽፋሉ፡፡ የጻፉትን የሕይወት ታሪክ ለቡድናቸው እንዲያነቡ ያደርጋሉ፡፡የተጻፈውን የሕይወት ታሪክ ሰብስበው ያርሙና ግብረ መልስ ይሰጣሉ፡፡

ትምህርት አምስት፡- የቃላት ፍች

ተማሪዎች ከሌሎች ቃላት አዳዲስ ቃላትን ፍች የመረዳት ዘዴዎችን እንዲረዱ በምሳሌ አስደግፈው ያሳዩዋቸው ፡፡ አዳዲስ ቃላት ከተለመዱና ከሚዘወተሩ ቃላት ወጣ ያሉ መሆናቸውን ይገንዘቡ፡፡ ተማሪዎችም ሁለተኛ ቋንቋ ተናጋሪ እንደመሆናቸው መጠን ለእነሱ አዳዲስ ቃላት ለአፍ መፍቻ ተናጋሪው የተለመደ ሊሆን ይችላል፡፡

ትምህርት ስድስት፤ የሰዋሰው ሕጎች

- ቁጥር፤ጾታና ጊዜ

የቁጥር፣ የጾታና የጊዜን አመልካች ቅጥያዎች ባህሪን ያስረዱ፡፡ ለዚህ ተግባር አስፈላጊ የሆኑ ቅጥያ ምእላዶችን ተማሪዎቹ በሚያውቋቸው የተለመዱ ቃላት ላይ በመጨመር ምሳሌዎች ሰርተው ያሳዩዋቸው፡፡ በመቀጠል ተማሪዎቹ

በቡድን ሆነው ልምምድ ያድርጉ፡፡ በልምምዳቸው ጊዜ የተጠቀሙባቸውን ለክፍሉ ያጋሩ፡፡

5. መርጃ መሳሪያዎች ፡-
የሕይወት ታሪክ አጻጻፍ መመሪያዎችና ናሙና ጽሑፎች፣ቃላትን ከነቅጥያዎቻቸው የሚሳይ የቢጋር ስንጠረዥ፣ፍላሽ ካርዶች

6. ግምገማ ፡-

- የማዳመጥ ጥያቄዎችን በትክክል መመለሳቸውን ማረጋገጥ
- በተሠጣቸው ርእስ ላይ በንቃት መወያየታቸውንና ተሳትፎ ማድረጋቸውን መከታተልና ግብረ መልስ መስጠት፡፡
- ስላነበቡት ነገር የተረዱትን በመጠየቅ መረዳታቸውን ማረጋገጥ
- የቃላትን አውዳዊ ፍች ለይተው መረዳታቸውን ማረጋገጥ፡፡
- የሕወይት ታሪክ አጻጻፍ ስርዓትን ተከትለው መጻፋቸውንና ማረማቸውን መከታተል፡፡

6. በናሙናነት ለተመረጡ ጥያቄዎች መልስ

የምእራፉን መልሶች በምእራፉ መጨረሻ ላይ ያገኟቸዋል፡፡

አንደኛ ሳምንት፡-አንደኛ ቀን

ትምህርት አንድ፡-ማዳመጥ

ቅድመ ማዳመጥ ጥያቄዎች

1. በሽታዎች በምን መንገድ ከሰው ወደ ሰው ይተላለፋሉ?
2. ተላላፊ ከሆኑ በሽታዎች የምታውቁትን ጥቀሱ፡፡
3. ተላላፊ ያልሆኑ በሽታዎች እንዳሉ ሰምታችሁ ተውቃላችሁ? ሰምታችሁ ከሆነ አስኪ ንገሩን፡፡

**ይህን ምንባብ ሰያነቡ በምልልሳዊ /ትወናዊ የንባብ ስልት/ ያንቡላቸው፡፡**

## ተላላፊ ያልሆኑ በሽታዎች

መምህር =በአለማችን ለሰው ልጆች በሞት መለየት ምክንያት የሚሆኑ ነገሮች ብዙ ቢሆኑም ከነዚህ ውስጥ ተላላፊ በሆኑ በሽታዎች ምክንያት የሚሞተው ሰው መጠን ግን በጣም የበዛ ነው፡፡ ለዚህ ጥሩ ምሳሌ ማድረግ የምንችለው በቅርቡ የተከሰተው የኮሮና በሽታን ነው ፡፡

ተማሪ = ሰዎች የሚሞቱት በተላላፊ በሽዎች ብቻ ነው እንዴ?

መምህር = አይደለም ፡፡ በተፈጥሮና በሰው ሰራሽ አደጋ፣በአርጅናና ተላላፊ ባልሆኑ በሽተዎችም ምክንያት ሊሆን ይችላል፡፡

ተማሪ = ተላላፊ ያልሆኑ በሽዎች ደግሞ ምንድናቸው?

መምህር= አዎን ዛሬ ልነግራቸህ የተዘጋጀሁበት ርእስ ስለእነሱ የሚጠቅስ ነበር፡፡ ተላላፊ ያልሆኑ በሽታዎች የተባሉበት ምክንያት ሰዎችን የሚያጠቁና ለስቃይና ለሞት የሚዳርጉ ሆነው ግን ከሰው ወደ ሰው የማይዛመቱ በመሆናቸው ነው፡፡

ተማሪ = ለመሆኑ እነዚህ በሽታዎች ምን ምን በመባል ይታወቃሉ?

መምህር= የደም ግፊት፣ የስኳር ህመም ፣ የኩላሊት ህምም፣ደም ማነስና ሌሎችም ያልጠቀስኳቸው ናቸው፡፡

ተማሪ = በሽታዎቹ በምን ምክንያት ሊከሰቱ ይችላሉ?

መምህር= የሰዎች የአኗኗር ጠባይ መለወጥና የአመጋገብ ሰርአት ምክንያት ነው፡፡

ተማሪ = የአኗኗር ጠባይና የአመጋገብ ስርአት ሲባል ምን ማለት ነው?

መምህር= በእርግጥ የበሽታዎቹ መነሻ ምክንያት ሙሉ በሙሉ

ባይረጋገጥም የአኗኗር ጠባይ የምንለው፤እረፍት

የለሽ የአእምሮ ጭንቀት፣የሰውነት እንቅስቃሴ

ጉድለት፣መጠኑ የበዛ ጨውና ስብ እንዲሁም

አልኮል መጠቀም ሊጠቀሱ

ይችላሉ።

ተማሪ = እነዚህ በሽታዎች የሚያጠቁት ምን ዓይነት ሰዎችን

ነው?

መምህር= እድሜያቸው 18 ና ከዚያ በላይ የሆኑ ሰዎችን ነው?

ተማሪ = በሽታዎቹ የሚሳዩት ምልክቶች ምን ምን ናቸው?

መምህር= የበሽታው ምልክቶች ከታማሚው ሰው በስተቀር

ለሌሎች ሰዎች በግልጽ ላይታይ ይችላል ። ይሁን

እንጂ በሽታው እየተባበሰ ሲሄድ በታማሚው ላይ

የሚታዩ ለውጦች ይኖራሉ።

ተማሪ = አነዚህን በሽዎች ለመከላከል የሚቻለው በመድሐኒት

ነው?

መምህር= አዎ በመድሐኒት ነው። ነገር ግን በሽታዎቹ

ከመከሰታቸው በፊት መከላከል የሚቻልበት መንገድ አለ።

ተማሪ = በምንድነው ቀድሞ መከላከል የሚቻለው?

መምህር= የአመጋገብ ሰርዓትን በማስካከል፣የምግብ ጨውን

ቀንሶና መጥኖ በመጠቀም ፣የአካል ብቃት

እንቅስቃሴ በማድረግ፤በቂ የእንቅልፍ ጊዜ

በመጠቀም መከላከል ይቻላል።

ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን የድህረ ንባብ ጥያቄዎች በቃል እንዲመልሱ ይጠይቋቸው፡፡

ድህረ ንባብ ጥያቄዎች

1. ያዳመጣችሁት ርእስ በምን ጉዳይ ላይ ያተኮረ ነው?
2. ተላላፊ የሆኑ በሽታዎች እንዳሉ ታወቁ ነበር፡፡ ካዳመጣችሁት ሌላ የሰማችሁት ካለ ንገሩን፡፡
3. ከዚህ በፊት ጨው አብዝቶ መጠቀም ለበሽታ እንደሚዳርግ ሰምታችሁ ነበር?
4. ውፍረት ውበት ተደርጎ መቆጠሩ ልክ ነው ትላላችሁ?

ምንጭ፤ የማይተላለፉ በሽታዎች የሀገሮች ገጽታ 2018፡፡ የአለም አቀፍ ጤና ድርጅት፡፡ በምልልስ መልክ ለማስተማር እንዲስማማ ተደርጎ የተዘጋጀ ትርጉም NON COMMUNICABLE DISEASES COUNTRY PROFILES 2018 World Health Organization

አንደኛ ሳምንት፤ ሁለተኛ ቀን

ትምህርት ሁለት፤መናገር

ተማሪዎች የሕይወት ተሞክሯቸውን ለመግለጽ እንዲያስችላቸው የሚከተሉትን ሂደቶች አንዲያነቡና በዚህ መልክ መልስ እየሰጡ በቅደም ተከተል ለጓደኞቻቸው እንዲናገሩ ያበረታቷቸው፡፡

- ስማችሁን አስተዋውቁ፣
- መኖሪያ አካባቢያችሁን ግለጹ፣
- ቤተሰባችሁን አስተዋውቁ፣
- የት እንደምትማሩ ግለጹ፣
- ምን አይነት ጨዋታ እንደምትወዱ አስረዱ፣
- በትርፍ ጊዜያችሁ ምን እንደምትሰሩ አብራሩ፣
- ከሰፈራችሁ ልጆች ጋር ምን ዓይነት በጎ ተግባር እንደምትፈጽሙ አስረዱ፡፡

አንደኛ ሳምንት፤ ሶስተኛ ቀን

ትምህርት ሶስት፡- ማንበብ /አውዳዊ ፍቺ ለማግኘት/

የተሰደዱ ስሞች በሚል የተዘጋጀውን ምንባብ በግላቸው በፍጥነት አንብበው የቃላትን አውዳዊ ፍች እንዲሰጡ አርስዎ አንድ ምሳሌ ሰርተው ያሳያዋቸው፡፡በመቀጠል በተሰጣቸው ምሳሌ መሰረት እንዲሰሩ ያድርጓቸው፡፡

ሁለተኛ ሳምንት፤አንደኛ ቀን

ትምህርት አራት፡- የሕይወት ታሪከ መጻፍ

የሕይወት ታሪክ ለመጻፍ የሚያስችላቸውን የአጻጻፍ ስልት ያስረዷቸው፡፡ በግል ታሪክና በሌላ ሰው የሕይወት ታሪክ አጻጻፍ መካከል ያለውን ልዩነት ግለጹላቸው፡፡

ባዮግራፊ/ ሲጻፍ የሚከተሉትን ፍሬ ሃሳቦችን ማካተት ያስፈልጋል፡፡

1. የሚጻፍለትን ሰው ታሪክ ፈቃድ ማግኘት፣
2. በቂ ጥናት ማድረግ፣
3. ስለሚጻፍላቸው ሰዎች ማስተማር የሚያስችል እንዳለ መለየት፣
4. ስለሚጻፍለት ሰው የቀድሞ ታሪክን አሁን ካለው ጋር በማያያዝ ማስታወስ፣
5. ለመጻፍ መነሻ የሆነውን አነሳሽ ምክንያት መዘርዘር

ሁለተኛ ሳምንት፤ ሁለተኛ ቀን

ትምህርት አምስት፡- የቃላት ፍች

መልመጃ ለሚከተሉት ቃላት ፍች ስጡ

በትምህርትአራት ላይ የተጠቀሰውን የሕይወት ታሪክ መልሰው እንዲያስታውሱ በማድረግ ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ቃላት በአውዱ መሰረትና ከአውዱ ውጭ ያላቸውን ፍቺ ስጡ፡፡

መልመጃ

ለሚከተሉት ቃላት ፍች ስጡ

| | |
|---|---|
| 1. የተመረቁት | 6. የቀዶ ጥገና |
| 2. ኮንትራት | 7. በማበርከት |

3. ተጠቂዎች

4. ፈተና

5. እውቅና

8. አስተዋጽኦ

9. የሚወደሱት

10. ተመስጣ

ሁለተኛ ሳምንት፤ሶስተኛ ቀን

ትምህርት ስድስት፡- የስዋስው ሕጎች /ቁጥር፣ጾታ፣ጊዜ/

የስም አርባታ /ቁጥር፣ጾታ፣ሙያ/

ስሞች ቁጥር፣ጾታና ሙያ ለሚባሉ ስዋስዋዊ ባህሪያት ቅርጻቸውን ይለዋውጣሉ፡፡ቅርጻቸውን የሚለዋውጡት ቅጥያዎችን በመጨመር ሊሆን ይችላል፡፡

ቁጥር መጠንን ወይም ስንትነትን የሚገልጽ ስዋስዋዊ ባህሪ ነው፡፡የሚቆጠሩና የማይቆጠሩ ስሞች አሉ፡፡አንድ ብቻ የሆነ ነገር ነጠላ፣ከአንድ በላይ የሆነ ነገር ግን ብዙ ቁጥር ይባላል፡፡

ምሳሌ

| ተ.ቁ | ስሞቹ | ብዙ ቁጥር |
|---|---|---|
| 1 | ቤት | ቤቶች |
| 2 | ተማሪ | ተማሪዎች |
| 3 | ሰራተኛ | ሰራተኞች |
| 4 | ወንድ | ወንዶች |
| 5 | ሴት | ሴቶች |

ሶስተኛ ሳምንት ፤አንደኛ ቀን

ትምህርት ሰባት፡- ጾታ

ጾታ ተፈጥሯዊና ሰዋሰዋው ተብሎ ለሁለት ሊከፈል ይችላል፡፡ ወንድ/ተባእታይ/ ሴት/አንስታይ/ ተብለው ይሰየማሉ፡፡ የአንስታይ ጾታ ምልክት ከሌላቸው ጾታቸው አይታወቅም ፡፡

ምሳሌ

ጾታ አመልካች ያላቸው

1. ልጅ ________________ ልጂት
2. ድመት________________ ድመቲት
3. ሙሽራ________________ ሙሽሪት

ምንም አይነት የጾታ አመልካች የሌላቸው

1. አባት________________እናት
2. አጎት________________አክስት
3. በሬ ________________ላም

ሶስተኛ ሳምንት፤ ሁለተኛ ቀን

ትምህርት ስምንት ፣ የስም ሙያ

ስሞች በአረፍተ ነገር ውስጥ የሚፈጽሙት ተግባር ሙያ ይባላል፡፡ሙያቸው የባለቤትነት፣የተሳቢነት ነው፡፡የባለቤትነት ሙያ ያላቸው የመጀመሪያውን ቦታ የተሳቢነት ሙያ ያላቸው ደግሞ ከማሰሪያ አንቀጹ /ግሱ/ቀደሞ ይገባል፡፡

ምሳሌ

| | ስም | ባለቤት | ተሳቢ |
|---|---|---|---|
| 1. | ልጅ | ልጅ | ልጅን |
| 2. | እናት | እናት | እናትን |

- **ልጅ** አባቱን ይወዳል፡፡
- አባት **ልጁን** ይንከባከባል፡፡

ሶስተኛ ሳምንት፤ሶስተኛ ቀን

ትምህርት ዘጠኝ ፡- ጊዜ

- ጊዜ የምንለው ድርጊቱ የተፈጸመበትን ወይም የሚፈጸምበትን ወቀት ነው፡፡ ተፈጽሞ ያበቃን ሀላፊ ጊዜ፣እየተፈጸመ ያለ ከሆነ ያሁን ጊዜ ያልተፈጸመ ከሆነ የትንቢት/የወደፊት/ ገዜ በሚል ይከፈላል፡፡
  ምሳሌ

| | ግሱ | ጊዜ |
|---|---|---|

| | | አሁን | ሀላፊ | ትንቢት |
|---|---|---|---|---|
| 1 | መጣ | መጣ | መጥቷል | ይመጣል |
| 2 | መጣች | መጣች | መጥታለች | ትመጣለች |

አራተኛ ሳምንት ፤አንደኛ ቀን

ትምህርት አስር፤ የቃል ክፍሎች (ማጠቃለያ)

ባለፉት ሁለት ሳምንታት የቃል ክፍሎችን በዝርዝር ተምራችኋል፡፡ በዚህ ቀን

አራቱንም የቃል ክፍሎች በማጠቃለል ሁሉንም የቃል ክፍሎች –ያካተቱ አረፍተ ነገሮች በመጻፍ የጻፋችሁትን ለአቻዎቻችሁ በማንበብ አጋሩ፡፡

የምእራፉ የግምገማ መልሶች

አንደኛ ሳምንት ፤ አንደኛ ቀን

ትምህርት አንድ ፡- ማዳመጥ

ቅድመ ማዳመጥ ጥያቄዎች

በተማሪዎች የሚመለሱ የግምት መልሶች ስለሆኑ መልሳቸውን መቀበል በቂ ነው፡፡

1. በሽታዎች በምን መንገድ ከሰዎች ወደ ሰዎች ይተላለፋሉ?
2. ተላላፊ ከሆኑ በሽታዎች የምታውቁትን ጥቀሱ፡፡
3. ተላላፊ ያልሆኑ በሽታዎች እንዳሉ ሰምታችሁ ታውቃላችሁ? ሰምታችሁ

   ከሆነ እስኪ ንገሩን፡፡

ድህረ ማዳመጥ ጥያቄዎች

ሀ. ተላላፊ ያልሆኑ በሽታዎች መንስኤ ምንድነው

ጨው፣ክበደት መጨመር

ለ. ተላላፊ ያልሆኑ በሽታዎች የሚባሉት ምን ምን ናቸው?

ስኳር፣የደም ግፊት፣የኩላሊት በሽታ

ሐ. የአመጋገብ ጠባይ ተብሎ የተጠቀሰው ምንድን ነው?

ቅባትነት ያላቸውን ምግቦች ማዘውተር፣ጨው

ትምህርት ሁለት፤መናገር

የሕይወት ተሞክሮን መናገር

የሕይወት ተሞክሮን ለመግለጽ የሚከተሉትን ሂደቶች መከተላቸውንና በዚህ መልክ በቅደም ተከተል ለጓደኞቻቸው መነጋገራቸውን በምልከታ ያረጋግጡ፡፡

ተማሪዎች በመመሪያው መሰረት ፡-

- ስማቸውን ያስተዋውቁ፣
- መኖሪያ አካባቢያቸውን ይግለጹ፣
- ቤተሰባቸውን ያስተዋውቁ፣
- የት አንደሚማሩ ይግለጹ፣
- ምን አይነት ጨዋታ መጫወት እንደሚወዱ ይናገሩ፣
- በትርፍ ጊዜያቸው ምን እንደሚሰሩ ይናገሩ፣
- ከሰፈራቸው ልጆች ጋር ምን ዓይነት በጎ ተግባር አንደሚሰሩ ያሳውቁ፡፡

አንደኛ ሳምንት፤ ሶስተኛ ቀን

ትምህርት ሶስት፡- ማንበብ /አውዳዊ ፍቺ ለማግኘት/

ለሚከተሉት ቃላት አውዳዊ ፍች ሰጡ፡፡

1. **ተጽዕኖ =ጫና**
2. **እየተዘወተሩ= እየተለመዱ**
3. **ቅኝ አገዛዝ = የባእድ ተጽእኖ**
4. **የዘመናዊነት =ከጊዘው ጋር የሚለወጥ**
5. **ጥቅም = አገልግሎት**
6. **ፍልስፍና = የአስተሳሰብ ውጤት**
7. **ቅርሶች = ለትውልድ የሚተላለፍ ቋሚ ማስታወሻ**
8. **ክስተት = ሁኔታ**

ሁለተኛ ሳምንት፤አንደኛ ቀን

ትምህርት አራት፡- የሕይወት ታሪክ መጻፍ

የቤት ስራ

በተማሪ መጽሐፍ በትምህርት አራት  የተጠቀሰው የታዋቂ ሰው የሕይወት ታሪክ እንደ አንድ ምሳሌ የሚወሰድ ነው፡፡ ተማሪዎችዎ የአንድ ሰው የሕይወት ታሪክ እንዲጽፉ የተጻፈውን ታሪክ ያንቡላቸው፡፡ መመሪያውን አሰረዷቸውና እሱን መሰረት አድርገው ጽፈው ያምጡና ያርሙላቸው፡፡

ባዮግራፊ/ ሲጻፍ የሚከተሉትን ፍሬ ሃሳቦችን ማካተት ማረጋገጥ ያስፈልጋል፡፡

1. የሚጻፍለትን ሰው ታሪክ ፈቃድ ማግኘት፣

2. በቂ ጥናት ማድረግ፣

3. የሚጻፍላቸውን ሰዎች ማስተማር የሚያስችል ልምድ እንዳላቸው መለየት፣

4. ስለሚጻፍለት ሰው የቀድሞ ታሪክን አሁን ካለው ጋር በማያያዝ ማስታወስ፣

5. ለመጻፍ መነሻ የሆነውን ምክንያት መዘርዘር

ትምህርት አምስት፡- የቃላት ፍች

በትምህርትአራት ላይ የተጠቀሰውን የሕይወት ታሪክ መልሰው እንዲያስታውሱ በማድረግ ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ቃላት በአውዱ መሰረትና ከአውዱ ውጭ ያላቸውን ፍቺ ይስጡ፡፡

| | | | |
|---|---|---|---|
| 1. ተመረቁ | ያጠናቀቁት፣የተባረኩት | 6. ቀዶ ጥገና | ሰውነት ከፍቶ ማከም |
| 2. ኮንትራት | በጊዜ የተገደበ ውል ፣ | 7. ማበርከት | መስጠት |
| 3. ተጠቂዎች | ተጎጂዎች | 8. አስተዋጽኦ | ድርሻ |
| 4. ፈተና | ተግዳሮት | 9. መወደስ | መመስገን |
| 5. እውቅና | ክብር | 10. ተመስጣ | ተስባ |

ትምህርት ስድስት፡- የስዋስው ሕጎች /ቁጥር፣ጾታ፣ጊዜ/

መልመጃ

ሀ. የሚከተሉትን ነጠላ ስሞች ወደ ብዙ ቁጥር ለውጡ

1.በሬ = በሬዎች

2.ልጅ = ልጆች

3.ገበሬ = ገበሬዎች

4.እናት = እናቶች

ለ . የሚከተሉትን የበዙ ቁጥር ስሞችን ወደ ነጣላ ቁጥር ለውጡ

1. ሰዎች = ሰው
2. ከተሞች = ከተማ
3. መንገዶች = መንገድ
4. አስተማሪዎች = አስተማሪ

ትምህርት ሰባት፡- ጾታ

ጾታ ተፈጥሯዊና ስዋሷዊ ተብሎ ለሁለት ሊከፈል ይችላል፡፡ ወንድ/ተባእታይ/ ሴት/አንስታይ/ ተብለው ይሰየማሉ፡፡ የአንስታይ ጾታ ምልክት ከሌላቸው ጾታቸው አይታወቅም ፡፡

ጾታ

1. ወንድም = አህት
2. ወፍ = ወፊት
3. ወይፈን = ጊደር
4. ፍየል = ፍየሊት

ሶስተኛ ሳምንት፤ ሁለተኛ ቀን

ትምህርት ስምንት ፣ የስም ሙያ

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምሳሌው መሰረት የባለቤትና የተሳቢ ሙያን በመለየት አረፍተ ነገር ሰርተው የሳዩዎት፡፡

1. ፈረስ ፈረስ ጋሪ ይስባል፡፡ /አረፍተ ነገሩ ሊለያይ ተሳቢዎች ግን በቦታቸው መገኘታቸውን ያረጋግጡ፡፡
2. ተማሪ
3. ወላጅ

ትምህርት ዘጠኝ ፤ ጊዜ

በተሰጠው ምሳሌ መሰረት የአሁን፣የሃላፊና የትንቢት ጊዜን በመለየት አሳዩ፡፡

1. አጠበ አጠበ አጥቧል ያጥባል
2. ጻፈች ጻፈች ጽፋለች ትጽፋለች
3. አነበበ አነበበ አነበበች ታነባለች
4. ሰራች ሰራች ሰርታለች ትሰራለች

| | ግሱ | ጊዜ | | |
|---|---|---|---|---|
| | | አሁን | ሀላፊ | ትንቢት |
| 1 | በላች | በላች | በልታለች | ትበላለች |
| 2 | ከበደ | ከበደ | ከበዷል | ይከብዳል |
| 3 | ሰራህ | ሰራህ | ሰርቷል | ይሰራል |
| 4 | ስራች | ሰራች | ሰርታለች | ትሰራለች |

# <u>ምዕራፍ ስድስት</u>

## ወዳጅ ሲከዳ

የተመደበው ክፍለ ጊዜ፡-10 ክ/ጊዜ

1. ርዕስ፡ ወዳጃችን ሲከዳን
2. የሚጠበቁ ውጤቶች ፡-

ተማሪዎች ከዚህ ትምህርት በኂላ ፡-

- አርአያ የሆነ ሰው የህይወት ታሪክ አዳምጠው በቅደም ተከተል መልሰው ይተርካሉ ።
- መፍትሄ በሚሹ ማህበራዊ ጉዳዮች ዙርያ ችግር ፈቺ የሆነ ንግግር ያደርጋሉ።
- አጭር ልብወለድ አንብበው ጥያቄዎችን ይመልሳሉ ።
- ድርሰት ይፅፋሉ።
- ስሞች ላይ ቅጥያ ምዕላዶችን በመጨመር ቅፅሎችን ይመሰርታሉ ።
- አዎንታዊና አሉታዊ አረፍተ ነገሮችን ይመሰርታሉ።

አንደኛ ሳምንት፡ አንደኛ ቀን

ትምህርት አንድ ፡- ማዳመጥ

- የቅድመ ማዳመጥ ጥያቄዎችን ይመልሳሉ።
- የሚቀርብላቸውን ምንባብ በትኩረት ያዳምጣሉ ።
- የማዳመጥ ጊዜ ጥያቄዎችን ይመልሳሉ።
- ባዳመጡት ምንባብ መሠረትነት ልዩ ልዩ ጥያቄዎችን ይመልሳሉ ።

## አንደኛ ሳምንት - ሁለተኛ ቀን

## ትምህርት ሁለት ፡- መናገር

- በመጀመሪያ መፅሀፋቸው ላይ የቀረበውን ምንባብ ሲነበብ አዳምጠው በቡድን ከተወያዩ በኋላ ንግግር ያደርጋሉ፡፡
- ለሚቀጥለው ክፍለ ጊዜ አጭር ልቦለድ አንብበው ይመጣሉ ፡፡

## አንደኛ ሳምንት - ሶስተኛ ቀን

## ትምህርት ሶስት ፡- ማንበብ

- ባለፈው ክፍለ ጊዜ በተነገራቸው መሠረት አንድ አጭር ልብወለድ አንብበው እንደሚመጡ ይታመናል ፡፡ በዚህ ክፍለ ጊዜ ደግሞ ባነበቡት አጭር ልብወለድ ዙሪያ ለቀረቡት ጥያቄዎች በፅሁፍ ምላሽ ይሰጣሉ ፡፡

ሁለተኛ ሳምንት፡- አንደኛ ቀን

ትምህርት አራት፡- ድርሰት መፃፍ

<u>አጫጭር የድርሰት አይነቶች</u>

አበይት የድርሰት አይነቶችን ከመማሪያ መፅሀፋቸው ላይ ይረዳሉ፡፡

<u>ተራኪ ድርሰት</u>

ሁለተኛ ሳምንት - ሁለተኛ ቀን

ትምህርት አምስት፡ መፃፍ

ለናሙናነት የቀረበውን ተራኪ ድርሰትና የታሪክ መግለጫ በማጤን የራሳቸውን ተራኪ ድርሰት ይፅፋሉ ፡፡

ሁለተኛ ሳምንት፡- ሶስተኛ ቀን

ባለፈው ክፍለ ጊዜ ፅፈው እንዲመጡ በታዘዙት ተራኪ ድርሰት ላይ በተሰጣቸው አስተያየት ዙሪያ ይወያያሉ፡፡

ሶስተኛ ሳምንት፡ አንደኛ ቀን

ትምህረት ሰባት፡- ቅጥያ ምዕላዶችን በመጠቀም ከስም ቅፅልን ይመስርታሉ፡፡

ምሳሌዎች

<u>ስም</u>

ኃይል - ሀይለኛ

ተራራ - ተራራማ

ወገን - ወገናዊ

ሀብት - ሀብታም

1. ጉልበት ____________
2. ቂም ____________
3. አሸዋ ____________
4. ድንጋይ ____________
5. ዘመን ____________
6. ሀገር ____________
7. ጥርስ ____________
8. ወረት ____________
9. ሆድ ____________
10. ጥፍር ____________

ሶስተኛ ሳምንት፡- ሁለተኛ ቀን

ትምህርት ስምንት፡- ሰዋሰው

<u>አውንታዊ አሉታዊ ዓ.ነገሮች</u>

- ስለ አወንታዊና አሉታዊ ዓ.ነገሮች የቀረበውን ማብራሪያ አንብበው ይገነዘባሉ፡፡
- የቀረቡላቸውን ዓ.ነገሮች አውንታዊና አሉታዊ በማለት ይለያሉ ፡፡

ሶስተኛ ሳምንት - ሶስተኛ ቀን

ትምህርት ዘጠኝ

በመማሪያ መፅሀፋቸው ላይ በቀረቡት አስር ቃላት አውንታዊና አሉታዊ አርተ ነገሮችን ይመሰርታሉ፡፡

<u>የምዕራፉ ማበልፀጊያ ጥያቄዎች</u>

1. የህይወት ታሪክ ሲፃፍ ምን ምን ነጥቦች ይካተቱበታል ?
2. የድርሰት ዓይነቶችን ዘርዝሩ ፡፡
3. ከልቦለድ አላባውያን መካከል ሶስቱን ጥቀሱ ፡፡
4. በሚከተሉት ስሞች ላይ ቅጥያ ምዕላዶችን በመጨመር ቅፅሎችን መስርቱ፡፡

ሀ. ሀገር ሀገራዊ

ለ. ጥፍር ጥፍራም

ሐ .ድንጋይ ድንጋያማ

4 የትምህርቱ አቀራረብ ፡-

አንደኛ ሳምንት፡ አንደኛ ቀን

ትምህርት አንድ፡ ማዳመጥ

መምህር/ት

የምዕራፉ የመጀመሪያ ትምህርት ማዳመጥ ነው ። ለዚህም አተገባበር ይረዳ ዘንድ ከዚህ በታች መንባብ ቀርቧል ። ምንባቡብ ለተማሪዎች ለማንበብዎ በፊት በትኩረት ለማዳመጥ እንዲዘጋጁ የቀረቡላቸውን የቅድመ ማዳመጥ ጥያቄዎች በመጠየቅ ምላሽ በመስጠት እንዲሳተፉ ያግዟቸው፡፡በመቀጠል ምንባቡን ተማሪዎቹ ማዳመጥ በሚችሉበት እርጋታና የድምጽ ከፍታ ያንብቡላቸው ። አንብበው ሲጨርሱ ምንባቡን አስመልክቶ በተማሪዎች መፅሐፍ ላይ የቀረቡትን ጥያቄዎች በመጠየቅ ምላሽ እንዲሰጡ ያበረታቷቸው

<u>የህይወት ታሪክ</u>

<u>አክሊሉ ለማ</u>

( 1928-1989 )

አክሊሉ በምስራቅ ኢትዮጵያ ጂጂጋ በምትባል ተማ ተወለደ ከዚያም ዩኒቨርሲቲ ገብቶ በ1955 በሳይንስ ትምህርት የመጀመሪያ ድግሪውን አገኘ፡፡ በመቀጠልም ወደ አሜሪካ ሄደ ። በ1965 ከጆን ሆፕኪንስ ዩንቨርሲቲ ዶክትሬት ማዕረግ አገኘ ።ከዚያ እንደተመለሰም በአድስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ( በዚያን ጊዜ የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ዩኒቨርሲቲ ) ተመድቦ በትምህርት ሲያለግል ቆየ፡፡

እንደሚታወቀው በሀገራችን በቀንድ አውጣ አማካይነት የሚተላለፍ አደገኛ በሽታ አለ፡፡ ቢልሃርዝያ ይባላል፡፡ የበሽታው መንስኤ የሆኑት ሺስቶስሚያሲስ በመባል የሚታወቁ ረቂቅ ተዛዋስያን የሚኖሩት በተለይ ረግረጋማ በሆኑ ሥፍራዎች ነው፡፡ በዚያ የሰው አካል ሲያገኙም ቆዳን ሰርስረው ይገባሉ፡፡ ሰውነት ውስጥ በመራባትም ቢሊሃርዝያ የተባለው በሽታ ያስከትላሉ፡፡

በዚህ አደገኛ በሽታ ብዙ የአገራችንንና የተለያዩ ሀገሮች ስዎች ይሰቃያሉ ። የዚህ በሽታ መንስኤ የሆኑትን ተህዋስያን በመግደል በሽታው እንዳይራባ የሚያስችለውን መከላከያ ለመጀመሪያ ጊዜ ያገኘው አክሊሉ ለማ ነው ።

አክሊሉ አንድ ጊዜ ወደ ሰሜን ኢትዮጵያ ሄዶ ነበር፡፡ በዚያ ለስራ ሲዘዋወር ከቆየ በኃላ አንድ ቀን ከወንዝ ዳር ልብስ የሚያጥቡ ሰዎች አጋጠሙት ልብሳቸውን የሚያጥቡት በሳሙና ሳይሆን አንዶድ ተባለ ተክል በድንጋይ እየጨቀጨቁ፣ አረፋ ሲዎጣው በዚያ ነበር የሚያጥቡት፡፡ ተመራማሪውን ያስደነቀው ይህ አልነበረም ሰዎች ከሚያጥቡበት ስፍራ ዝቅ ብሎ ብዙ ብዙ ቀንዳውጣዎች ተረፍርፈው አየ በመደነቅም እነዚህ ቀንዳውጣዎች እንዴት ሊሞቱ ቻሉ? ብሎ ራሱን ጠየቀ ከዚያ በኃላ ምርምሩን ቀጠለ፡፡

**የማዳመጥ ጊዜ ጥያቄ፡ ለክሊሉ በምርምሩ ምን ውጤት የሚያገኝ ይመስላችኋል**

አክሊሉ ለማ ለዚህ በሽታ መከላከያ የሆነውን መድኊኒት ወዲያውኑ አላገኘም ምክንያቱም የአንዳንድ ተክል አይነቱ ብዙ ስለሆነ ከዚያ ውስጥ የትኛው አይነት አንዶድ ቀንዳውጣን እንደሚገድል ሲያጠና በመቆየቱ ነው ፡፡ የምርምሩ ተባባሪ ከሆነው ከዶክተር ለገሰ ዮሐንስ ጋር ነበር ጥናቱን የሚያካሂደው፡፡ከ30 አመታት ጥናትና ምርምር በኃላ ግን ምስጥሩን ደረሰበት ፡፡ ተስፋ ባለመቁረጥ በትጋት በመስራት ከዚህ ተክል ‹‹ እንዶድ 44›› የተባለ ቀንዳውጦችን የሚገድል መድኊኒት አዘጋጀ፡፡መድኊኒቱ ቀንዳውጣዎችን ሲገድል በነሱ ላይ ጥገኛ የሆኑ ተሃዋስያንም መኖር አይችሉም ፡፡

አክሊሉ ለማ የብልሃርዚያን በሽታ መድኃኒት ለማግኘትና ጥቅም ላይ እንዲውል ለማድረግ የነበረው ፅኑ ዓላማ ተሳካለት ፡፡

አንዳንድ የውጪ ሀገር መድኃኒት አምራች ኩባንያዎች ግን የዚህን ሳይንቲስት የሥራ ውጤት ለመቀበል ፈቃደኞች አልነበሩም፡፡ ነገር ግን በዚህ አስተሳሰባቸው ሊገፉ አልቻሉም፡፡ ምክንያቱም ምርምር በተለያዩ ቦታዎች ተሞክሮ ውጤታማ ሆኖ በመገኘት ከኢትዮጵያ ውጪ ባሉ ሀገሮች ተሰራጨ፡፡ ብዙ ቀንድ አውጣዎች በሚራቡበት ረግረጋማ ቦታም ተሰራጨ፡፡ በባዶ እግራቸው በውሃ ወይም በረግረግ ቦታ የሚሄዱ ድሆች ገበሬዎችና ሌሎች ሰዎችም በበሽታው ከመያዝ ተረፉ፡፡

አንደኛ ሳምንት ፡ሁለተኛ ቀን

ትምህርት ሁለት፡- መናገር

ትምህርት ሁለት ተማሪዎች ንግግር ካሂላቸውን እንዲያዳብሩ የሚያግዝ ይዘት ነው፡፡ በመማሪያ መፅሀፍ ላይ የቀረበውን ምንባብ ለተማሪዎች ያንብቡላቸው፡፡ ከዚያም በምንባቡ ላይ በተጠቀሰው ርዕስ ጉዳይ ዙርያ ‹‹እናንተ የዕድሩ አባላት ብትሆኑ ምን ሀሳብ ትሰጣላችሁ ?››ለሚለው ጥያቄ በቡድን በመወያየት ሀሳባቸውን በነፃነት እንዲገልፁ ያበረታቷቸው ፡፡ በዚህ ሂደት ሁሉም ተማሪዎች ተሳትፎ እንዲያደርግ በመሀከላቸው በመዘዋወር ያበረታቷቸው ፡፡ በመጨረሻም ከየ ቡድኑ አስተያየት እንዲሰጡ በመጠየቅ ሙሉ ክፍሉን ያወያዩ ፡፡ የዕለቱ ትምህርት ሲጠናቀቅ ተማሪዎቹ ለሚቀጥለው ክፍለ ጊዜ አንድ አጭር ልብወለድ አንብበው እንዲመጡ ያሳስቧቸው፡፡ በትምህርት ቤቱ በተመፅሀፍት ውስጥ ምን ዓይነት ልብወለድ እንዳለ ቀድመው በማወቅ ጥቆማ በመስጠት ይርዷቸው፡፡

አንደኛ ሳምንት፡ ሶስተኛ ቀን

ሐ. ትምህርት ሶስት ማንበብ

ባለፈው ክፍለ ጊዜ በተነገራቸው መሠረት አንድ አጭር ልብወለድ አንብበው የመጡ ስለሆነ ያነበቡትን መፅሀፍ ርዕስ፣ያጭር ልብወለዱን ርዕስ፣ ገጸባህሪያቱ እነማን እንደሆኑ ወዘተ. በሚል በመማሪያ መጽሀፋቸው ላይ ያሉትን ጥያቄዎች በመጠየቅ እንዲመልሱ ያድርጉአቸው፡፡ በደንብ የመለሱትን

ተማሪዎች ከሌሎች በተለየ በማበረታታት ( እጅግ በጣም ጥሩ ፣በጣም ጥሩ ፣ጎበዝ) በማለት እውቅና ይስጧቸው፡፡

ሁለተኛ ሳምንት አንደኛ ቀን

መ. ትምህት አራት -መፃፍ

በዚህ የትምህርት ክፍለ ጊዜ አራት ዋና ዋና የድርሰት አይነቶች በተመለከተ በመማሪያ መፅሀፋቸው ላይ የተቀመጠውን ማብራሪያ እንዲያነቡ ያድርጓቸው ፡፡ በመቀጠል በምሳሌ የተደገፈ ማብራሪያ በመስጠት ያስገነዝቧቸው ፡፡ ወይም ደግሞ አጠር ያለ ማስታወሻ በሰሌዳ ላይ በመፃፍ በደብተራቸው ላይ እንዲገለብጡ ያድርጓቸውና ማብራሪ ይስጧቸው ፡፡ በዚህ ሂደት ተማሪዎቹ እየፃፉ መሆናቸውንና ማብራሪያ ሲሰጣቸው በንቃት እየተከታተሉ መሆናቸውን ማረጋገጥ ያስፈልጋል ፡፡

ሁለተኛ ሳምንት፡ ሁለተኛ ቀን

ሠ. ትምህርት አምስት፡- መፃፍ

በትምህርት አራት ላይ ከተጠቀሱት አራታ ዋና ዋና ልብወለዶች መካከል አንዱ የሆነውን ተራኪ ድርሰት ለማስረዳት ‹‹ ወዳጃችን ሲከዳ ›› በሚል ርዕስ በናሙናነት የቀረበውን ተራኪ ድርሰት እንዲያነቡት ያድርጓቸው፡፡ ታሪኩን አንብበው ሲጨርሱ ቀጥሎ የቀረበውን የድርጊት ቅደም ተከተል በማስተዋል እንዲያነቡት በማድረግ ከታሪኩ ጋር አያይዘው ያስረዷቸው፡፡ በዚህ ሂደት ተማሪዎች ያልተረዱት ነገር ካለ እንዲጠይቁ ያበረታቷቸው፡፡ ለሚቀጥለው ክፍለ ጊዜ አጠር ያለ ተራኪ ድርሰት ፅፈው መምጣት ስለሚጠበቅባቸው አስቀድመው ማብራሪያ በመስጠት ይደግፏቸው፡፡ በመጨረሻም አጭር ተራኪ ድርሰት ፅፈው እንዲመጡ የቤት ሥራ በመስጠት የዕለቱን ትምህርት ያጠናቅቁ ፡፡

ሁለተኛ ሳምንት፡ ሶስተኛ ቀን

ረ. ትምህርት ስድስት፡-

ባለፈው የትምህርት ክፍለ ጊዜ በታዘዘው መሠረት ተማሪዎች ተራኪ ድርሰት ፅፈዋል ፡፡ በቡድን እንዲቀመጡ በማድረግ ደብተራቸውን በመቀያየር አንዱ የሌላውን ድርሰት እንዲያነቡት ማድረግና ጥሩ የሚሉትን አንዳንድ ድርሰት ከየቡድኑ እንዲመርጡ ያድርጉ የተመረጡትን ድርሰቶች የያዙት ተማሪዎች እንደገና እንደሌላ ቡድን በመመስረት አሁንም ልብወለዱን ተቀያይረው እንዲያነቡ በማድረግ አንድ ድርሰት እንዲመርጡ ያድርጉ፡፡ በመጨረሻ የተመረጠውን ድርሰት በመጠቀም ተማሪዎቹን እያወያዩ በልብወለድ ላይ የታሪክ መግለጫ ይፃፍላቸው ፡፡ ድርሰታቸውን ተቀያይረው በማንበብ አሪፍ ነው ያሉትን ሲመርጡ ‹‹ ለፃፉቸው ድርሰት ርዕስ ፣ ገፀባህሪያት ፣ መቼት ያለው መሆኑና የታሪኩ ድርጊት በጊዜ ቅደም ተከተል በግልፅ መቀመጡንና ጭብጥ ያለው መሆኑን በመገምገም እንዲመርጡ ያድርጓቸው፡፡

ሶስተኛ ሳምንት፡ አንደኛ ቀን

ሰ. ትምህርት ሰባት፡-

ትምህርት ሰባት ሰዋሰውን ለማስተማርየቀረበ ይዘት ነው፡፡ ባለፈው የክፍል ደረጃ የቃላት እርባታን በተመለከተ የተማሩ ስለሆነ በዚህ የክፍል ደረጃ ቅጥያ ምዕላዶችን በመጠቀም ከስም ቅፅልን እንዲመሠርቱ ለማድረግ የቀረቡላቸውን ምሳሌ ያብራሩላቸው፡፡ በምሳሌውም መሠረት በተሰጧቸው አስር ስሞች ላይ ተስማሚ የሆነውን ቅጥያ ምዕላድ በመጨመር ቅፅል እንዲመሠርቱ ያድርጓቸው ተማሪዎች ይህንን መልመጃ ሲሰሩ በክፍሉ ውስጥ በመዘዋወር አስራሩ ያልገባቸው ተማሪዎች ካሉ ተጨማሪ ምሳሌና ማብራሪያ በመስጠት ይስረዷቸው፡፡

ሶስተኛ ሳምንት፡ ሶስተኛ ቀን

ሸ. ትምህርት ስምንት ፡-

ስለ አውንታዊ እና አሉታዊ ዓ.ነገር የቀረበውን ማብራሪያ አንብበው እንዲገነዘቡ ያበረታቷቸው፡፡ ያለተረዱት ነገር ሊኖር ስለሚችል ተጨማሪ ማብራሪያ በመስጠት ያስረዷቸው፡፡ በመቀጠል በተሰጣቸው ምሳሌ መሠረት በመማሪያ መፅሀፋቸው ላይ የቀረቡትን ዓ.ነገሮች አውንታዊ ወይም አሉታዊ ዓ.ነገር በማለት እንዲለዩያድርጓቸው፡፡ በመጨረሻም የብጤ እርማት እንዲሰጣጡ ይዘዟቸው፡፡ ተማሪዎች ትክክለኛውን መልስ እጅ በማንሳት እንዲመልሱ በመጠየቅና በመንገር ያረጋግጡላቸው ፡፡

ሶስተኛ ሳምንት፡ ሶስተኛ ቀን

ቀ. ትምህርት ዘጠኝ፡-

ይህ ትምህርት ከትምህርት ስምንት የቀጠለ ነው ፡፡ በትምህርት ስምንት ላይ የቀረቡትን ዓ.ነገሮች አወንታዊና አሉታዊ በማለት ለይተዋል በዚህ ትምህርት ደግሞ በተሰጧቸው ቃላት አዎንታዊና አሉታዊ ዓ.ነገረሮችን እንዲመሰርቱ ያበረታቷቸው፡፡ በትክክል እየሠሩ መሆናቸውን በመከታተል የሚያነሱት ጥያቄ ካለ ማብራሪያ ይስጧቸው፡፡

4. የመረጃ መሳሪያ
    - ተቀርጾ የቀረበ የሚደመጡ አጭር ትረካ
    - በወረቀት ላይ ተጽፈው ለክፍሉ የሚታደሉ አጫጭር ልብወለዶች
    - ለናሙናነት የቀረበ ሞዴል ተራኪ ድርሰት

5.ግምገማ

- አርአያ የሆነ ሰው የህይወት ታሪክ አዳምጠው መልሰው መተረክ መቻላቸውን ማረጋገጥ
- መፍትሄ በሚሹ ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ችግር ፈቺ ንግግር ማድረጋቸውን መገምገም

- አጭር ልብወለድ አንብበው በመገንዘብ ለሚቀርብላቸው ጥያቄዎች ምላሽ መስጠታቸውን ማረጋገጥ
- ስሞች ላይ ቅጥያ ምዕላዶችን በመጨመር ቅፅሎችን መመስረታቸውን መፈተሽ
- አውንታዊና አሉታዊ ዓ.ነገሮችን ለይተው በመገንዘብ ዓ.ነገር መመስረታቸውን መመርመር

<u>በናሙናነት ለተመረጡ ጥያቄዎች መልስ</u>

ትምህርት ሰባት፡-

ከስም ቅፅልን መመስረት

1. ጉልበት - <u>ጉልበተኛ</u> -
2. ቂም - <u>ቂመኛ</u>
3. አሸዋ - <u>አሸዋማ</u>
4. ድንጋይ -<u>ድንጋያማ</u>
5. ጥርስ - <u>ጥርሳም</u>
6. ዘመን - <u>ዘመናዊ</u>
7. ወረት - <u>ወረተኛ</u>
8. ሀገር - <u>ሀገራዊ</u>
9. ሆድ - <u>ሆዳም</u>
10. ጥፍር - ጥፍራም

## ምዕራፍ ሰባት

## ኮተት

( 12 ክፍለ ጊዜያት)

1. **ርዕስ=አጭር ልቦለድ**

2. **የሚጠበቁ ውጤቶች**

ተማሪዎች የዚህን ምዕራፍ ትምህርት ከተማሩ በኋላ፦

- ምንባቡን አንብበው ፍሬ ሀሳቡን ይናገራሉ፡፡
- የራሳቸውን ማህበራዊ ሚና ያብራራሉ፡፡
- በበጎ ተግባር ላይ ይነጋገራሉ፡፡
- የአካባቢያቸውን የስራ ባህል የተመለከተ አመዛዛኝ ድርሰት ይጽፋሉ፡፡
- በፃፉት ድርሰት አፃፃፍ ላይ ይወያያሉ፡፡
- የአጭር ልቦለድን ምንነት ይገልጻሉ፡፡
- የአጭር ልቦለድ ባህሪያትን ይጠቅሳሉ፡፡
- አጭር ልቦለድ አንብበው ዋና ገፀባህሪያትን ይለያሉ፡፡
- የቃል ክፍሎችን ይለያሉ፡፡
- የአረፍተ ነገር ክፍሎችን ይለያሉ፡፡
- የሰዋስው ህግን የጠበቁ አረፍተ ነገሮችን ይመሰርታሉ፡፡

**3.ዝርዝር ይዘቶች**

**ትምህርት አንድ፦ በለሆሳስ ማንበብ**

- የቅድመ ማንበብ ጥያቄዎችን ይሰራሉ፡፡
- “ ሱስና መዘዙ ” የሚለውን ምንባብ በለሆሳስ ያነባሉ፡፡
- ድህረ ማንበብ/ አንብቦ የመረዳት ጥያቄዎችን ይሰራሉ፡፡

ትምህርት ሁለት፦ ማድመጥ

- የቅድመ ማድመጥ ጥያቄዎችን ይሰራሉ፡፡
- “ ድር ቢያብር ” የሚለውን ምንባብ መምህሩ/ሯ ሲያነብላቸው/ስታነብላቸው በጥሞና ያደምጣሉ፡፡
- በቡድን በመሆን የድህረ ማድመጥ ጥያቄዎችን ይሰራሉ፡፡

ትምህርት ሶስት፦ መናገር

- በቡድን በመሆን ተማሪዎች በአካባቢያቸው በማህበራዊ ህይወት ስላላቸው ሚና የደረጉትን ውይይት ይከልሳሉ፡፡
- የውይይታቸውን ፍሬ ሀሳብ ማስታወሻ በመያዝ በተወካዮቻቸው አማካይነት ለክፍል ጓደኞቻቸው በቃል ያቀርባሉ፡፡

ትምህርት አራት፦ በበጎ ተግባራት ላይ መወያየት

- በቡድን በመደራጀት ስለ ትምህርት ቤታቸው በጎ አድራጎት ክበብ ይወያያሉ፡፡

ትምህርት አምስት፦ የንግግር ክሂልን ማዳበር

- ባለፈው ክፍለ ጊዜ ያደረጉትን ውይይት የማጠቃለያ ሀሳብ በተወካዮቻቸው አማካይነት ለክፍል ጓደኞቻቸው በቃል ያቀርባሉ፡፡

ትምህርት ስድስት፦ አመዛዛኝ ድርሰት መፃፍ

- ስለ ድርሰት አይነቶች የቀረበውን ማስታወሻ ያነባሉ፡፡
- መምህር/ት ስለ ድርሰት አይነቶች የሚሰጡትን ገለፃ ተማሪዎች ይከታተላሉ፤ የሚያቀርቧቸውንም አስረጂዎች ያስተውላሉ፡፡
- በቀረበው መስታወሻ፣በተነገራቸው ገለፃና በአስረጂው መሠረት፣ የአከባቢያቸውን የስራ ባህል በተመለከተ አመዛዛኝ ድርሰት ጽፈው ለመምህራቸው እንዲያቀርቡ ቤት ወሰድ ስራ አድርገው ለመምህራቸው ያቀርባሉ፡፡

ትምህርት ሰባት፦ በፃፉት አመዛዛኝ ድርሰት አፃፃፍ ስርዓት ላይ መወያየት

- ስለድርሰት አይነቶች የቀረበላቸውን ማስታወሻና በመምህር/ት የቀረበላቸውን ገለፃ ያስተውላሉ፡፡
- በዚህ መሠረት የፃፉትን አመዛዛኝ ድርሰት አፃፃፍ በተመለከተ በቡድን ይወያያሉ፡፡
- የውይይታቸውን ዋና ዋና ሀሳቦች በተወካዮቻቸው አማካይነት ለክፍል ጓደኞቻቸው በቃል ያቀርባሉ፡፡

ትምህርት ስምንት፦ የአጭር ልቦለድን ምንነትና የአጭር ልቦለድ ባህሪያትን መገንዘብ

- የቀረበላቸውን ማስታወሻ ያነባሉ፡፡
- በመምህር/ት የሚቀርብላቸውን ገለፃና አስረጂ ይከታተላሉ፡፡
- ለጥያቄዎች ምላሽ በጽሁፍ ይሰጣል፡፡

ትምህርት ዘጠኝ፦ አጭር ልቦለድ በማንበብ የአፃፃፍ ዘዴውን መመርመር

- የቀረበላቸውን አጭር ልቦለድ ያነባሉ፡፡
- ለጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት ምላሽ ይሰጣሉ፡፡
- የአፃፃፍ ዘዴውን ይመረምራሉ፡፡

ትምህርት አስር፦ በልቦለድ ታሪኩ ውስጥ በታዩት ለውጦች ዙሪያ መወያየት

- በቋንቋ፣ በባህል፣በገፀባህሪ…አንፃር የታዩ ለውጦችን ይመረምራሉ፡፡
- የቡድናቸውን የማጠቃለያ ሀሳብ በተወካዮቻቸው አማካይነት ለክፍል ጓደኞቻቸው ያቀርናሉ፡፡

ትምህርት አስራ አንድ፦ ሰዋስው(የቃል ክፍሎች)

- የቃል ክፍሎችን በተመለከተ የቀረበውን አጭር ማስታወሻ ያነባሉ፡፡
- የተሰጧቸውን ቃላት በቃል ክፍሎች ለይተው ይጽፋሉ፡፡

ትምህርት አስራ ሁለት፦ የአረፍተ ነገር ክፍሎች

- የአረፍተ ነገር ክፍሎችን አጭር ማስታወሻ ያነባሉ፡፡
- አረፍተ ነገሮችን፣ በስማዊ ሀረግና በግሳዊ ሀረግ በመክፈል ይለያሉ፡፡
- አረፍተ ነገሮችን የሰዋስው ህግን ጠብቀው ይመሰርታሉ፡፡

የምዕራፉ የማበልጸገያ ጥያቄዎች

- በአረፍተ ነገር ውስጥ የተሰመረባቸውን ቃላት የቃል ክፍል ለይተው ይናገራሉ፡፡
- የተሰጧቸው አረፍተ ነገሮች ውስጥ ያሉትን ቃላት በሙሉ የቃል ክፍል ይለያሉ፡፡
- ስማዊ ሀረግና ግሳዊ ሀረግ ይለያሉ፡፡

4. **የትምህርቱ አቀራረብ**

*መምህር*

ከዚህ በታች ዐበይት በሆኑ ጉዳዮች ዙሪያ ብቻ አጠቃላይ የአቀራረብ ብልሃቶች ቀርበዋል፡፡የቀረቡት ብልሃቶች ትምህርቱን ከሞላ ጎደል በተሳካ ሁኔታ ለመምራት ያስችሎታል፡፡ነገር ግን እነዚህ ብልሃቶች ብቸኛ ናቸው ብለው ራስዎን በእነሱ ብቻ እንዳያጥሩ፡፡ እንደ ሁኔታዎች ጋባዥነት ወይም አስገዳጅነት ፣እንደ ትምህርት ቤትዎ ተጨባጭ ሁኔታ የራስዎን ፈጠራዎችና የተሻሉ ዘዴዎችን በመጠቀም ተማሪዎችዎን ሊያግዟቸው ይችላሉ፡፡

**አንደኛ ሳምንት፤ አንደኛ ቀን**

**ትምህርት አንድ፡ በለሆሳስ ማንበብ**

መምህር ተማሪዎችዎ የቀረበላቸውን ምንባብ ከማንበባቸው በፊት የቅድመ ማንበብ ጥያቄዎችን ያስሰሯቸው፡፡ የቁልፍ ቃላትን ፍች ያስገምቷቸው፡፡ “ ሱስና መዘዙ ” የሚለውን ምንባብ በየግላቸው በለሆሳስ እንዲያነቡ ያድርጓቸው፡፡ የድህረ ማንበብ መልመጃዎችን ያስሰሯቸው፡፡ መምህር/ት የእርስዎም እገዛ አይለያቸው፡፡

**አንደኛ ሳምንት፤ ሁለተኛ ቀን**

**ትምህርት ሁለት፡ ማዳመጥ**

መምህር “ ድር ቢያብር ” የሚለውን ምንባብ ለተማሪዎቹ ያንብቡላቸው፡፡ ከዚያ በፊት ግን የቅድመ ማድመጥ ጥያቄዎችን በቃል እንዲሰሩ ያበረታቷቸው፡፡ ተማሪዎችዎ የማድመጥ ፍላጎታቸው መነሳሳቱን ማረጋገጥ አለብዎት፡፡

የቅድመ ማድመጥ ጥያቄዎች

1. ‹‹ ድር ቢያብር አንበሳ ያስር ›› የሚለው ምሳሌያዊ ንግግር ምንን የሚገልፅ ነው?

2. ስለ ደቦ የምታውቁትን ለክፍል ጓደኞቻችሁ ተናገሩ፡፡

**ድር ቢያብር**

እኔ የምኖረው በኮንሶ ዞን በአንድ የገጠር መንደር ውስጥ ነው፡፡ የአካባቢያችን መልክአ ምድር ወጣ-ገባ ነው፡፡ የእኛ መንደር ሰዎች ዋንኛ መተዳደሪያ የእርሻ ሥራ ነው፡፡ በሁለተኛ ደረጃ ከብት ያረባሉ፤ ንብም ያንባሉ፡፡ ይሁን እንጂ መልክአ ምድሩ ወጣ-ገባ በመሆኑ የእርሻ ሥራችን በጣም አድካሚ ወይም እልህ አስጨራሽ ነው፡፡ እርከን መስራት እና የአፈርና የውሃ ጥበቃ ሥራ ማከናወን ፋታ የማይሰጡ የዘወትር ተግባራት ናቸው፡፡ በዓመት ውስጥ የምናገኘው የዝናብ መጠን አነስተኛ ስለሆነ ያለ መዘናጋት ስራችንን መስራት የህልውና ጉዳይ ነው፡፡

የኮንሶ ማህበረሰብ ጠንከራ የሥራ ባህል አለው፡፡ በአንድ መንደር ያሉ ሰዎች በሙሉ ሴት ወንድ ህፃን አዋቂ ሳይባል አንድ ላይ ሆነው ኃይላቸውን አስተባብረው ከባዱን ሥራ በአንድ ጊዜ በወኔ ያከናውኑታል፡፡ አንድ ሰው ብቻውን ቢሆን ብዙ ጊዜ ሊወስድበት የሚችለውን ሥራ አንድ ሰዓት ባልሞላ ጊዜ ይፈጽሙታል፡፡ በዚህ አይነት የህብረት ሥራ (ደቦ) የመንደራችን ነዋሪዎች በሙሉ ይሳተፋሉ፡፡

በዚህ የህብረት ሥራ ባህላችን አስቸጋሪውን መልክአ ምድር በቁጥጥራችን ስር ማድረግ ችለናል፡፡ በአነስተኛ የዝናብ መጠን በአግባቡ በመጠቀማችን በምግብ እህል ራሳችንን ከመቻል አልፈን ጤፍ፣ በቆሎ፣ ማሽላ፣ ማር የመሳሰሉ ምርቶችን ለአጎራባች ዞኖችና ክልሎች እንሸጣለን፡፡ በጠንካራ የሥራ ባህላችን በፈጠርነው የእርከን ሥራችን በአገር ደረጃ ብቻ ሳይሆን በዓለም አቀፍ ደረጃ ጭምር እውቅናን አግኝተናል፡፡

"ድር ቢያብር አንበሳ ያስር" የሚለው ምሳሌያዊ ንግግር በኛ ዞን በተግባር ተተርጉሟል፡፡ በአጠቃላይ በእርከን ስራችንና የ"ኒውዮርክ" ገፀ ምድር የአገር ውስጥና የውጭ አገር ጎብኚዎችን ቀልብ ስበናል፡፡ በዚህም ለበርካታ

የአካባቢያችን ወጣቶች የስራ ዕድል ከመፈጠሩም በተጨማሪ ለአካባቢያችንና ለአገራችን የቱሪዝም እንዱስትሪ የገቢ ምንጭ ሆኗል፡፡

መምህር/ት ለተማሪዎችዎ ምንባቡን በመካከለኛ ፍጥነት ሁለት ጊዜ ወይም ሶስት ጊዜ ካነበቡላቸው በኋላ፣ በሚከተሉት የድህረ ማድመጥ ጥያቄዎች ላይ በአነስተኛ ቡድን ሆነው ይወያዩበት፡፡ እርስዎም እየተከታተሉ ያበረታቷቸው፡፡

## የድህረ ማድመጥ ጥያቄዎች

1. የኮንሶ ማህበረሰብ የሚኖሩበት አካባቢ አጠቃላይ ገጽታ ምን ይመስላል?
2. የኮንሶ ነዋሪዎች በጋራ ሆነው የሚሰሯቸው ስራዎች ምን ምንድናቸው?
3. የህብረት ሥራው ለኮንሶዎች ምን ጥቅም አስገኝቶላቸዋል?
4. በእናንተ አካባቢ ያለው ማህበራዊ ግንኙነት ምን ይመስላል?
5. በዚህ ማህበራዊ ሕይወት ውስጥ የእናንተ ሚና ምንድነው?

## አንደኛ ሳምንት፤ ሶስተኛ ቀን

## ትምህርት ሶስት፡ ንግግር

መምህር ተማሪዎች ባለፈው ክፍለ ጊዜ “ ድር ቢያብር ” የሚለውን ምንባብ አዳምጠው በእነሱም አካባቢ ያለውን ማህበራዊ ግንኙነት በተመለከተ ያደረጉትን ውይይት ያስታውሱ፡፡ የውይይቱን ማጠቃለያ ሀሳብ የጋራ ያድርጉና በተወካዮቻቸው አማካይነት ለክፍል ጓደኞቻቸው በቃል ይግለጹ፡፡ አቅራቢዎቹን በመቀያየር የተማሪዎችን እኩል ተሳትፎ ያበረታቱ፡፡

## ሁለተኛ ሳምንት፤ አንደኛ ቀን

## ትምህርት አራት፡ በበጎ ተግባራት ላይ መወያየት

መምህር ተማሪዎችዎ በአነስተኛ ቡድኖች ይደራጁ፡፡ ችሎታ፣ ፆታና የመማሪያ ስልት በቡድን አደረጃጀት ወቅት ትኩረት ይሰጠው፡፡ በትምህርት ቤታቸው በጎ አድራጎት ክበብ ስለሚከናወኑ ተግባራት፣ ክበቡን ስለማጠናከርና ስለክበቡ የገቢ

ምንጭ ይመያዩ። እርስዎም በየጠረጴዛው በመሄድ የተማሪዎችን እኩል ተሳትፎ ያረጋግጡ። ድጋፍና ማበረታቻም ይስጧቸው።

**ሁለተኛ ሳምንት፤ ሁለተኛ ቀን**

**ትምህርት አምስት፦ የንግግር ክሂልን ማዳበር**

መምህር ተማሪዎች ባለፈው ክፍለ ጊዜ በነበሩበት ቡድን ይደራጁ። በትምህርት አራት ያነሱትን ሃሳብ ያስታውሱ። ፍሬ ሃሳቦቹን በማስታወሻ ይፃፉ። የጋራ ሀሳባቸውን በተወካዮቻቸው አማካይነት ለክፍል ጓደኞቻቸው በቃል ያቅርቡ።

**ሁለተኛ ሳምንት፤ ሶስተኛ ቀን**

**ትምህርት ስድስት፦ አመዛዛኝ ድርሰት መጻፍ**

መምህር ተማሪዎች ስለ ድርሰት አይነቶች የቀረበውን ማስታወሻ በጥሞና እንዲያነቡ ያድርጉ። በተለይ ስለ አመዛዛኝ ድርሰት የተፃፈውን ማስታወሻ ትኩረት እንዲሰጡበት ይደረግ። መምህር/ት እርስዎም በአመዛዛኝ ድርሰት ላይ አትኩረው ገለፃ ያድርጉላቸው። አስረጂም ይስጧቸው። በመጨረሻም ቤት ወሰድ ስራ በማድረግ አመዛዛኝ ድርሰት እንዲፅፉ ይስጧቸው።

**ሶስተኛ ሳምንት፤ አንደኛ ቀን**

**ትምህርት ሰባት፦ በፃፉት አመዛዛኝ ድርሰት አፃፃፍ ስርዓት ላይ መወያየት**

መምህር በትምህርት ስድስት ተማሪዎች የፃፉትን አመዛዛኝ ድርሰት በተመለከተ አፃፃፉን በማየት እንዲወያዩ ያድርጉ። ሀሳቡን የጋራ በማድረግ በተወካዮቻቸው አማካይነት ለክፍል ጓደኞቻቸው በቃል ያቅርቡ። እርስዎም ከአመዛዛኝ ድርሰት አፃፃፍ መመሪያ አንፃር ማጠቃለያ ይስጧቸው።

**ሶስተኛ ሳምንት፤ ሁለተኛ ቀን**

**ትምህርት ስምንት፦ አጭር ልቦለድ በማንበብ የአፃፃፍ ዘዴውን መመርመር**

መምህር ተማሪዎችዎ " ኮተት " የሚለውን አጭር ልቦለድ እንዲያነቡ ያድርጉ፡፡ ልቦለዱን ሲያነቡ በአጭር ልቦለድ ውስጥ ያሉትን ዋና ገፀ ባህሪያትን ለይተው እንዲያወጡ ይንገሯቸው፡፡ መልመጃዎችን ያሰሯቸው፡፡

**ሶስተኛ ሳምንት፤ ሶስተኛ ቀን**

**ትምህርት ዘጠኝ፦ የአጭር ልቦለድን ምንነትና ባህሪያት መገንዘብ**

መምህር ስለአጭር ልቦለድ ምንነትና ባህሪያት በተመለከተ የቀረበውን ማስታወሻ ተማሪዎችዎ በጥሞና ያንብቡ፡፡ እርስዎም አጭር ማብራሪያ ይስጧቸው፡፡ የቀረቡትንም የመልመጃ ጥያቄዎች ያስሰሯቸው፡፡

**አራተኛ ሳምንት፤ አንደኛ ቀን**

**ትምህርት አስር፦ በልቦለድ ታሪኩ ውስጥ በታዩት ለውጦች ዙሪያ መወያየት**

" ኮተት " በሚል ርእስ የቀረበውን ልቦለድ ታሪክ በማስታወስ በገፀ ባህሪያት ቋንቋ፣ባህል፣ወዘተ.የታዩ ለውጦችን በቡድን እንዲወያዩ ያድርጓቸው፡፡

እንዲሁም ከክፍል ውጭ በትርፍ ጊዜአቸው ቢያንስ ሁለት፣ ሁለት አጭር ልቦለድ እንዲያነቡና ስለ ገፀባህሪያት እና ስለአጭር ልቦለድ ባህሪያት እንዲዘግቡ ያድርጓቸው፡፡

**አራተኛ ሳምንት፤ ሁለተኛ ቀን**

**ትምህርት አስራ አንድ፦ ሰዋስው ( የቃል ክፍሎች )**

መምህር ተማሪዎች ስለቃል ክፍሎች የቀረበውን አጭር ማስታወሻ በትኩረት ያንብቡ፡፡ እርስዎም ገለፃ ያድርጉላቸው፡፡ ጥያቄ ይጠይቋቸው፡፡ ጥያቄ እንዲጠይቁም ያበረታቷቸው፡፡ በመልመጃ የተሰጧቸውን ቃላት፣የቃል ክፍል

ለይተው እንዲፅፉ ያድርጓቸው፡፡ እርስዎም ምሳሌ በመስጠት ያሳዩአቸው፡፡ተማሪዎችዎ እስኪረዱ ድረስ ሳይሰለቹ ያግዙአቸው፡፡

**አራተኛ ሳምንት፤ ሶስተኛ ቀን**

**ትምህርት አስራ ሁለት፡ የአረፍተ ነገር ክፍሎች**

መምህር ተማሪዎችዎ ከዚህ ቀደም በሌሎች ምዕራፎች እንዲሁም በሌሎች ክፍሎች የተማሯቸውን እንዲያስታውሱ ያድርጓቸው፡፡ በዚህ የትምህርት ክፍልም የቀረበውን አጭር ማስታወሻ እንዲያነቡ ያድርጉ፡፡ በተሰጣቸው ምሳሌ መሠረት አረፍተ ነገሮችን ስማዊ ሀረግና ግሳዊ ሀረግ እንዲለዩ ያበረታቷቸው፡፡ በመጨረሻም የሰዋስው ህጉን የጠበቁ አረፍተ ነገሮችን እንዲመሠርቱ ይንገሯቸው፡፡

የምዕራፉ የማበልፀጊያ ጥያቄዎች

በምዕራፉ ውስጥ የተነሱ ዋና ዋና ርዕሰ ጉዳዮችን የተመለከቱ ጥያቄዎች በዚህ ክፍል ቀርበዋል፡፡ የእርስዎ እገዛ ሳይለያቸው ተማሪዎች የማበልፀጊያ ጥያቄዎቹን ይስሯቸው፡፡ መምህር/ት እርስዎ ግብረ መልስ ይስጧቸው፡፡

5.ግምገማ

- ተማሪዎቹ “ ሱስና መዘዙ ” የሚለውን ምንባብ በለሆሳስ አንብበው በምንባቡ ሊተላለፍ የተፈለገውን ዋና ሀሳብ መናገራቸውን ማረጋገጥ፤
- “ ድር ቢያብር ” የሚለውን ታሪክ አድምጠው ስለ ማህበራዊ ህይወት፣ ስለ መተባበርና ስለ ደቦ መወያየት መቻላቸውን መከታተል፤
- የራሳቸውን ማህበራዊ ሚና ማብራራታቸውን መከታተል፤
- ስለ ትምህርት ቤታቸው በጎ አድራጎት ክበብ መወያየታቸውን መከታተል፤
- ስለ አጭር ልቦለድ ምንነትና ባህሪያት መናገር መቻላቸውን ማረጋገጥ፤

- አጭር ልቦለድ አንብበው ዋና ዋና ገፀ ባህሪያትን መለየት መቻላቸውን ማረጋገጥ፤
- የአካባቢያቸውን የሥራ ባህል የተመለከተ አመዛዘኝ ድርሰት መጻፍ መቻላቸውን ማረጋገጥ፤
- በፃፉት አመዛዛኝ ድርሰት አፃፃፍ ላይ ሲወያዩ መከታተል፤
- የቃል ክፍሎችንና የአረፍተ ነገር ክፍሎችን መለየት መቻላቸውን ማረጋገጥ፤
- የሰዋስው ህግ የጠበቁ አረፍተ ነገሮችን መመስረት መቻላቸውን ማረጋገጥ ነው፡፡

7.ለተመረጡ ጥያቄዎች መልስ

ትምህርት አንድ

እውነት/ሐሰት

1. ሐሰት 2. ሐሰት 3. ሐሰት 4. ሐሰት 5.እውነት

ትምህርት ስምንት

እውነት/ሐሰት

1. እውነት 2. ሐሰት 3. እውነት 4. እውነት 5. ሐሰት

ማዛመድ

1. መ 2. ሠ 3. ለ 4. ሀ 5. ሐ

ትምህርት አስራ አንድ

የቃል ክፍሎችን መለየት

1. ስም
2. ስም
6. ስም
7. ግስ

3. ግስ
4. መስተዋድድ
5. ተውሳከ ግስ
8. ቅፅል
9. ስም
10. ቅፅል

ትምህርት አስራ ሁለት

የአረፍተ ነገር ክፍሎችን (ስማዊ ሀረግና ግሳዊ ሀረግ) መለየት

1. ስማዊ ሀረግ= ኛካል
   ግሳዊ ሀረግ= ተማሪ ነው፡፡
2. ስማዊ ሀረግ= ዘነበች
   ግሳዊ ሀረግ= እናቷን ትመስላለች፡፡
3. ስማዊ ሀረግ= ተማሪዎቹ
   ግሳዊ ሀረግ= ደብዳቤ ጻፉ፡፡
4. ስማዊ ሀረግ= ለቤና
   ግሳዊ ሀረግ= በመኪና ወደ ሆሳዕና ሄደ፡፡
5. ስማዊ ሀረግ= ሰይድ የገዛው መጽሐፍ
   ግሳዊ ሀረግ= ጠፋ፡፡

የምዕራፉ ማበልፀጊያ ጥያቄዎች መልስ

ሀ. የቃል ክፍሎችን መለየት

1. ጂንካ= ስም
2. ነበሩ= ግስ
3. ቡላ= ስም
4. ቀይ= ቅፅል
5. ወደ= መስተዋድድ

ለ. በአረፍተ ነገር ውስጥ የሚገኙ ቃላትን፣ የቃል ክፍል መለየት

1. ሆርዶፋ(ስም)
   ጥሩ(ቅፅል)
   ሰው(ስም)
   ነው(ግስ)
2. ሰውዬው(ስም)
   አዘውትሮ(ተውሳከ ግስ)
   ፍራፍሬ(ስም)
   ይመገባል(ግስ)
3. ማንዴላ(ስም)
   ሰላም(ስም)
   ወዳድ(ቅፅል)
   መሪ(ስም)
   ነበረ(ግስ)

ሐ. የአረፍተ ነገር ክፍሎችን (ስማዊ ሀረግና ግሳዊ ሀረግ) ለይቶ መጻፍ

1. ስማዊ ሀረግ= ዱሎ
   ግሳዊ ሀረግ= ዛሬ ወደ ወራቤ ሄደ፡፡
2. ስማዊ ሀረግ= ሲማቶና ኢርባ
   ግሳዊ ሀረግ= ጓደኛሞች ናቸው፡፡
3. ስማዊ ሀረግ= የኮሌጃችን ተማሪዎች
   ግሳዊ ሀረግ= ፀረ ኮቭድ 19 ክትባት ተከተቡ፡፡

ምእራፍ ስምንት

ወራሾቹ ክ/ጊዜ 6

1. ርዕስ ፤ ወራሾቹ

2. የሚጠበቁ ውጤቶች

ተማሪዎች ይህን ትምህርት ከተማሩ በኂላ

- በልዩነትና ብዝሀነት ላይ ጉዳይ ያዳመጡትን ጭብጥ ያንጸባርቃሉ፡፡
- በፍጥነት ሃሳብ አፍልቀው ይናገራሉ፡፡
- የተራኪ ጽሑፍ አላባውያንን ለይተው ይገልጻሉ ፡፡
- በፈጣን የንባብ ስልት ያነባሉ፡፡
- የጽሕፈት ሂደትን ተከትለው ይጽፋሉ፡፡

3.ዝርዝር ይዘቶች

ሀ. መዳመጥ

- ለማዳመጥ ዝግጁ የሚያደርጓቸውን የቅድመ ማዳመጥ ጥያቄዎችን ይሰራሉ፡፡
- የሚቀርብላቸውን ምንባብ በትኩረት ያዳምጣሉ፡፡
- በዳመጡት ምንባብ መሠረት ያዳመጡትን ያንጸባርቃሉ፡፡

ለ. ትምህርት ሁለት፡- የንግግር ክሂል ማዳበር

- የሕይወት ተሞክሯቸውን መሰረት በማድረግ ይናገራሉ፡፡

ሐ. /ተራኪ ጽሑፍ አላባውያን/ መለየት

ትምህርት ሶስት ፡ /ተራኪ ጽሑፍ አላባውያን/

- ተራኪ ጽሑፍ

መ.ማንበብ

ትምህርት ሶስት፡-

- ጥቂት መረጃዎችን ለማግኘት የፍጥነት ንባብ ያከናውናሉ፡፡

ሠ. መጻፍ

ትምህርት አራት፡- የጽህፈት ደረጃዎች

4. የትምህርቱ አቀራረብ

ሀ.ትምህርት አንድ፡ማዳመጥ

መምህር/ት

በብዝሐነት ላይ የቀረበውን ጽሑፍ አዳምጠው ለጋደኞቻቸው ያንጽባርቃሉ፡፡ ልክ ቀደም ሲል በነበሩት የማዳመጥ ተግባራት እንደሚያደረጉት ቅድመ ንባብና የማዳመጥ ጊዜ እንዲሁም የድህረ ማዳመጥ ጥያቄዎች ለተማሪዎች መቅረባቸው መዘንጋት የለበትም፡፡

ለ.ትምህርት ሁለት፡-

ትምህርት ሁለት የንግግር ክሂል የሚዳብርበት ይዘት ነው፡፡ አስቀድሞ ሲነበብ ያዳመጡትን (ስለራሳቸው በሚገባ ስለሚያውቁ ) ይህን መነሻ በማድረግ ባዳመጡት ጉዳይ ላይ ያስተዋሉትን በቡድን ሆነው እንዲወያዩበት ያድርጓቸው ፡፡ በዚህ ወቅት በየቡድኑ ያሉ ተማሪዎች ሁሉም እንዲሳተፉ ክትትል በማድረግ ያበረታቷቸው፡፡

ሐ/የልቦለድ አላባውያንን መለየት

ከዚህ በታች አበይት በሆኑ ጉዳዮች ዙሪያ ብቻ አጠቃለይ የአቀራረብ ብልሃቶች ቀርበዋል፡፡ ቢመለከቷቸው ትምህርቱን ከሞላ ጎደል በተሳካ ሁኔታ ለመምራት ያስችሉዎታል፡፡ ነገር ግን እነዚህ ብልሀቶች ብቸኛ ናቸው ብለው ራስዎን በእነሱ ብቻ እንዳያጥሩ፡፡ እንደሁኔታዎች ጋባዥነት ወይም አስገዳጅነት እየተመለከቱ፣ የራስዎን ፈጠራዎችንና የተሻሉ ዘዴዎችን በመጠቀም ተማሪዎቹን ሊያግዟቸው ይችላሉ፡፡

ይህ ክፍል የሚ ለከተው የተራኪ ጽሑፍ አላባውያንን መለየት ነው፡፡ ወራሾቹ በሚል ርእስ የተጻፈ አንድ አጭር ተራኪ ጽሁፍ ቀርቧል ፡፡ ጽሁፉን በለሆሳስ በማንበብ የተራኪውን ጽሑፍ አላባ መለየት ዋናው ተግባር ነው፡፡ የተራኪ ጽሑፍን አላባ መለየት ለልቦለድ አላባውያን እንደ መነሻ አውቀት ሆኖ ያገለግላቸዋል፡፡

ትምህርት ሶስት ፤መናገር

ሐ.ትምህርት አራት፡- ማንበብ

ተማሪዎች በመማሪያ መጻህፋቸው ላይ መረጃን በፍጥነት ለማግኘት የሚከናወን ንባብ ይተገብራሉ፡፡ ይህን መረጃ ለማግኘት የቀረበው ንባብ የማንበብ ስልትን የሚመለከት ሲሆን፤ ፍጥነት የሚለካው በጊዜ ስለሆነ ጊዜ ወስነው ያስነብቡ፡፡

መ. መጻፍ

ትምህርት አምስት ፡- የጽህፈት ደረጃዎች

ተማሪዎች ለመጻፍ ሲዘጋጁ ማወቅ የሚገባቸው የአጻጻፍ ሂደቶች አሉ፡፡ እነዚህ ሂደቶች አስቀድሞ ሊብራራላቸው ይገባል፡፡ ምሳሌ በመማሪያ መጽሀፋቸው ላይ ቀርቧል፡፡ ሂደቱን ተከትለው እንዲጽፉ ከተማሪዎች ጋር ተጋርተው ይጻፉ፡፡

1. መርጃ መሳሪያዎች ፡-

   የአጻጻፍ ሂደት መመሪያዎችና ናሙና፣ የቢጋር ሰንጠረዥ/የትረካ ካርታ/ የብዝሀነት መገለጫ /የብሔር ብሄረ ሰቦች ስዕል፣- አለባበስ የሚያሳይ/

6. ግምገማ ፡-

- ሰለ ተራኪ ጽሑፍ አላባውያን መረዳታቸውን በሚሰጡት መልስ ማረጋገጥ
  - የማዳመጥ ጥያቄዎችን በትክክል መመለሳቸውን ማረጋገጥ
  - በተሠጣቸው ርእስ ላይ በንቃት መወያየታቸውንና ተሳትፎ ማድረጋቸውን መከታተልና ግብረ መልስ መስጠት፡፡
  - ስላነበቡት ነገር የተረዱትን በመጠየቅ መረዳታቸውን ማረጋገጥ
  - አጻጻፍ ስርዓትን ተከትለው መጻፋቸውንና ማረማቸውን መከታተል፡፡

7. በናሙናነት ለተመረጡ ጥያቄዎች መልስ

በምእራፉ መጨረሻ ላይ ይመልከቱ

አንደኛ ሳምንት ፤አንደኛ ቀን

ትምህርት አንድ፡ማዳመጥ/ በብዝሐነት ላይ የሚደመጥ ጽሁፍ

መምህር ከዚህ በታች የቀረበውን ምንባብ ሁለት ጊዜ ያንብቡላቸው፡፡ በመቀጠል ተማሪዎቹ ያዳመጡትን መልሰው ለጓደኞቻቸቸው ያንጸባርቁ፡፡ እርስዎ እየተዘዋወሩ ይከታተሉ፡፡

ብዝሐነት

ውበት እንደተመልካቹ ነው የሚባለው አባባል በብዛት ሲነገር እንሰማለን፡፡ በእርግጥ ለአንዱ የተዋበ ለሌላው ደብዛዛ ፣ለአንዱ ደብዛዛ የሆነ ለሌላው አንጸባራቂ ሆኖ መታየት የኖርንበት፣ ያደረግነው፣ የተረጋገጠና ያልተጋነነ ሐቅ መሆኑን አናውቃለን ፡፡ ውበት አንድ አይነትነት? ወይስ ልዩነት የሚል ጥያቄ ቢነሳ መልሳችን ምን ይሆን? እንደኔ ከሆነ ውበት ልዩነት ነው፡፡ሁሉም ነገር አንድ አይነት ሆኖ የተፈጠረ ነገርስ ቢሆን ምን አለ?

አንድ አይነት ናቸው ብለን የገዛናቸው፤የሰራናቸው፤የመረጥናቸው የቤት ቁሰቁሶች እንኳ በአንድ ነገራቸው ላይ አሳሳች ያልሆነ ልዩነት አይጠፋባቸውም ፡፡ አንድ አይነት ነገር ያሰለቻል፡፡የተለመደ ሲሆን ደግሞ ሊጠላም ይችላል፡፡ አስኪ ልብ ብላችሁ ተመልከቱ፤ሁለቱ ዐይኖቻችን ፣ሁለቱ ጆሮቻችን አንድ ቢመስሉንም ከፊታችን የተለያዩ አቅጣጫዎች ላይ በመገኘታቸው ብቻ እንኳን ልዩነታቸው ይታያል፡፡ በርግጥ ምድራችን በብዙ ልዩነቶች የተሞሉ በርካታ ነገሮችን አቅፋ ይዛለች፡፡

አቅፋ ከያዘቻቸው ልዩነቶች ለአብነት የሀገራችንን ህዝብ ብዘሀነት እንደ አንድ ምሳሌ አድርገን ልንውሰድ እንችላለን፡፡ ኢትዮጵያ በዝሀነትን ከሚያስተናግዱ የአፍሪካ ሀገሮች አንዷ ናት፡፡ ልዩነት ተፈጥሯዊ ነውና በብዘሀነት ውስጥም መስተናገዱ አይቀሬ ነው፡፡ የልዩነት ምንጩ ተፈጥሮ ያመጣው ጸጋ መሆኑን ለተገነዘበው ውበትን ቁልጭ አድርጎ የሚሳየው ምስል አለው፡፡ ኢትዮጵያ ከ85 በላይ ብሄሮችን አቅፋ የያዘች የመሆኗን ያህል በብዙሀነቷ ውስጥ ልዩነትን ታስተናግዳለች፡፡ ልዩነቱ የባህል፣ የቋንቋ እንጂ የስነ ልቦና አይደለም፡፡ የስነ ልቦና ትስስሩ ለዘመናት የዘለቀ ከአባት ወደ ልጅ የተላለፈ በማይፈታ አብሮነት የተጋመደ ነው፡፡ ይህ መጋመድ ምስክርነቱ ጠላት ደንበር በደፈረ ቁጥር ሆ ! ብሎ መነሳቱ በልዩነቱ ውስጥ ያለውን አንድነት ፍንትው አድርጎ

ያሰየናል፡፡ጥብቅ የስነ ልቦና ትስስር መኖሩን ከዚህ የተሸለ ምስክርነተ ሊኖረን አይችልም፡፡

የባህላችንና የቋንቋችን መለያየት አንደ ጠቃሚ ሀብት ስናየውና ስናደንቀው በረከቱ የበዛ ነው፡፡ አለባበሳችን፣ጭፈራችን፣አመጋገባችን ባህላዊ ሰርአታችን አይቶ ለሚደነቀው አንግዳ አገር ጎብኝ ውበታችን ልዩነታችን ከመሆኑም በላይ ይዞ የሚመጣው ምንዛሪ ለአገር ግንባታ ቤዛ ይሆናል፡፡

ልዩነታችን ውበታችንን አጉልቶ የሚያሳይልን ማስጌጫ ሆኖ ከተገኘ አንደ ጸጋ ቆጥረን በመከባበርና በመፈቃቀር ልናስቀጥለው ይገባናል፡፡ ስለሆነም ልዩነት የብዝሀነት ውጤት እንጂ የትንሽነትና የበታችነት ምልክት አድርገው ሊከፋፍሉን ለሚሹ ጠንቀኞች ፊት ልንሰጣቸው አይገባም፡፡

በአዘጋጆቹ

አንደኛ ሳምንት፤ ሁለተኛ ቀን

ትምህርት ሁለት፡ መናገር/ሃሳብ አፍልቆ በፍጥነት መናገር

መጀመሪያ ስለሚናገሩት ርእስ እንዲያስቡ ይንገሯቸው፡፡ ያሰቡትን ጥንድ
በመሆን ለጓደኞቻቸው አንዲናገሩ ያድርጉ፡፡ ሲናገሩ ግን በፍጥነት መናገር
አንዳለባቸው ያሳስቧቸው፡፡ አርሶም በመካከላቸው እየዞሩ ይመልከቷቸው፡፡

አንደኛ ሳምንት ፤ሶስተኛ ቀን

ትምህርት ሶስት፡የተራኪ ጽሁፍ አላባውያን

ወራሾቹ

በወይና ቀበሌ አበዲናጎና ካሚቴ የተባሉ አንድ ወንድና አንዲት ሴት የባለፀጋ ልጆች ነበሩ፡፡ ከወላጆቻቸው በርካታ ንብረቶችን በውርስ ስላገኙ ሥራ አይወዱም ነበር፡፡ አባታቸው በሞት ከተለየ ሁለት አመታት በኋላ በሳጥን ቆልፎ ከጎረቤት ያስቀመጠላቸውን ዕቃ መከፋፈል ፈለጉ፡፡ ወንዱ "እኔ ታላቅ ስለሆንኩ ካንቺ የሚበልጠውን መውሰድ አለብኝ እንጂ፣ እኩል መካፈል የለብኝም" ሲል፣ ሴቷ ደግሞ "አባቴ እጅግ ይወደኝ እንደነበር ታውቃለህ፣ ስለዚህ መውሰድ ያለብኝ እኔ ነኝ" በማለት መጨቃጨቅ ጀመሩ ፡፡

መስማማትም ስላልቻሉ፣ሳጥኑን በአደራ ካስቀመጡላቸው ሽማግሌ ቤት ሄዱ።ሁለቱም ሀሳባቸውን ለሽማግሌው በየተራ ገለፁ። ሽማግሌውም በልጆቹ ሀሳብ በጣም ተገረሙ። "ልጆቼ አባታችሁ ደግ ሰው ነበር። ለሰዎች የሚያዝን፣ ለእኔ ከማለት ይልቅ ለእናንተ የሚል ቸር ነበር። ለዚያ ደግነቱ ወሮታ የመለስኩ ስለመሰለኝ፣ የአባታችሁን አደራ ለአምስት ዓመታት ጠብቄ አቆይቼላችኋለሁ። እንዳይባክ ንባችሁም በማሰብ እስካሁን ሳልነግራችሁ ቆይቻለሁ። አሁንም በውስጡ ያለውን ሀብት ባላውቅም ተስማም ታችሁ እንድትከፍፈሉ እለምናችኋለሁ። አንተም ታላቅ በመሆንህ አንቺም ታናሽና ተወዳጅ በመሆንሽ የበለ ጠውን መውሰድ አለብኝ አትበሉ፤ ሁላችሁም እኩል ልትካፈሉ ይገባል" በማለት አግባቧቸው ። ሁለቱ ወራ ሾችም ሽማግሌው ባሉት መሠረት እኩል ሊከፋፈሉ ተስማሙ።ሽማግሌውም በአደራ ያስቀመጡትን ከልጆቹ ፊት አቀረቡ። ልጆቹም ሳጥኑን በአባታቸው ፊርማ መታሸጉን አረጋገጡ። ከዚያም በሽማግሌው እጅ ሳጥኑ እንዲከፈት ተስማሙ። ሽማግሌውም ሳጥኑን ከፈቱት፤ በውስጡ ግን ልጆቹ እንዳሰቡት ወርቅ ሳይሆን ምክር የያዘ መጽሐፍ ሆኖ ተገኘ። ሽማግሌውም በልጆቹ አባት ብልህነት በጣም ተደነቁ።የማያልቅ የሀብት ምንጭ የሆነውን መጽሐፍ በመዋዋስ እንዲያነቡትና እንዲጠቀሙበት አሳስበው አሰናበቷቸው።

(አማርኛ እንደአፍ መፍቻ ቋንቋ የተማሪው መጽሐፍ 6ኛ ክፍል ከገጽ112-113 የተወሰደ)

ከላይ የተመለከተውን አጭር ተራኪ ጽሑፍ ካነበቡ በኋላ የሚከተሉትን የተራኪ ጽሑፍ አላባውያን ለዩ።

ሁለተኛ ሳምንት፤አንደኛ ቀን፤

ትምህርት አራት፤ማንበብ /የንባብ ስልቶች/

ክንዋኔው ሁለት ተከታታይ የትምህርት ጊዜ ይወስዳል፡፡ በዚህኛው ትምህርት ጥልቅ ንባብ ተጨማሪ ጊዜ የሚፈለግ ስለሆነ በተከታዩ ትምህርት የሚቀርብ ይሆናል፡፡አርሶም ለተማሪዎችዎ ስለ ንባብ ስልት አጭር መግለጫ እንዲሰጡ ይጠበቅቦታል፡፡

.የንባብ ስልቶች

ንባብ የመቀበያ ክሂል ነው፡፡ በመሆኑም የአንድን የንባብ መልዕክት ጸሐፊው (መልዕክት አስተላላፊው)ስራዬ ብሎ ማለት የፈለገውን እንዲልለት አመቻችቶ ይጽፈዋል፡፡ ጸሐፊው ማስተላለፍ የፈለገውን ጉዳይ ሊል ከፈለገበት ዓላማ አንጻር ሲጽፈው አንባቢው ደግሞ በሚያነብበው ነገር ላይ ካለው ጉዳይ ጥብቅነት ወይም አሰፈላጊነት አኳያ ልብ ሰጥቶ ያነበዋል፡፡

ስለዚህ የንባብ ዓላማው የአነባበብ ስልቱን እንዴት ሊያመለክት እንደሚችል ቀጥሎ እንመለከታለን፡፡

### ሀ. የአሰሳ ንባብ (Scanning)

ስልቱም የሚፈለገው ጉዳይ እስኪገኝ ዓይንን ከግራ ወደ ቀኝ ከቀኝ ወደ ግራ በፍጥነት በማንቀሳቀስ፣ ገጾችን ገልበጥ ገልበጥ ከማድረግ ጋር ይያያዛል፡፡ የምንፈልገውን ስናገኝ ቆምና ረጋ ብለን እናነባለን፡፡ ተፈላጊው መረጃ ዓመተ ምህረት፣ ቀመር(ፎርሙላ)፣ የቦታ ወይም የድርጅት ስም፣ የስልክ ቁጥር፣ የትውልድ ቦታ፣ዕድሜ፣ የስራ ልምድ፣ አባባል፣ ተረት፣ በሰዎች መካከል የተደረገ ክርክር፣ የአንድ ነገር ፍቺ ትርጉም ትንታኔ….ወዘተ. ሊሆን ይችላል፡፡

### ለ. የገረፍ ገረፍ ንባብ (skimming)

በገረፍታ የንባብ ስልት ዓይን በሚነበበው ጉዳይ ላይ በፍጥነት ከወዲያ ወዲህ ይንቀሳቀሳል፡፡ ዓላማው በሚነበበው ጉዳይ ውስጥ አንድ ጠቃሚ የሆነ ነገር አገኝበት ይሆን ብሎ ማንበብን ይመለከታል፡፡ ይህን ሃሳብ ወይም ዕውቅ ነገር አገኛለሁ ብለን ለመፈለግ ወይም የተወሰነ ፍሬ ነገር ለማግኘት ወቅታዊነት ያለው ትኩረት የሚስብ ቁም ነገር ባገኝበት ብለን ገልበጥ ገልበጥ በማድረግ የምናነብበው የንባብ ስልት ነው፡፡ ይህን ስልት ተጠቅመን የምናነባቸው እንደ ጋዜጣ መጽሔት የማስታወቂያ ሰሌዳ የካርቱን መልዕክቶች …ወዘተ. የመሳሰሉት ናቸው፡፡

### ሐ. ጥልቅ የትኩረት ንባብ (intensive reading)

የትኩረት ንባብ በተለያዩ ስያሜዎች ሲጠራ ይስተዋላል፡የጥናት ንባብ(study reading) በአንዳንዶች የማስተዋል ንባብ ይሉታል፡፡ የትኩረት ንባብ ስልት በጥልቀት ዝግ ብሎ ወደፊትና ወደኋላ መለስ ቀለስ እያሉ በማብላላት ማንበብን ያሳያል፡፡ የሚነበበው ምን ያህል ቢበዛም ያነባበብ ስልቱ በዝግታ ነው፡፡ የምናነበውን ክፍል በትክክልና በምንጠብቀው መጠን መረዳታችንን እስክናረጋግጥ ድረስ መላልሰን እናነባለን፡፡በማንበብ መገምገምና ማመዛዘን እንዲሁም እያጣጣሙ ማገናዘብና የራስን አስተያየት ጨምሮ የተከተልነው የንባብ ስልት የማስተዋል የንባብ ስልት ይባላል፡፡

### ሠ. ሰፊ ንባብ (Extensive Reading

ለጠቅላላ ዕውቀትና ለመዝናናት የሚነበብ የንባብ ስልት ነው፡፡ ዋና ዓላማው የንባብ ልምድ ለማዳበርና ለደስታም ጭምር ይሆናል፡፡ በዚህ የአነባበብ ስልት የሚነበቡት በአብዛኛው ረጃጅም ልቦለዶች፣ አጫጭር ልቦለዶች፣በተለያዩ ጋዜጦችና መጽሔቶች ስር የሚቀርቡ መጣጥፎች፣ በተለያዩ ድርጅቶች እየተዘጋጁ የሚወጡ አዝናኝ ጽሑፎች ናቸው፡፡

ሁለተኛ ሳምንት ፤ሁለተኛ ቀን

ትምህርት አምስት ፤ የጥልቅ ንባብ ልምምድ

በዚህኛው የንባብ ጊዜ ተማሪዎች ለጥልቅ ንባብ የተዘጋጀውን ምንባብ አንብበው ለቀረቡ ጥያቄዎች መልስ ይሰጣሉ፡፡

ሁለተኛ ሳምንት ሶስተኛ ቀን

ትምህርት ሰድስት፡ የጽሕፈት ደረጃዎች /የጽሑፍ ሂደት /

ወደ ጽሕፈት ተግባር ከመሄዳቸው በፊት ስለሂደቱ መሳወቅ ተገቢ ነው፡፡
እርስዎም ቀድመው ማብራሪያውን ያስረዷቸው፡፡

የአጻጻፍ ሂደት

1. የአጻጻፍ ሂደት ምንድን ነው? የአጻጻፍ ሂደት ማለት በጽሐፍ ወቅት የምንከተለው የጽሕፈት ሂደት ማለት ነው፡፡ ማንኛውም ጸሁፍ በማንኛውም ርዕስ ይጻፍ፣ የረሳውን ፅሁፍ በእለት ከዕለት ተግባቦት ውስጥ እንደ ንግግር ተነግሮ የሚያበቃው ሣይሆን ጸሐፊው በየጊዜው እየመላለሰ ያርመዋል፤ያስተካክለዋል፡፡ በማረምም ይሁን በመፃፍ ሂደት ከሌሎቹ የቋንቋ ክሂልች በበለጠ መልኩ እየደጋገመ ስለሚጽፈው፣ ቀድሞ ስለጻፈውና ሲፅፍ ስለተሣሣተው በአንድ ጊዜ የሚያስብበት ሂደት ነው፡፡ ይህ ብቻ አይደለም፡፡ ከስነ ልሣንና ከስነ ፅሁፍ እውቀቶች ጋር ተያይዘው የሚመጡ የቋንቋ ህግና ሥርዓት ተከትል መፃፍ /ዓ.ነገርን በትክክል ማዋቀርን/፣ ከሚጽፈው ርዕስ ጋር ተስማሚ የሚሆኑ ቃላትን መምረጥ/ ማራኪና ትክክለኛ ሀሣብን ለታዳሚ በታለመለት መሠረት ማድረስ መቻልን ይጠይቃል፡፡

ከላይ የተዘረዘሩት ፀሐፉው በፅሁፍ ሂደት ውስጥ በተመሣሣይ ጊዜ፣ በተመሣሣይ ሁነት አእምሮውን የሚያጨናንቁት የፅህፈት አላባዎች /Writing Rubrics/ ድርሰቱ ምለዕ ሆኖ ታዲሚ ዘንድ እንዲደርስ እውቀትና ልምድ በእጅጉ የሚሹ ናቸው፡፡ደራሲ በሂደቱ የሚፅፍበትን ሃሳብ ማፈላለግ ትክክለኛነትን ማረጋገጥ፣ የሃሳብ ተጠየቃዊ አካሄድን መጠበቅ፣ ሀሣብን ማደራጀት፣ መተንተን፣ የጻፈውን ማረም ይጠበቅበታል፡፡ እነዚህ ተግባራት ሲከናውኑ በአንድ ጊዜ የሚያጠናቅቃቸው ሣይሆኑ በየፈርጃቸው ከፍፍል እንደአመጣጣቸውና እንደሚያስተካከለት የጽሕፈት አላባ መልክ መልክ ያሲዛቸዋል፡፡ ይህ የሚያሣየን መፃፍ ሂደታዊ እንደሆነ ነው ፡፡ በአንድ ጊዜ ታርሞ የማያልቅ በየጊዜው የሚታረም ቢሞከር የሚጨመር፣ የሚቀነስና የሚቃና ሃሣብ የሚገኝበት መሆኑን ነው፡፡ ከጽህፈት ዓላማዎች በተጨማሪ በደራሲው ልቦና ውስጥ ያለ የደርሰቱ የሃሣብ ምጥቀት፣ ቅለት፣ ተጨባጭነትና ረቂቅነት ነው፡፡ እነዚህ የሚወሰኑት አንደ ደራሲውና ታዳሚ ይሆናል፡፡

ማንኛውም ርዕሰ ጉዲይ ሲፃፍ የሚያልፍባቸው የጽሕፈት ደረጃዎች ወይም ሂደቶች አሉ፡፡ ከዚህ ቀጥሎ በቅደም ተከተል በማቅረብ እያንዳንዳቸውን ለማየት እንሞክራለን፡፡

ቅድመ ጽሕፈት /ከመፃፍ በፉት / ቅድመ ጽህፈት ወሣኙ የጽህፈት ሂደት ሲሆን ደራሲው ድርሰቱን ከመጀመሩ በፉት የሚያከናውናቸውን ተግባራትን የሚመለከት ተግባር ነው፡፡ ተግባራቱም የሚፅፍበትን ርዕስ መፈለግ፣ ዓላማውን መወሰን፣ ለማን እንደሚጻፍ መረጃ ከየትና እንዴት እንደሚገኝ፣

መረጃዉን እንደሚሰበሰብ የሚወሰንበት፣ ሃሳቡን እንዴት ማደረጀትና ማቅረብ የሚወስንበት ነው፡፡ እያንዳንደን የቅድመ መፃፍ ተግባራት በተናጠል ለማየት እንሞክራለን፡፡

1. ርዕስ መምረጥ ርዕስ በድርሰት ውስጥ የሚቀርበውን ሀሣብ ማሣየት አለበት፡፡ ርዕስ ማጥበብ በድርሰቱ የሚተለለፈውን መልእክት፣ የሚጻፈውን ይዘት፣ የአንባቢውን ማንነትና የጭብጥን ጠቀሜታ ከግምት ውስጥ ያስገባ መሆን አለበት፡፡ በተጨማሪም ርዕስ ሲጠብ ለመፃፍ የታሰበውን የገፅ ብዛት፣ የፅሁፍ ግብ መችነት ከግምት ውስጥ ያስገባ መሆኑን ማሣየት ይጠበቅበታሌ፡፡ ለምሣሌ፡- "የህዲሴው ግዴብ" በሚል ርዕስ ከአንድ ገፅ ባልበለጠ ወይም ከ300 ቃላት በማያንስ፣ በቅርጹ በይዘቱ የተዋጣለት ድርሰት ፃፍ የሚል የጽሁፍ ትዕዛዝ ስጥ ጸሐፉው ርዕሱን ከተዘረዘሩት ትዕዛዞች አንፃር ማጥበብ ይኖርበታል ማለት ነው፡፡
2. የድርሰታችንን ዋና ሀሣብ መለየት  እስካሁን ባካሄድናቸው ተግባራት ልንፅፍበት በፈለግነው ርዕሰ ዙሪያ የተለያዩ መረጃዎችን ከራሣችንም ሆነ ከሌልች የመረጃ ምንጮች የሰበሰብነው መረጃ ሁለ በድርሰታችን ውስጥ መካተት ሊይኖርበት ይችላል፡፡ ስለዚህ በድርሰቱ የምንገልፀውን /የምናቀርበውን በጣም ጠቃሚ ሀሣብ እና ከሱ ጋር የጠበቀ ዝምዴና ያላቸውን ሀሣቦች መምረጥ ይኖርብናል ማለት ነው፡፡
3. የምንፅፍበትን አላማ ማወቅ  /ከወሰንን የምናጠበው ርዕስ ከዓላማችን ጋር የሰመረ፣ የምንሰበስበው መረጃ አላማችንን የሚያሣካ፣የምንመርጠው የአደረጃጀት ስሌት ያን አላማ ከግብ የሚያደርስ ወዘተ ይሆናል፡፡
4. አንባቢን ማወቅ ሲባል ድርሰታችን የሚያነበውን ሰው ፍላጐቱን፣ እምነቱን፣ አቋሙን፣ ባህሉን፣ የትምህርት ደረጃውን፣ እዴሜውን፣ ጾታውን ወ.ዘ.ተ መለየት መቻል ነው፡፡
5. ቢጋር መንደፍ ቢጋር የምንፅፍበትን መንገድ ግልጽ አድርጐ ማሣያ "ኮምፓስ" ነው፡፡ ስለዚህ ድርሰት ከመፃፋችን በፉት የጠበበውን ርዕስ መሠረት በማድረግ ንድፍ ማዘጋጀት ያስፈልጋል፡፡
6. ማርቀቅ /መፃፍ   በግርድፍ የሚፃፍ የመጀመሪያው የጽሕፈት ጊዜ ተግባር ነው፡፡ ተግባሩም በቅድመ ፅህፈት የሰበሰብናቸውን መረጃዎች አረፍተ ነገር መልክ የምናቀናብርበት ነው፡፡ በሌላ አገላለፅ የቅድመ መፃፍ ዓላማ ከጸሐፉው ከአንባቢው ዓላማ ጋር የተስማማና የተዋጣለት ፅሐፍ /ሀተታን፣ ዘገባን፣ ደብዳቤን፣ ምልልስን፣ መመሪያዎች ወዘተ/ መፃፍ

እንደቻለ ሁኔታዎችን ማመቻቸት ነው። ፅሁፍ /ድርሰቱ/ የተዋጣለት ይሆን ዘንዴ ዓ.ነገር በአግባቡ ማዋቀር፣ ዓ.ነገርን አቀናጅቶ አንቀጽ መመስረት፣ አንቀጽን አደራጅቶ ሙለ ድርሰት መፃፍን ይመለከታል

የምዕራፋ የግምገማ መልሶች

አንደኛ ሳምንት፤ አንደኛ ቀን

ትምህርት አንድ፡ማዳመጥ/

ቅድመ ማዳመጥ ጥያቄዎች

1. የምንባቡን ርእስ ገምቱ።
   ስእሉን ውይም ፎቶውን አይተው ይገምታሉ።
2. ደቡብ ክልል የሚገኙ ብሔሮች ቁጥር ምን ያህል ይሆናል?
   ቀደም ሲል የሚያወቁ ካሉ ቁጥር ይጠራሉ ካልሆነም ይገምታሉ።
3. ብዛታቸውና ልዩነታቸው ያመጣው ጸጋ ምን ይመስላችኋል?
   ውበትና፣ ምንዛሪ

ድህረ ማዳመጥ ጥያቄዎች

1. በዝሐነት ውበት ሊሆን የሚችለው እንዴት ነው?
   አንድ ሆነን ስንተባበርና ስንከባበር
2. ልዩነት ውበት የሆነው ምን ስለሆነ ነው?
   ጸጋ ስለሆነ
3. ስለ ብዝሐነት የሰማችሁትን ለቡድን ጓደኞቻችሁ አስረዱ

   የተለያዩ መልሶች ሊሰጡ ይችላሉና ግብረ መልስ በመስጠት ይደግፏቸው።

አንደኛ ሳምንት ፡ሶስተኛ ቀን

ትምህርት ሶስት፡ የተራኪ ጽሑፍ አላባውያን

መልመጃ

ከላይ የተመለከተውን አጭር ተራኪ ጽሑፍ ካነበባችሁ በኋላ የሚከተሉትን የተራኪ ጽሑፍ አላባውያን ለዩ፡፡

| የተራኪ ጽሑፍ ካርታ | |
|---|---|
| መቼት | ታሪኩ የተፈጸመው መቼ ነው? ክረምቱ አልፎ በጸደይ ዋዜማ |
| | ታሪኩ የተፈጸመው የት ነው? ወይና ቀበሌ |
| | |
| ገፀ ባህሪያት | በታሪኩ ውስጥ ያሉት ዋና ሰዎች እነማን ናቸው |
| | አብዲናጎ፣ ካሚቴና ሽማግሌው |
| ችግር | ዋና ገፀ ባህሪው ያጋጠመው ችግር ምንድን ነው? |
| | በውርሱ ይገባኛል ጥያቄ የተፈጠረ አለመግባባት |
| ሤራ | በታሪኩ ውስጥ የተፈጠሩት ዋና ነገሮች ምንድን ናቸው? |
| | ውርሱ አጓጓቸው፣ለኔ ነው የሚገባው በሚል ተጋጨ፣ውርሱ ግን የሚያጣላ ሳይሆን የሚያስማማ ነበር |
| አጨራረስ | በታሪኩ ውስጥ የተከሰተው ችግር እንዴት ተቋጨ? |
| | ያልተጠበቀ አጨራረስ ነበረው፡፡ |

ሁለተኛ ሳምንት፤አንደኛ ቀን

ትምህርት አራት፤ማንበብ /የንባብ ስልቶች/

በመማሪያ መጽሀፉ ላይ የተመለከተውን አጭር ምንባብ በፍጥነት አንብበው ለቀረቡ ጥያቄዎች መልስ ይስጡ፡፡አርስዎ መልሳቸውን ተቀብለው ግብረ መልስ ይስጡ፡፡

1. ማስታወቂያው የምን ማስታወቂያ ነው?
   የስራ ፈላጊዎች ማስታወቂያ
2. ስራ ፈላጊ በትሆኑ ቶሎ ማወቅ የምትፈልጉት ምንድነው?
   የስራውን አይነት፣የሚጠይቀው የትምህርት ደረጃ…ወዘተ
3. ድርጅቱ የሚያበረታታው ማንን ነው?
   ሴቶችና የአካል ጉዳተኞችን
4. ይህን መረጃ በፍጥነት ለመረዳት ምን ዓይነት ስልት ተጠቀማችሁ?

ሁለተኛ ሳምንት ፣ሁለተኛ ቀን

ትምህርት አምስት ፣ የጥልቅ ንባብ ልምምድ

ይህን አጭር ምንባብ በጥንቃቄ ካነባበችሁ በኋላ ለሚከተሉት ጥያቄዎች መልስ ስጡ፡፡

1. ግሉኮስ ምን ዓይነት ስኳር ነው?

   ቀላል ስኳር

2. በዚህ ምንባብ ውሰጥ የተጠቀሰው ስኳር ከሻይ ስኳር በምን ይለያል?

   የሻይ ስኳር በፋብሪካ የተመረተ ሲሆን፣ በምንባቡ የተጠቀሰው ስኳር ግን ከተለያዩ የምግብ ይዘቶች ውስጥ ተጨምቆ በሰውነታችን ውስጥ የሚያገለግለው ነው፡፡

3. ሰውነት ውስጥ ገብቶ ቶሎ ጥቅም የሚሰጠው የትኛው ስኳር ነው?

   ቀላል ስኳር ነው፡፡

ሁለተኛ ሳምንት፣ ሶስተኛ ቀን

ትምህርት ስድስት፡ የጽሕፈት ደረጃዎችን /የጽሑፍ ሂደት / ተከትለው እንዲጽፉ ድጋፍ መስጠትና ከተማሪዎች ጋር በጋራ የሚሰራ አንድ ሞዴል ጽሑፍ ማሳየት ይጠበቅቦታል፡፡

- ርእስ ማስመረጥ
- መረጃ በምን መንገድ እንደሚሰበስቡ መጠቆም
- ለምን እንዲሚጽፉ መጠየቅና ግብረ መልስ መስጠት
- ለማን እንደሚጽፉ አስበው እንዲናገሩ እድል መስጠት
- ቢጋር እንዲነድፉ ማሳየት
- እንዲያረቁ/እንዲጽፉ ማበረታታት

ምእራፍ ዘጠኝ
9 ክ/ጊዜ

ዓባይ

1. የሚጠበቁ ውጤቶች

| |
|---|
| ተማሪዎች የዚህን ምዕራፍ ትምህርት ከተማሩ በኋላ<br>• ተራኪ ጽሑፍ አዳምጠው ጥያቄዎችን ይመልሳሉ፡፡<br>• በተሳጣቸው ሪዕሰ ጉዳይ ላይ ንግግር ያደርጋሉ፡፡<br>• አያያዦችን ተጠቅመው አረፍተ ነገር ይመሰርታሉ፡፡<br>• የምቱን ስልት ተከትለው ግጥም ያነባሉ፡፡<br>• ግጥም አንብበው መልእክቱን ይናገራሉ፡፡<br>• ግጥም አንብበው ወደ ዝርው ይቀይራሉ፡፡ |

2. ዝርዝር ይዘቶች

አንደኛ ሳምንት፤ አንደኛ ቀን

ትምህርት አንድ ፤ ማዳመጥ

- የቅድመ ማዳመጥ ጥያቄዎችን ይገምታሉ፡፡
- የማዳመጥ ጊዜ ጥያቄ ይገምታሉ፡፡
- ባዳመጡት ጽሑፍ መሰረት ጥያቄዎችን ይመልሳሉ፡፤

አንደኛ ሳምንት ፤ሁለተኛ ቀን

ትምህርት ሁለት፤ መናገር

በመማሪያ መጽሀፋቸው ላይ የቀረበውን ጽሁፍ አንብበው ፡-

- መልእክቱን ያሰላስላሉ፡፡
- ለአምስት በመሆን ይወያያሉ፡፡
- የተስማሙብትን ሃሳብ በቡድን መሪያቸው አማካይነት ለመምህራቸው ይናገራሉ፡፡

አንደኛ ሳምንት ፡ ሶስተኛ ቀን

ትምህርት ሶስት፤ መጻፍ

- አያያዦችን በተገቢ ቦታቸው በማስገባት አረፍተ ነገሮችን ያሟላሉ፡፡

ሁለተኛ ሳምንት፤አንደኛ ቀን

ትምህርት አራት ፤ መጻፍ

- አያያዦችን ተጠቅመው አረፍተ ነገሮችን ይመሰርታሉ፡፡

ሁለተኛ ሳምንት ፤ሁለተኛ ቀን

ትምህርት አምስት፡ ግጥም

- የቀረበላቸውን ግጥም የምቱን ስልት ተከትለው ያነባሉ፡፡

ሁለተኛ ሳምንት፡ ሶስተኛ ቀን

ትምምህርት ስድስት፤ ግጥም

- ያነበቡትን ግጥም ለሚመለከቱ ጥያቄዎች በጽሁፍ ምላሽ ይሰጣሉ፡፡
- የግጥሙን መልእክት በዝርው ይገልጻሉ፡፡

ሶስተኛ ሳምንት ፤አንደኛ ቀን

ትምህርት ሰባት፤ ግጥም

- የግጥሙን ስልተ ምት ተክትለው ያነባሉ፡፡

ሶስተኛ ሳምንት፤ ሁለተኛ ቀን

ትምሀርት ስምንት ፤ ግጥም

ግጥም አንብበው መልእክቱን ይናገራሉ፡፡

ሶስተኛ ሣምንት፡ ሶስተኛ ቀን

ትምህርት ዘጠኝ ፣ ክለሳ

*መምህር የምእራፉን ማበልጸጊያ ጥያቄዎች እንደ ክለሳ /ማጠቃለያ/ በሚመች መልኩ ያሰሯቸው፡፡*

3. የትምህርቱ አቀራረብ

አንደኛ ሳምንት፡ አንደኛ ቀን

ሀ. ትምህርት አንድ ማዳመጥ

መምህር/ት

በዚህ ምእራፍ የመጀመሪያው ትምህርት ማዳመጥ ነው፡፡ ይህን ክሂል ለማስተማር ‹‹የብርሃን ልጆች›› የሚል ጽሑፍ ቀርቧል፡፡ ጽሁፉን ከማንበብዎ በፊት የቁልፍ ቃላትን ፍች እንዲገምቱ ያድረጓቸው፡፡ ይህን ማድረግዎ የተማሪዎችን የቀደመ አውቀት ለመቀስቀስና የማዳመጥ ሂደቱ እንዳይደናቀፍ ለማድረግ ይረዳል፡፡ ማንበብዎን ገታ አድርገው የማዳመጥ ጊዜ ጥያቄ እንዲሞክሩ ያድርጉ አንብበው ሲጨርሱ ከጽሁፉ የተውጣጡ ጥቄዎችን በቃል እንዲመልሱ ያበረታቱ፡፡

የብርሀን ልጆች

አራት ወጣቶች ከአንድ ጎልማሳ ጋር ተቀምጠው የሞቀ ክርክር የሚመስል ጫወታ ይዘዋል፡፡ አንዱ ወጣት ‹‹በዘች አገር ምን ተስፋ? ምን አርአያ አለን? መሰደድን ብንመኝ በሱስ ብንጠመድ ማን ሊፈርድብን ይችላል?›› አለ፡፡ ወጣቶች እየተፈራረቁ ምክንያታዊ ብሶታቸው ገነፈለ፡፡ ሁሉም ሲናገሩ ከትከሻው ጀምሮ ጭቅንላቱን በጥቁር ፎጣ ሸፍኖ በእርጋታ የተቀመጠውን ጎልማሳ እየተመለከቱ ነበር፡፡ እሱም በትእግስት ከአንድ ጊዜ በስተቀር ያለምንም ማቋረጥ ሲሰማቸው ቆይቷል፡፡

ጉሮሮውን እንደ መጥረግ ‹‹እ! እ!›› አለና፤ በተራው ቀጠለ፡፡

‹‹ ወንድሞቼ ብሶታችሁ መነሻ ያለው ፣ቁጭታችሁም ተገቢ ነው፡፡ ያላችሁት ሁሉ ከሞላ ጎደል አውነት ነው፡፡ ነገር ግን ሁል ጊዜም ሊነጋ ሲል ጨለማው ይበረታል፡፡ የንጋቱን ጨለማ አልፈን ከንጋቱ ስንደርስ ባለሀብቶች ባለጸጎች ይሆናሉ፡፡ ምሁራን ጥበበኞች ይሆናሉ፡፡ ሹመኞች የህዝብ አገልጋይ ይሆናሉ፡፡ የሃይማኖትመሪዎች የምእመናን አባቶችይባላሉ፡፡ዜጎች ሁሉ ከስሜታዊነት ወደ ምክንያታዊነት ከአሉባታ ወደ መረጃ ይዞራሉ፡፡ሲወዘርላንድ የአለም ታማኝ ሀብታም ግምጃ ቤት ሆናለች፡፡ ደቡብ ኮሪያ በለጽጋለች፡፡ አነዚህ ከኢትዮጵያ የተፈጥሮ ጸጋ ሲወዳደሩ መናኛ ናቸው፡፡ ይሄ ታራራውን በዶማ የሚንድ ህዝብ ፣እራሱ በሰራው ማረሻ መሬት እየቀደደ ወገኑን የሚቀልብ አጆ ሸካረው ህዝብ የስራ ስልት የሚያውቅ መሪ፣መጽሀፍ የገለጡ በተግባር የተፈተኑ አደ

ጥበበኛ ምሁራንን ያገኘ ዘመን ኒውክሌር ይብላላል›› አለ፡፡ንግግሩ በራስ መተማማን የተላበሰ ከስሜት የጸዳ ይመስላል፡፡

**የማዳመጥ ጊዜ ጥያቄ**

**አራቱ ወጣቶች በምን አይነት ስሜት ውስጥ ይገኛሉ?**

‹‹ማነው ይሄ መሪ? ምሁራኖቹስ ? መቼ ነው የሚገኙት? ›› አለ አንደኛው ወጣት በስሜት፡፡

ሌላኛው ተቀበለ፡፡

‹‹ ሕዝቡ እኮ ቃተተ፡፡ ሀገራዊ ጀግና፣ሀጋረዊ ጠቢብ፣ ሀገራዊ አባት አጣን፡፡ ህዝቡ በየማዕዘኑ ይህን ይፈልጋል፡፡ ከመቃተቱ የተነሳ ተስፋ ያደረገውን ይከተላል፡፡ መጠባበቁ አደከመን፣በቃ ሰለቸን! መንገራገጨ ታከተን! ›› አለ፡፡

አንገቱን እየወዘወዘ ሲያዳምጥ የቆየው ጎልማሳ ‹‹ አውነትነው! ›› አለና ቀድሞ የጀመረውን ሀሳብ ቀጠለበት፡፡ ‹‹ ጨለማው ሲነጋ ፣የደፈረሰው ሲጠራ ፣ አቧራው ሲሰከሰን የምንጠብቃቸው ጀግኖች፣ጠቢባንና አባቶች ከመካከላችን ይነሳሉ፡፡በግብራቸው ይታወቃሉ፡፡ ስልጣን አይሹም፡፡ ህዝቡ ግን ይሾማቸዋል፡፡ ታወቃላችሁይባላሉ፤እንጂእናውቅላቸዋለን አይሉም፤ክብር አይፈልጉ፤ ህዝቡ ግን ያከብራቸዋል፡፡ እነሱም እየተራቆቱ ያለብሱታል፣ እየደከሙ ያበረቱታል፣ እየወደ ዱ ያዋደዱታል፣ትሁት ሆነ ጀግና ያደርጉታል፣በምጽት ሳይሆን በላቡ ያከብሩታል፡፡ ብርሀን የብርሀን ልጆች፣ብርሀን ዘኢትዮጵያ ይባላሉ፡፡ ሃይማኖታቸው ፍቅር ነው፡፡ ሐረጋቸው ኢትየጵያ ነው፡፡ ወገናቸው ሰው ነው፡፡ ሀገር እንጂ መንደር የላቸውም፡፡ ሀላፊነት እንጂ ስልጣን የላቸውም፡፡ የሚቃወማቸው ሞረዳቸው ነው፡፡የሚደግፋቸው ምርኩዛቸው ነው፡፡ ልበ ሙሉ ጀግኖች ስለሆኑ ተጻራሪያቸው በጮኸ ቁጥር ደምብረው አያስደነብሩም፡፡ የሚበልጣቸወን ያከብራሉ ፣የሚያንሳቸውን ያበረታታሉ፡፡

ምንጭ፡ ዓለማየሁ ዋሴ (ዶ.ር) ፡፡2010 ዓ.ም መርበብት ገጽ 217-224

አንደኛ ሳምንት፡ ሁለተኛ ቀን

ትምህርት ሁለት፤ መናገር

ይህ ትምህርት ተማሪዎች የንግግር ክሂላቸውን እንዲያዳብሩ የሚያግዝ ይዘት ነው፡፡ ተማሪዎች በመማሪያ መጽሐፋቸው ላይ ‹‹የብርጭቆ ውሃ›› በሚል ርእስ የቀረበውን ጽሑፍ በግል እንዲያነቡ ያድርጓቸው፡፡በመቀጠል የጽሑፉ መልእክት ምን እንደሆነ ለመገንዘብ እንዲያሰላስሉ ደቂቃ በመወሰን ይንገሯቸው፡፡

የተሰጣቸው ደቂቃ ሲያልቅ ጥንድ ጥንድ ሆነው ያሰቡትን ከጓደኞቻቸው ጋር እንዲነጋገሩበት ያድርጋቸው፡፡ በዚህ ሂደት በተማሪዎች መካከል በመዘወዋር ሁሉም ተማሪዎች እየተዳመማጡ በየተራ መነጋገራቸውን ያረጋግጡ፡፡ በመጨረሻም በጥንድ አውርተው የተስማሙበትን መልእክት እንዲናገሩ ያድርጓቸው፡፡

አንደኛ ሳምንት፡ ሶስተኛ ቀን

ትምህርት ሶስት፤ መጻፍ

ስለ አያያዥ ቃላት አገልግት ባለፈው የክፍል ደረጃ የተማሩትን እንዲያስታውሱ ይርዷቸው፡፡ በመቀጠል በትምህርት ሶስት ከቀረበው ጽሁፍ ውስጥ የተወሰዱትን ዓ.ነገሮች እንዲያነቡ በማድረግ አያያዦችን በመጠቀም የተመሰረቱ መሆናቸውን ለተማሪዎቹ ማብራሪያ ይስጧቸው፡፡ ከዚያም ቀጥሎ የቀረቡትን ዓ.ነገሮች በተገቢው ስርዓተ ነጥቦች እንዲያሟሉ ይርዷቸው፡፡ ሁሉም ተማሪዎች ሰርተው ሲጨርሱ እርስ በርሳቸው ደብተራቸውን እንዲቀያየሩ ያድርጓቸው፡፡ በመጨረሻም ትክክለኛው መልስ የትኛው እንደሆነ ተማሪዎችን በመጠየቅ እጅ እያነሱ እንዲመልሱ ያድርጓቸው፡፡ አረፍተ ነገሮቹን ለሚሟላት በክፍት ቦታዎች መግባት ያለባቸውን አያያዦች ለተማሪዎች በመንገር እርማት እንዲሰጣጡ ይርዷቸው፡፡ በመጨረሻም ውጤት መዝግበው ደብተሩን ለባለቤቱ እንዲመልሱ ያድርጓቸው፡፡

ሁለተኛ ሳምንት አንደኛ ቀን

ትምህርት አራት፡ መጻፍ

በትምህርት አራት በቀረቡላቸው አስር አረፍተ ነገሮች ውስጥ በክፍት ቦታዎቹ ላይ አያያዞችን እያስገቡ አረፍተ ነገሮቹ የተሟሉ እንዲሆኑ በማድረግ ልምምድ አድርገዋል፡፡ በዚህ ከፍለ ጊዜ ደግም በቀረቡላቸው አያያዥ ቃላት ተጠቅመው አረፍተ ነገሮችን በቡድናቸውእየተነጋገሩ እንዲመሰርቱ ያድርጓቸው፡፡ ከዚያ በፊት ግን አምስት አባላትን የያዘ ቡድን በመመስረት ለየቡደናቸው ሰብሳቢና ጸሀፊ እንዲመርጡ ያድርጓቸው፡፡ ሰብሳቢው አባላቱን እያወያየ አረፍተ ነገሮችን እንዲመሰርቱ ያደርጋል፡፡ ጸሀፊው ደግሞ የተስማሙበትን አረፍተ ነገር ይጽፋል፡፡ በመጨረሻም ለቡድናቸው በሚሰጣቸው ዕድል መሰረት፣ለክፍሉ ተማሪዎች እንዲናገሩ ያድርጓቸው ፡፡

ሁለተኛ ሳምንት፡ ሁለተኛ ቀን

ትምህርት አምስት፤ ግጥም

በመማሪያ መጽሐፋቸው ላይ ‹ዓባይ› በሚል ርእስ የቀረበውን ግጥም ስልተ ምቱን ተከትለው ድምጾን ከፍ አድርገው ያንብቡላቸው ። በመቀጠልግጥሙን በአንን ከፋፍለው ለተማሪዎች በመስጠት ተራ በተራ ድምጾቻቸውን ከፍ አድርገው የግጥሙን ዜማ ጠብቀው እንዲያነቡ ያድርጉ።

ሁለተኛ ሳምንት፡ ሶስተኛ ቀን

ትምህርት ስድስት፤ ግጥም

ተማሪዎች ባለፈው ክፍለ ጊዜ አባይ የተሰኘውን ግጥም በየተራ እያነበቡ ልምምድ አድርገዋል። በዚህ ክፍለ ጊዜ ደግሞ የግጥሙ መልእክት ምን እንደሆነ በቡድን በመወያየት በዝርው እንዲጽፉ ያድርጓቸው። በየቡድኑ የጻፉትን እየዞሩ በመመልከት እርማት ይስጧቸው ።

ሶስተኛ ሳምንት፡ አንደኛ ቀን

ትምህርት ሰባት፤ ግጥም

ልክ እንደ ትምህርት ሰባት ሁሉ በዚህም ትምህርት ክፍል ‹ተባበር› በሚል ርእስ ግጥም ቀርቧል።

መምህር ድምጾን ከፍ አድርገው ግጥሙን ለተማሪዎችዎ ያንበቡላቸው። በመቀጠልም በአንጓዎች በመከፋፈል ለተማሪዎች በመስጠት ስልተ ምቱን ተከትለው ግጥሙን በዜማ እንዲያነቡ ያድርጓቸው።ሁሉም ተማሪዎች የማንበብ እድል እንዲደርሳቸው ሰዓት በመያዝ ያለማምዷቸው።

ሶስተኛ ሳምንት፡ ሁለተኛ ቀን

ትምህርት ስምንት፡ የግጥም መልእክት

ተማሪዎች ባለፈው ክፍለ ጊዜ ሲያነቡ የነበረውን ግጥም ዛሬም በጥሞና ካነበቡ በኋላ በቡድን ሆነው በመወያየት የግጥሙ መልእክት ምን እነደሆነ እንዲጽፉ ያድርጓቸው። በመቀጠል የየቡድኑ ተወካዩች ለክፍል ጓደኞቻቸው እንዲናገሩ እድል ይስጧቸው። በውይይቱ ሂደት ሁሉም የቡደን አባላት እንዲናገሩ ያበረታቱ። በተማሪዎችም መካከል ተዟዙረው ይመልከቱ።

4. ግምገማ

- ተራኪ ጽሁፍ አዳምጠው ለሚቀርቡላቸው ጥያቄዎች ምላሽ መስጠታቸውን ማረጋገጥ፤
- በተሰታቸው ርእሰ ጉዳይ ላይ ንግገር ማድረግ መቻላቸውን መገምገም፤
- አያያዞችን በመጠቀም አረፍተ ነገሮችን መመስረታቸውን ማረጋገጥ፤
- የግጥምን ስልተ ምት ተከትለው በዜማ ማንበብ መቻላቸውን መፈተሽ፤
- ግጥም አንብበው መልእክቱን መናገር መቻላቸውን መመርመር፤
- የግጥሙን መልእክት በዝርው ጽሁፍ ማቅረብ መቻላቸውን ማረጋገጥ፡፡

5. በናሙናነት የተመረጡ ጥያቄዎች መልስ

ትምህርት አንድ

እውነት /ሐሰት

1. ሐሰት
2. እውነት
3. ሐሰት
4. ሐሰት
5. አውነት

ትምህርት አንድ

በቃል መልስ ስጡ

1. አራት
2. ይጨልማል
3. በሀገራችን ላይ እንዲነሱ የምንፈልጋቸው ሀቀኛ ጀግኖች፣ ጠቢባን፣ አባቶች ናቸው፡፡
4. ህዝቡ የቃተተው በሀገራቸው ላይ ሐቀኛ የሆኑ ለሕዝብ የሚያስቡ ጀግኖች፣ጠቢባንና አባቶች አንዲነሱ በተስፋ በመጠበቅ ነው፡፡
5. ሃይማኖታቸው ፍቅር፣ሀረጋቸው ኢትዮጵያ ነው፡፡

ትምህርት ሶስት

አያያዥ ቃላት

ሀ/ እንደ

ለ/ ነገርግን

ሐ/ ስለዚህ

መ/ ስለ

ሠ/ አለበለዚያ

ረ/ ስለ

ሰ/ ስለዚህ

ሸ/ ስለ

ቀ/ እንደ

በ/ ነገር ግን

## ምእራፍ አስር

**ሀብታሙ ሰው 10 ክ/ጊዜ**

**1/ የምዕራፉ ርዕስ፡ ሀብታሙ ሰው**

**2/ የሚጠበቁ ብቃቶች**

ተማሪዎች ከዚህ ትምህርት በኋላ
- የጓደኞቻቸውን ሀሳብ ያዳምጣሉ፡፡
- ሚና በመውሰድ ጭውውት ያደርጋሉ፡፡
- በተለያዩ ሀሳቦች ላይ ይከራከራሉ፡፡
- የምሳሌያዊ አነጋገሮችን ሃሳብ ያስረዳሉ፡፡
- ተረቶችን በትረካዊ ዘዴ ያወራሉ፡፡

**3.ዝርዝር ይዘቶች**

*ሀ ማዳመጥ፤*

**ትምህርት አንድ ፡ የጓደኛን ሀሳብ ማዳመጥ**

የልምድ ልውውጥ

**ለ. ትምህርት ሁለት፡ ክርክር**

- በአማራጭ ሃሰቦች ላይ መከራከር

**ትምህርት ሶስት፡ መናገር**

- ሚና በመስጠት የተሰጣቸውን ሚና ማጫወት፡

**ትምህርት አራት፡ ምሰሌያዊ ንግገሮችን መሰረዳት**

- ምሳሌያዊ ንግግሮችን በተመሰሳይ ምሳሌያዊ አነጋገር መተካት
- ካልሆነም በማብራሪያ ማስረዳት

**ትምህርት አምስት፡ ተረቶችን ማውራት**

ተረቶችን በተራኪ አቀራረብ ስልት ማውራት

**ትምህርት ስድስት፡ ተረቶችን ማውራት**

- የተረቶችን ሃሳብ ማብራራት

**4. የትምህርቱ አቀራረብ**

ትምህርት አንድ፤ የጓደኛን ሀሳብ ማዳመጥ

- የልምድ ልውውጥ

*መምህር/ት*

የምዕራፉ የመጀመሪያ ትምህርት ክፍል የጓደኛን ሀሳብ አዳምጦ መረዳት ነው፡፡ ለዚህ ትምህርት አቀራረብ የምንጠቀመው ርእስ በልምድ ልውውጥ ወይም በመስክ ጎዞ ላይ የተገኘ ሃሳብን ለጓደኛ ማካፈል ነው፡፡ ለዚህ የማዳመጥ ተግባር ይመች ዘንድ በመምህር የሚነበብ የመስክ ጉዞ ላይ ያተኮረ ዘገባ ማስደመጥ ነው፡፡

**ትምህርት ሁለት፡ መናገር**

- በዚህ ክፍል ሚና በመስጠት የተሰጣቸውን ሚና ማጫወት፡፡ የተዘጋጀ ሚና ጨዋታ ላይ ሚና በማከፋፈል ጨዋታውን ለቡድናቸው ማቅረበ ነው፡፡

**ትምህርት ሶስት፡ ክርክር**

- በአማራጭ ሃሰቦች ላይ መከራከር/ እናንተ ብትሆኑ ምን ታደርጋላችሁ?/

**ትምህርት አራት፡ ምስሊያዊ ንግገሮችን ማስረዳት**

- ምሳሊያዊ ንግግሮችን በተመሰሳይ ምሳሊያዊ አነጋገር መተካት
- ካልሆነም በማብራሪያ ማስረዳት

ትምህርት አምስት፡ ተረቶችን ማውራት

ተረቶችን በተራኪ አቀራረብ ስልት ማውራት

5. መርጃ መሳሪያዎች ፡-

ምሳሊያዊ ንግግሮች፣ውይይቶች፣ተረቶች፣ ሚና ጨዋታ

6. ግምገማ ፡- የቃል መልስ ፣ ሚናን መጫወት፣ተረት መተረክ፣ምሳሊያዊ ንግግርን መፍታትና ግበረ መልስ መስጠት

7. በናሙናነት ለተመረጡ ጥያቄዎች መልስ

በምእራፉ መጨረሻ ላይ ያገኙታል፡፡

## አንደኛ ሳምንት፡አንደኛ ቀን

## ትምህርት አንድ፡ ማዳመጥ

ከዚህ በታች መዘዙ በሚል ርዕስ መነሻ በማድረግ ስለ ሶስት ጓደኛሞች የቀረበ ትረካን ያንቡላቸው፡፡ ይህን ታሪክ ሲያነቡ በንቃት አዳምጠው ማስታወሻ እንዲይዙ ያድርጉ፡፡ ያዳመጡትን ሃሳብ መልሰው እንዲናገሩ ያድርጉ፡፡

ቅድመ ማዳመጥ

ተግባር አንድ፡ <u>የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልስ ገምቱ፡፡</u>

ለጓደኞቻችሁ በሆነ አጋጣሚ የደረሰባችሁን ችግር ተናግራችሁ ታውቃላችሁ?

እስኪ ጥንድ ሆናችሁ ተነጋገሩ፡፡

መዘዙ

ተሰፋ ከጠፋ ሶስት ሳምንት አልፎታል፤ጓደኞቹ ሳንቴና ቡለን ተጨንቀዋል፡፡ ከወልቂጤ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ዘጠነኛ ክፍል ጀምረው ለከፍተኛ ትምህርት ተመድበው ከመጡበት ጊዜ አስከ ተሰወረበት ሰአት ድረስ ተለያይተው አያወቁም፡፡ የግል የሚባል ሚስጥር የላቸውም ፡፡ አንዱ የሚሰራውን ለሌላው ካልተናገረ እምነት ያጎደለ አሰኪመስል ድረስ ቅርበት አላቸው፡፡ የተስፋ በድንገት ለሶሰት ሳምንታት መሰወር ግን አንቆቅልሽ ሆኖ ግራ አጋብቷቸዋል፡፡ስልኩ ዝግ ነው፡፡ ቤተሰቦቹ ደጋግመው ቢደውሉ ሲለማይነሳ ከአንዴም ሁለቴ በእነሱ ስልክ ሲደውሉላቸው ‹‹ፈተና ሰለበዛበት ስልኩን ዘግቶ ነው›› የሚል መልስ በመስጠት ዋሽተዋል፡፡ ተስፋን

ያልፈለጉበት፣ ያላስፈለገበት፣የቀራቸው ቦታ የለም፡፡ ዲላን ሙሉ በሙሉ አስሰዋታል፡፡

## ተስፋ የት የሄደ ይመስላችኋል?

ከሶስት ሳምንታት ቆይታ በኋላ ሁኔታው ተለዋውጦ ድንገት ከዶርማችው ተከሰተ፡፡ቢደነግጡም ሁኔታውን መገምገም ጀመሩ፡፡ ውብ የሆነ ስኒከር ጫማ ተጫምቷል ፣ ነጭ ቲሸርት ደርቧል ፣ጥቁር ጂንስ ሱሪ አጥልቋል፡፡ ግራ ቢገባቸውም ፤በሕይወት መገኘቱ እጅግ አሰድስቷቸዋል፡፡ ትምህርትን ያክል ነገር ጥሎ መጥፋቱ ፣ስልኩን መዝጋቱና ማንም ሳያውቅ መሰወሩን እንዲነግራቸው ስለፈለጉ ማኩረፉን ትተው እንዲያጫውታቸው ጠየቁት፡፡

ተስፋ፡- ጉሮሮውን አየተናነቀው በደከመ ድምጽ እንዲህ ሲል ተናገረ፡፡ ‹‹በመጀመሪያ ከዚህ ለመጥፌቴ ምክንያት የሆነው የተፈጠረ ድንገት ነው፡፡ አዲስ አበባ በንግድ ስራ ይተዳደር የነበረ ያጎቴ ልጅ ደውሎ ዲላ ከሚገኝ አንድ ሆቴል እነደሚገኝና ቶሎ ደርሼ እንዳናግረው አበሰረኝ ፡፡

ያው አንደምታውቁት ተማሪ ዘመድ ሲያስጠራው ያልታሰበ ሲሳይ አንደሚያስገኝለት የሚጠረጥረው ብዙ በመሆኑ፤ መረጃ ደበቆ ከግቢ መውጣቱ፣

፤ የሲሳዩን ተጋሪ መቀነስ ስለሚያስችል በሚስጥር ሾልኮ መውጣቱ የተለመደ ነውና ጊዜ ሳላጠፋ ከተባለው ሆቴል ደረስኩ፡፡ ያጎቴ ልጅ ነበር ፡፡ በሆቴሉ አልጋ ክፍል ይዞኝ ገባ፡፡ በቀጣዩ ቀን ለስራ ወደ ሞያሌ እንደሚሄድ ነግሮኝ ምሳ ጋብዞኝ፣ ከቻልኩ ለዛሬ አብሬው አንድቆይ ለመነኝ ፡፡ የማገኘውን ሲሳይ በማሰብ እሺታዬን ገለጽኩለት፡፡

ትንሽ አንደቆየን ስለ ትምህርቴ ጠየቀኝ ፣ስመረቅ ስለማገኘው ደሞዝ በቂነት ፣ሰለመዝናናነትና ፣በጉብዘና ወራት ስለመሮጥ ሰበከኝ ፡፡ ‹‹ይዞ መገኘት ነው›› አለኝ፡፡ የማግኘት አማራጮች የት እንዳደረሱት አወጋኝ፡፡ ምንም አንኳን የኢኮኖሚክስ ትምህርት ተማሪ ብሆንም፤ያልተማረው ያጎቴ ልጅ ሌክቸር ካስተማሪዎቼ በላይ ዘልቆ ገባኝ፡፡ በሰከንድ ያለምንም ፈተና ወደሱ የጥናት መስክ ተሸጋገርኩ፡፡ በቀላሉ ተቆጣጠረኝ፡፡

በማግስቱ ሞያሌ ተገኘሁ፡፡ በጉዟችን ስለ ኮንተሮባንድ፣ስለ ህገ ወጥ ንግድ አዋጭነት ነገረኝ፡፡ ስለ ድፍረት የሚየነሳሳ ተረት አስተማረኝ ‹‹ፈሪ ጮማ አይቆርጥም›› አለኝ፡፡ ምን አንደነካኝ ባለውቅም የሚነገረኝን ሁሉ በእሺታ

ተቀበልኩ፡፡ በል ሲለው ይናገራል፡፡ ለረጅም ሰዓት ደግሞ ይፈዛል፡፡ ምን እንደሆነ ለመጠየቅ ግን አልደፍርኩም፡፡በእሱ ሙሉ ወጪዬ ተሸፍኖልኝ ሞያሌ ደረስን ፡፡

በማግስቱ ጫማዎችን፣ልባሽ ጨርቆችን፣ሞባይሎችን በማዳበሪያ ሞልቶ ይዞ መጣ፡፡ አሮጌ ልብሴን አስወልቆ፣ እንዴት ደራርቤ እንደምለብስ መለስተኛ ስልጠና ሰጠኝ፡፡ ልብስ የለበሰ አሻንጉለት የሆንኩ አይነት ስሜት ተሰማኝ፡፡ ትርፉ የጋራ እንደሆነ ሲነገረኝ፤ አማራጭ የለኝምና ተስማማሁ፡፡ ከተማርኩት ትምህርት እውቀት ያገኘሁት ጭብጥ ብን ብሎ የጠፋ ያህል ተሰማኝ፡፡ ኮንትሮባንድ፣በሀገር ኢኮኖሚ እድገት ላይ የሚያስከትለውን ጫና በጥናታዊ ጽሁፎች ላይ በደንብ ያነበብኩ፣የተማርኩና ለሴሚስተር ማሚያ አቅርቤ ያገኘሁት ትልቅ ውጤት ዛሬ ረከሰብኝ፡፡ ምን ላድርግ ስብከቱ አደንዝዞኛል ፡፡ የመደንዘዝ ስሜትም ተጨጭኖኛል፡፡

ውረዱ! ውረዱ! የሚል የትእዛዝ ድምጽ ተሰማ ደንዝዤለሁ ፡፡ የደራረብኩት ልብስ ከበረሀው ሙቀት ጋር ተዳምሮ መተንፈስ እስኪሳነኝ አቅም አሳጥቶኛል፡፡ፈታሹ በጠንካራ መዳፉ የደራረብኩትን ልብስ ጨምድዶ እየገተተ ለኬላ ጠባቂዎች አስረከበኝ፡፡ ሁኔታዬን የጠረጠሩት ፈታሾች ወደ ልዩ መፈተሻ ክፍል አስገብተው መንጥረው ፈተሹኝ ፡፡ ከውስጥ ሱሪዬና ቲሸርት በስተቀር ሁሉም ከላዬ ላይ ወልቆ እርቃኔን ስጋደም እራሴን አላውቅም ነበር፡፡

በማግስቱ ራሴን ማወቅ ስጀምር ተማሪ መሆኔን ያወቁት ፖሊሶች ካጎቴ ልጅ ጋር ፍርድ ቤት አቀረቡን ፡፡ ለምርመራ ቀጠሮ ተጠየቀብን፡፡ ከአስራ አምስት ቀን በኋላ በኩንተሮባንድና አደንዛዥ እጽ ይዞ መገኘት ተከሰስን፡፡ ተማሪ መሆኔ የሚያሳየው የመታወቂያ ካርዴና የምርመራ ውጤቴ ከእጽ ተጠቃሚነት ነጻ ቢያደርገኝም፡፡ የደራረብከት ልብስ አግዚቢት ሆኖ በመገኘቱ ሲወረስ፤ በግለሰቦች ድጋፍ ይህን የምታዩትን ልበስና ጫማ ተመጽውቼ ፣ በሾፌሮች መራራት በሶስተኛ ሳምንቴ እዚህ ተገኘሁላችሁ፡፡ እናም ይቅር በሉኝ፡፡

ደህረ ማዳመጥ

- ከላይ የቀረበውን ታሪክ ለተማሪዎችዎ ካነበቡላቸው በኋላ በሃሰቡ ላይ ያወያዩዋቸው፡፡ ታሪኩን በማዳመጥ ያስታወሱትን መልሰው እንዲናገሩ ያደርጉ፡፡

## አንደኛ ሳምንት፡ሁለተኛ ቀን

**ትምህርት ሁለት ፡ መናገር**

**ክርክር**

በሚከተለው ታሪክ መነሻነት ለክርክር አንድ ታሪክ ቀርቧል ፡፡ በዚህ መሠረት የቀረበውን ርእስ አንበውላቸው እንዲከራከሩ በቡድን ያደራጇቸው፡፡

**አንደኛ ሳምንት፡ሶስተኛ ቀን**

**ትምህርት ሶስት፡ክርክር**

በትምህርት ሁለት ያለውን ርእስ መሰረት በማድረግ ከየቡድኑ የተወጣጡ አከላትን በሁለት ከፍለው እንዲከራከሩ ያድርጓቸው፡፡

**ሁለተኛ ሳምንት፡አንደኛ ቀን**

**ትምህርት አራት፡ ሚና ጨዋታ/ዳኝነት/**

- የኮንትሮባንድና የአደንዛዥ እጽ የሚል ርእስ ወስደው የኮንትሮባንድ ነጋዴ፣የፖሊስ፣የፈታሽ ፣የዳኛ ሚና ያከፋፍሉ፡፡
- ሚና የሚወስደውን ተማሪ ምን ላይ መዘጋጀት እንዳለበት ያነጋግሩ፡፡
- በቡድናቸው ጭውውት ለማቅረብ ይዘጋጁ፡፡
- ካልተስማሙ በእጣ ይመድቧቸው፡፡

**ሁለተኛ ሳምንት ፡ሁለተኛ ቀን**

**ትምህርት አምሰት፤ ሚና ተከፋፍሎ ጭውውት ማቅረብ**

በትምህርት አምስት ላይ ያደረጉትን ዝግጅት አስመልክተው የተሰጣቸውን ሚና በማከፋፈል በክፍሉ ፊት ወጥተው እንዲጫወቱ ያመቻቹላቸው፡፡

**ሁለተኛ ሳምንት፡ሶስተኛ ቀን**

**ትምህርት ስድስት ፡ተረት ማውራት**

ተረቱን በትርካ ዘዴ ያንብቡላቸው፡፡ ስለተረቱ ምን እንደተማሩ ይጠይቋቸው፡፡

<u>በቀጣዩ ክፍለ ጊዜ ተረት ሰበሰስበው እንዲመጡ ይንገሯቸው፡፡</u>

**ሶስተኛ ሳምንት ፡አንደኛ ቀን**

**ትምህርት ሰባት፡ሰበሰበው ያመጡትን ተረት ለቡድናቸወ ማውራት**

የሰበሰቡትን ተረት ለየቡድናቸው በየተራ ሲያወሩ መከታተልና ግብረ መልስ መስጠት፡፡

**ሶስተኛ ሳምንት፡ ሁለተኛ ቀን**

**ትምህርት ስምንት፡ምሳሌያዊ አነጋገርን መጠቀም**

**ሰበሰበው ያመጡትን ምሳሌያዊ አነጋገሮች እንዲያነቡ ማድረግ፡፡ በምን ምክንያት እንደተነገሩ መጠየቅና ግብረ መልስ መስጠት፡፡**

**ከዚህ በታች የሚገኘውን መስታወሻ ያስረዷቸው፡፡**

ምሳሊያዊ አነጋገሮች

- በአጭር አገላለጾች የሚጠቀሱ ዘይቢያዊ አነጋገር ያላቸው ናቸው፡፡
- ከህብረተሰቡ የእለት ገጠመኝ በምልከታ የተገኙ ናቸው
- ሀቅነታቸው በማህበረሰቡ የተረጋገጠላቸው ናቸው፡፡

ምሳሌ፡- ውሸታምና ስንቅ እያደር ይቀላል፡፡

ውሸታም ውሸቱ ሲጋለጥ ክብር ያጣል፤ ስንቅም እየተበላለት ሲቆይ ክብደቱ ይቀንሳል፡፡

የሚከተሉትን ምሳሌያዊ አነጋገሮች በጋራ ተወያይተው አባባሎቹን እንዲያስረዱ ይጠይቋቸው፡፡

1. ተልባ ቢንጫጫ በአንድ ሙቀጫ
2. ውሎ ውሎ ከቤት ኑሮ ኑሮ ከመሬት
3. ከሞኝ ደጅ ሞፈር ይቆረጣል

**የምእራፉ የግምገማ መልሶች**

**ትምህርት ስድስት ፤ተረት ማውራት**

**አዛምዱ**

1. ረ
2. ሠ
3. መ
4. ለ
5. ሐ
6. ሀ

2/ ተረቱ ምን ያስተምረናል?

ከፉ የሰራ መጨረሻው አያምርም፡፡

**ትምህርት ስምንት**

1. ተልባ ቢንጫጫ በአንድ ሙቀጫ
2. ውሎ ውሎ ከቤት ኑሮ ኑሮ ከመሬት
3. ከሞኝ ደጅ ሞፈር ይቆረጣል

**መምህር ፡ አማራጭ መልሶችን ይጠቀሙ፡፡**

1. ጉልበተኛ ደካሞችን ይቆጣጠራሉ፡፡
2. ሁሉም ከሞት አይቀርም፡፡
3. ብልጦች ሞኞችን ይጠቀሙባቸዋል፡፡

## አማርኛ እንደ ሁለተኛ ቋንቋ በመማር ከክፍል ደረጃው የሚጠበቅ አጥጋቢ የመማር ብቃት ደረጃ /ስምንተኛ ክፍል/

### የስምንተኛ ክፍል MLC (አጥጋቢ የመማር ብቃት)

ተማሪዎች ከዚህ ትምህርት በኋላ የሚከተሉት ችሎታዎች ይኖራቸዋል፡፡

ማዳመጥ፡-

- ለዝርዝር የቃል ጥያቄዎች አዳምጥው መልስ ይሰጣሉ፡፡
- ቀጥተኛና ቀጥተኛ ላልሆኑ የቃል ጥያቄዎች በቃል ምላሽ ይሰጣሉ፡፡
- ተጽፈው የቀረቡ የሚደመጡ ጽሁፎች ላይ የተመሰረቱ ፈሊጣዊ ጥያቄዎችን አዳምጠው በቃል ይመልሳሉ፡፡
- የእውነት ሀሰት ጥያቄዎችን አዳምጠው ምክንያታዊ ምላሽ ይሰጣሉ፡፡
- ባዳመጡት ጽሁፍ ላይ ተመስርተው ባዶ ቦታዎችን ያሟላሉ፡፡
- ላዳመጧቸው ምልልሶች፣መመሪያዎችና ጭውቶች ምላሽ ይሰጣሉ፡፡

መናገር፡-

- መፍትሄ ለሚሹ አካባቢያዊ ጉዳዮች በማስረጃ የተደገፈ የመፍትሄ ሀሳብ ይሰጣሉ፡፡
- በክፍል ተማሪዎች ፊት ቀርበው ስለራሳቸው ባህልና አካባቢያዊ ዕውቀት ላይ ተመስርተው ንግግር ያቀርባሉ፡፡
- መረጃ ላይ ተመስርተው አጭር ንግግር ያደርጋሉ፡፡
- ከመምህራቸውና ከክፍል ጓደኞቻቸው ጋር በተመረጡ ጉዳዮች ላይ ተመስርተው ንግግር ያደርጋሉ፡፡
- በቡድናቸው ውስጥ ውይይት ያካሂዳሉ፡፡
- ከክፍል ጓደኞቻቸው ጋር አወነወታዊ ተግባቦችን የሚፈጥሩ ጥያቄዎችን ይጠያየቃሉ፡፡
- በተሰጣቸው የሚና ጨዋታ ላይ ይሳተፋሉ፡፡
- ስላደረጓቸው የመስክ ጉብኝት ገለጻ ያደርጋሉ፡፡
- በቀረቡ ካርታዎች፣ፎቶዎችና ስዕላዊ መግለጫዎች ተመስርተው ማብራሪያ ይሰጣሉ፡፡
- ካነበቡት ጽሁፍ ያገኙትን አዲስ መረጃ ለጓደኞቻቸው በቃል ይገልጻሉ፡፡

ማንበብ፡-

- ውስን መረጃን ፈልፍሎ ለማግኘት ምንባብን ያነባሉ፡፡
- ዝርዝር መረጃዎችንና ፍንጮችን ከአውድ ለማግኘት ያነባሉ፡፡
- የተወሰኑ ፍንጮችን ተጠቅመው የጽሑፉን ሃሳብ ይተነብያሉ፡፡

- ልዩ ልዩ የማንበብ ስልቶችን ይጠቀማሉ፡፡
- ቀጣይነት ያላቸውን ትዕዛዞች፣ መመሪያዎችና ቅደምተከተሎችን አንብበው ይተገብራሉ፡፡
- ትዕዛዞችን፣መመሪያዎችንና ቅደምተከተሎችን አንብቦ ይተረጉማሉ፡፡
- አጫጭር ታሪኮችንና ግጥሞችን ለመዝናናት ያነባሉ፡፡
- የታሪኩን ጭብጥ ለመለየት ያነባሉ፡፡
- ታሪክን በማንበብ ቀጥተኛና ስውር ትርጉምን ይለያሉ፡፡
- የቅድመ፣ የጊዜና የድህረ ንባብ ስልቶችን በመጠቀም ጥያቄዎችን ይመልሳሉ፡፡
- አዲስ ሃሳብ ለመረዳት አንብበው ይወያያሉ፡፡
- ቀለል ያሉ ምንባቦችን ደጋግሞ በማንበብ የአዳዲስ ቃላትን ፍች ለመረዳት ጥረት ያደርጋሉ፡፡
- የተሸለና ውጤታማ የሰዋስው መማሪያ ስልቶችን ይጠቀማሉ፡፡
- አንብቦ በመረዳት ሂደት የአዳዲስ ቃላትን ፍች ይለያሉ፡፡
- የአዳዲስ ቃላትን ፍች ለመረዳት ፍንጮችን ወይንም ቁልፍ ቃላትን ይጠቀማሉ
- የቃላትን አውዳዊ ፍች ከዓረፍተ ነገር ውስጥ ይለያሉ፡፡
- የአዲስ ቃላትን ፍች ለመረዳት ሰፊ ንባብ ያነባሉ፡፡

መጻፍ፡-

- የጽህፈት ህጎችን ዕውቀት ተጠቅመው ይጽፋሉ፡፡
- የአንቀጽ አጻጻፍ ህጎችን ተጠቅሞ አንቀጽ ይጽፋሉ፡፡
- ሥርዓተ ነጥቦችን በአንቀጽ ውስጥ በተገቢው ቦታ ይጠቀማሉ፡፡
- በድርሰት ውስጥ አያያዦችንና መስተዋድዶችን ይጠቀማሉ፡፡
- ድርብ ዓረፍተ ነገሮችን ይጽፋሉ፡፡
- አያያዦችን በመጠቀም ሰፋፊ ዐረፍተ ነገሮችን ይጠቀማሉ፡፡
- የተዘበራረቁ ዐረፍተ ነገሮችን አስተካክለው አንቀጽ ይጽፋሉ፡፡

ቃላት፡-

- አንብቦ ለመረዳት የቃላት እውቀት አስፈላጊነትን ይገልጻሉ፡፡
- የቁልፍ ቃላትን ፍች  በጽሁፍ ውስጥ ይጠቀማሉ፡፡
- የቃላትን አውዳዊ ፍች ይገምታሉ፡፡
- መዝገበ ቃላትን በመጠቀም የቃላትን ፍች ይገልጻሉ፡፡
- ቃላትን ይመሰርታሉ፡፡
- ከቀረበው ምንባብ አዳዲስ ቃላትን ይለያሉ፡፤
- ቋንቋ የቃላትና የቃላት ፍች ዕውቀት መሆኑን ይለያሉ፡፡
- የቃላትን ፍቺ ተጠቅመው አንብበው ይረዳሉ፡፡
- የቃላትን አውዳዊ ፍች ይረዳሉ፡፡

ሰዋስው፡-

- የዐረፍተ ነገር ክፍሎችን ለይተው ዐረፍተ ነገር ይመሰርታሉ፡፡

- ተመሳሳይ ቃላትን ያዛምዳሉ፡፡
- የቃል ክፍሎችን ይለያሉ፡፡
- የተወሰኑ የሰዋስው ህጎችን አውቀው ይጠቀማሉ፡፡
- አዎንታዊና አሉታዊ ዓረፍተ ነገሮችን ለይተው ይጽፋሉ፡፡
- ዓረፍተ ነገር ይመሰርታሉ፡፡

መጀመሪያው ወሰነ ትምህርት                    የተሰጠው ክ/ጊዜ 9

ምእራፍ አንድ፡-የሕይወት ቅመም

አጠቃላይ የሚጠበቅ ውጤት፡- ቀላል ምንባብ አዳምጠው አስተያየት ይሰጣሉ፡፡
በቀረበላቸው ርዕሰ ጉዳይ ላይ ውይይት ያደርጋሉ ፡፡
የቁልፍ ቃላትን ፍቺ ይረዳሉ፡፡ በምንባቡ መሠረት ጥያቄዎችን ይመልሳሉ፡፡ የምንባቡን ዋና ሃሳብ ይገልጻሉ፡፡ መመሪያዎችን አንብበው ያብራራሉ፡፡ አንቀጽ ይጽፋሉ፡፡ የአረፍተ ነገር ክፍሎችን ለይተው ዐ.ነገር ያዋቅራሉ፡፡

| የማድመጥና የመናገር ብቃት፣እንዲሁም የቃላትና የስዋሰው ችሎታ | የማንበብና የመጻፍ ብቃት | የመማር ማስተማር ክንውኖችና ስልቶች |
|---|---|---|
| • የቅድመ ማዳመጥ ጥያቄዎችን መሞከር<br>• ጽሁፍን አዳምጠ ልዩ ልዩ ጥያቄዎችን መመለስ<br>• በታክስ ጉዳይ ላይ የተመለከቱ መረጃዎችን መሰረት በማድረግ መናገር<br>• የአረፍተ ነገር ክፍሎችመለየት<br>• አረፍተ ነገር ማዋቀር | • ቅድመ ንበብ ጥያቄዎችን በቃል መመለስ<br>• የቀረበላቸውን ምንባብ አስተካክሎ በማንበብ የድህረ ንባብ ጥያቄዎችን መመለስ<br>• አንቀጽ መጻፍ | • የቅድመ ማዳመጥ ጥያቄዎችን እንዲሞክሩ ማድረግ<br>• ቅድመ ንባብ ጥያቄዎችን በቃል እንዲመልሱ ማበረታት<br>• የሚነበብላቸውን ጽሁፍ አዳምጠው በርዕሰ ጉዳዩ ዙሪያ በቡድን እንዲወያዩ ማድረግ<br>• የቀረበላቸውን ምንባብ አስተካክለው በማንበብ የድህረ ንባብ ጥያቄዎችን እንዲመልሱ ማድረግ<br>• የአረፍተ ነገር ክፍሎችን ለይተው እንዲጽፉ ማድረግ<br>• አረፍተ ነገር እንዲያዋቅሩ ማድረግ<br>• አንቀጽ  እንዲጽፉ ማበረታታት |

ግምገማ፡-

- የማዳመጥ ጥያቄዎችን በትክክል መመለሳቸውን ማረጋገጥ
- በተሠጣቸው ርእስ ላይ በንቃት መወያየታቸውንና ተሳትፎ ማድረጋቸውን መከታተልና ግብረ መልስ መስጠት
- ስላነበቡት ነገር የተረዱትን በመጠየቅ መረዳታቸውን ማረጋገጥ
- የአ.ነገር ክፍሎችን ለይተው መረዳታቸውን ማረጋገጥ
- ዐ. ነገርና አንቀጽ መመስረታቸውን ማረጋገጥ

አማርኛ እንደ ሁለተኛ ቋንቋ መርሐ ትምህርት ስምንተኛ ክፍል

መጀመሪያው ወሰነ ትምህርት                    የተሰጠው ክ/ጊዜ 9

ምእራፍ ሁለት፡- የሕይወት መመሪያ

የሚጠበቅ ውጤት- ተማሪዎች ከዚህ ትምህርት በኋላ ምንባብ አዳምጠው አስተያየት ይሰጣሉ፤የሚና ጫዋታን መሰረት በማድረግ ምልልስ ያደርጋሉ፤መመሪያዎችን አንብበው ይገልጻሉ ፤ የዕለት ውሎ ዘገባ ይጽፋሉ፤ የቁልፍ ቃላትን ፍቺ ያስረዳሉ፤ ተመሳሳይና ተቃራኒ ቃላትን ያዛምዳሉ፡፡

| የማድመጥና የመናገር ብቃት፣የሕይወት ክህሎት እንዲሁም የቃላትና የስዋሰው ችሎታ | የማንበብና የመጻፍ ብቃት እንዲሁም የስነ ጽሁፍ ችሎታ | የመማር ማስተማር ክንውኖችና ስልቶች |
|---|---|---|
| • የቁልፍ ቃላትን ፍቺ መገመት፡፡<br>• ጽሁፍን ካዳመጡ በኃላ የተለያዩ ጥያቄዎችን መመለስ፡፡<br>• ቀደም ሲል ጠንክሮ መስራት በሚል ርዕስ በቀረበላቸው ምንባብ ላይ ውይይት ማካሄድ፡፡<br>• የሚና ጫወታ ድርሻ ከተከፋፈሉ በኂላ ልምምድ ማድረግ<br>• ዘገባ መጻፍ<br>• ተመሳሳይና ተቃራኒ ቃላትን ማዛመድ | • የቀደመ እውቀትን መቀስቀስ<br>• አዳምጦ መረዳትና ሃሳቡን ማብራራት<br>• አንብቦ መረዳትና ሀሳቡን መግለጽ<br>• የጽሑፍን ፍሬ ነገር መጻፍ<br>• ተመሳሳይና ተቃራኒ ቃላትን ፍች ለይተው መጻፍ፡፡ | • ቁልፍ ቃላትን ፣የምንባብ ርእስን መገመት<br>• የአዳምጦ መረዳት ጽሑፎችን ሃሳብ ማበራራት<br>• የአንብቦ በመረዳት ማጠቃለያ መስጠት<br>• የሚና ጨዋታና ማከፋፈል<br>• የዘገባ ጸሕፈት |

ግምገማ

- ጠንክሮ መስራት የሚለውን ጽንሰ ሀሳብ አዳምጠው መረዳታቸውን ማረጋገጥ፣
- ሰዎች በተሰማሩበት የሥራ መስክ ውጤታማ ለመሆን ምን ማድረግ እንደሚገባቸው አዳምጠው መገንዘባቸውን መገምገም፣
- በሚና ጫዋታ ምልልስ ማድረግ መቻላቸውን መፈተሸ፣
- የህይወት መመሪያዎችን መዘርዘር መቻላቸውን ማወቅ፣
- የእለት ውሏቸውን በዘገባ መልክ መፃፍ እንዲቻሉ ማረጋገጥ፣
- ለሚቀርቡላቸው ጥያቄዎች በማስረጃ የተደገፍ ምላሾችን መስጠት መቻላቸውን መገምገም፣
- የቃላትን ተመሳሳይና ተቃራኒ ፍቺ ለይተው መረዳታቸውን መፈተሸ

አማርኛ እንደ ሁለተኛ ቋንቋ መርሐ ትምህርት ስምንተኛ ክፍል

መጀመሪያው ወሰነ ትምህርት የተሰጠው ክ/ጊዜ= 12 ክፍለ ጊዜያት

ምእራፍ ሶስት፡- የሰው ልጆች አቅም

**<u>የሚጠበቁ ውጤቶች</u>** ተማሪዎች ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት በኂላ፦ ምንባብ አዳምጠው ለጥያቄዎች ምላሽ ይሰጣሉ፤በችግር ፍቺ ክርክር ይሳተፋሉ፤የምንባቡን ዋና ሀሳብ ይገልፃሉ፤ ለቃላት አውዳዊና መዝገበ ቃላዊ ፍች ይሰጣሉ፤የወዳጅ ዘመድ ደብዳቤ፣የጥሪ ደበዳቤና ማመልከቻ ይጽፋሉ፤ ምዕላዶችን ይነጥላሉ፤ያጣምራሉ።

| የማድመጥና የመናገር ብቃት፣የሕይወት ክህሎት እንዲሁም የቃላትና የስዋሰው ችሎታ | የማንበብና የመጻፍ ብቃት እንዲሁም የስነ ጽሁፍ ችሎታ | የመማር ማስተማር ክንውኖችና ስልቶች |
|---|---|---|
| • የቅድመ ማድመጥ ጥያቄዎችን መስራት<br>• ስለ ስርአተ ፆታ በቡድን መወያየት<br>• በችግር ፈቺ ክርክር መሳተፍ<br>• የቡድናቸውን ሀሳብ ለክፍል ጓደኞቻቸው በቃል ማቅረብ<br>• ለቃላት አውዳዊ ፍች መስጠት<br>• የሰው ልጅ ዐቅም በሚለው ምንባብ ዋና ሀሳብ ምንነት መነጋገር<br>• ለቃላት አውዳዊ ፍች መስጠት<br>• ምእላድን መነጠልና ማጣመር | • የቅድመ ማንበብ ጥያቄዎችን መመለስ<br>• ዋና ሀሳብ ለማግኘት ማንበብ<br>• የጊዜ ማንበብ ጥያቄዎችን መመለስ<br>• የድህረ ማንበብ ጥያቄዎችን መመለስ<br>• የወዳጅ ዘመድ ደብዳቤ መጻፍ<br>• ማመልከቻ መጻፍ<br>• የጥሪ ደብዳቤ መጻፍ | • የቅድመ ማድመጥ ጥያቄዎችን ማሰራት<br>• የሚደመጠውን ምንባብ ማቅረብ<br>• ተማሪዎች ሲወያዩ/ ሲከራከሩ/ ሲሰሩ መከታተልና መደገፍ<br>ምሳሌ በመስጠት በምሳሌው መሠረት እንዲሰሩ ማለማመድ/ማድረግ |

ግምገማ

- ምንባብ ሲነበብላቸው አዳምጠው መረዳታቸውን ለማረጋገጥ ጥያቄዎችን እየጠየቁ ማረጋገጥ
- በቀረበላቸው ርዕስ ጉዳይ ላይ ንቁ ተሳትፎ አድርገው መከራከራቸውን መከታተል እና በመጨረሻ የመፍትሄ ሀሳቦችን እንዲያቀርቡ በማድረግ የንግግር ችሎታቸውን ማጤን
- የምንባቡ-ብ ዋና ሀሳብ መረዳታቸውን ማረጋገጥ
- የቃላትን አውዳዊ ፍች መረዳታቸውን ማረጋገጥ
- የወዳጅ ዘመድ ደብዳቤ በትክክል መፃፍ መቻላቸውን መከታተል
- ማመልከቻ መፃፍ መቻላቸውን መከታተል
- የጥሪ ደብዳቤ መፃፍ መቻላቸውን መከታተል
- የቃላትን መዝገበ ቃላዊ ፍች መፈለግ መቻላቸውን ማረጋገጥ
- ምዕላዶችን መነጠልና ማጣመር መቻላቸውን ማረጋገጥ

አማርኛ እንደ ሁለተኛ ቋንቋ መርሐ ትምህርት ስምንተኛ ክፍል

መጀመሪያው ወሰነ ትምህርት የተሰጠው ክ/ጊዜ 9 ክ/ጊዜ

ምእራፍ አራት፡- አካቶ ትምህርት

የሚጠበቅ ውጤት፤ተማሪዎች ከዚህ ትምህርት በኋላ ሳይንስና ቴክኖሎጂን ያካተተ መረጃ የያዘ ጽሑፍ አዳምጠው አስተያየት ይሰጣሉ፤ስእሎችንና ሁነቶችን በመተንተን የተጓደሉ ሃሳቦችን ያሟላሉ፤በማህበራዊ ጉዳዮች ላይ ውይይት በማድረግ ይሳተፋሉ፤ያልተሟሉ አረፍተ ነገሮችን የያዘ አንቀጽ ያሟላሉ፤የቃላትን መሰረት በመለየት ቃላትን ይመሰርታሉ፤ቃላትን በቃል ክፍሎቻቸው መሰረት ይመድባሉ፡፡

| የማድመጥና የመናገር ብቃት፣የሕይወት ክህሎት እንዲሁም የቃላትና የስዋሰው ችሎታ | የማንበብና የመጻፍ ብቃት እንዲሁም የስነ ጽሁፍ ችሎታ | የመማር ማስተማር ክንውኖችና ስልቶች |
|---|---|---|
| • ሳይንስና ቴክኖሎጂን ያካተተ መረጃ የያዘ ጽሑፍ አዳምጠው አስተያየት መስጠት፡፡<br>• ስእሎችንና ሁነቶችን በመተንተን የተጓደሉ ሃሳቦችን ማሟላት፡፡<br>• በማህበራዊ ጉዳዮች ላይ ውይይት በማድረግ መሳተፍ፡፡<br>• ያልተሟሉ አረፍተ ነገሮችን የያዘ አንቀጽ ማሟላት፡፡<br>• የቃላትን መሰረት በመለየት ቃላትን መመስረት፡፡<br>• ቃላትን በቃል ክፍሎቻቸው መሰረት መመድብ፡፡ | • የተጓደሉ ሃሳቦችን ማሟላት<br>• ጅምር አንቀጾችን በጽሑፍ ያሟላሉ፡፡<br>• አንቀጽ ይጽፋሉ፡፡ | • አስተያየት መስጠት<br>• የቡድን ውይይት<br>• ስእሎችንና ሁነቶችን ማብራራት<br>• የአንቀጽ አጻጻፍ ናሙና አይቶ መዳፍ |

ግምገማ

- የማዳመጥ ጥያቄዎችን በትክክል መመለሳቸውን ማረጋገጥ
- በተሠጣቸው ርእስ ላይ በንቃት መወያየታቸውንና ተሳትፎ ማድረጋቸውን መከታተልና ግብረ መልስ መስጠት፡፡
- ስላነበቡት ነገር የተረዱትን በመጠየቅ መረዳታቸውን ማረጋገጥ
- የአንቀጽ ቀሪ ክፍሎችን ለይተው መረዳታቸውን አንቀጽ መመስረታቸውን ማረጋገጥ፡፡

አማርኛ እንደ ሁለተኛ ቋንቋ መርሐ ትምህርት ስምንተኛ ክፍል

መጀመሪያው ወሰነ ትምህርት የተሰጠው ክ/ጊዜ 9

ምእራፍ አምስት፡-የተሰደዱ ስሞች

የሚጠበቅ ውጤት፤ተማሪዎች ከዚህ ትምህርት በኋላ ፡- በተላላፊ በሽታዎች ጉዳይ ላይ አዳምጠው አስተያየት ይሰጣሉ፤የራሳቸውን የሕይወት ተሞክሮ ለአቻዎቻቸው ይናገራሉ፤በምንባቡ መሰረት አውዳዊ ፍች ይሰጣሉ፤የሕይወት ታሪካቸውን ይጽፋሉ፤ለአዳዲስ ቃላት ፍቺ ይጽፋሉ ፤ቁጥር፣ ጾታና ጊዜ አመልካች ቅጥያዎችን ይለያሉ፡፡

| የማድመጥና የመናገር ብቃት፣የሕይወት ክህሎት እንዲሁም የቃላትና የስዋሰው ችሎታ | የማንበብና የመጻፍ ብቃት እንዲሁም የስነ ጽሁፍ ችሎታ | የመማር ማስተማር ክንውኖችና ስልቶች |
|---|---|---|
| • በተላላፊ በሽታዎች ጉዳይ ላይ አዳምጠው አስተያየት መስጠት፡፡<br>• የራሳቸውን የሕይወት ተሞክሮ ለአቻዎቻቸው መናገር፡፡<br>• በምንባቡ መሰረት አውዳዊ ፍች መስጠት፡፡<br>• የሕይወት ታሪካቸውን መጻፍ፡፡<br>• ለአዳዲስ ቃላት ፍቺ መስጠት፡፡<br>• ቁጥር፣ ጾታና ጊዜ አመልካች ቅጥያዎችን መለየት፡፡ | • አውዳዊ ፍቹን መለየት<br>• በአንብቦ መረዳት ሂደት ጥያቄዎችን መመለስ<br>• የሕይወት ታሪክ መጻፍ | • የጽሑፍና የቃል መልስ<br>• የሕይወት ታሪክ ዝርዝር ልምምድ |

ግምገማ

- የማዳመጥ ጥያቄዎችን በትክክል መመለሳቸውን ማረጋገጥ
- በተሠጣቸው ርእስ ላይ በንቃት መወያየታቸውንና ተሳትፎ ማድረጋቸውን መከታተልና ግብረ መልስ መስጠት፡፡
- ስላነበቡት ነገር የተረዱትን በመጠየቅ መረዳታቸውን ማረጋገጥ
- የአንቀጽ ቀሪ ክፍሎችን ለይተው መረዳታቸውን አንቀጽ መመስረታቸውን ማረጋገጥ፡

አማርኛ እንደ ሁለተኛ ቋንቋ መርሐ ትምህርት ስምንተኛ ክፍል

ሁለተኛው ወሰነትምህርት                              የተመደበው ክ/ጊዜ 9

ምእራፍ ስድስት፡-ወዳጅ ሲከዳ

የሚጠበቁ ውጤቶች ፣ተማሪዎች ከዚህ ትምህርት በኃላ ፡-አርአያ የሆነ ሰው የህይወት ታሪክ አዳምጠው በቅደም ተከተል መልሰው ይተርካሉ፣ መፍትሄ በሚሹ ማህበራዊ ጉዳዮች ዙርያ ችግር ፈቺ የሆነ ንግግር ያደርጋሉ፣አጭር ልብወለድ አንብበው ጥያቄዎችን ይመልሳሉ፣ድርሰት ይፅፋሉ፣ስሞች ላይ ቅጥያ ምዕላዶችን በመጨመር ቅፅሎችን ይመሰርታሉ፡፡

| የማድመጥና የመናገር ብቃት፣የሕይወት ክህሎት እንዲሁም የቃላትና የስዋሰው ችሎታ | የማንበብና የመጻፍ ብቃት እንዲሁም የስነ ጽሁፍ ችሎታ | የመማር ማስተማር ክንውኖችና ስልቶች |
|---|---|---|
| • የቅድመ ማዳመጥ ጥያቄዎችን መመለስ<br>• የሚቀርብላቸውን ጽሁፍ በትኩረት በማዳመጥ ልዩ ልዩ ጥያቄዎችን መመለስ<br>• ሲነበብ አዳምጠው በቡድን ከተወያዩ በኂላ ንግግር ማድረግ<br>• በተሰጣቸው ርዕሰ ጉዳይ ላይ በቡድን ተወይይተው ንግግር ማድረግ<br>• የቀረበውን ምንባብ ሲነበብ አዳምጠው በቡድን ከተወያዩ በኂላ ንግግር ማድረግ | • በትርፍ ጊዜ በቤታቸው (በቤተመጻህፍት) ፣ አንድ አጭር ልቦለድ ማንበብ<br>• ድርሰት መጻፍ<br>• ስሞች ላይ ቅጥያ ምዕላዶችን በመጨመር ቅፅሎችን መመስረት | • ጥያቄዎችን እንዲመልሱ ማበረታታት<br>• ተማሪዎችን በቡድን በማስቀመጥ ማወያየት<br>• ለሚቀጥለው ክፍለ ጊዜ አንድ አጭር ልቦለድ አንብበው እንዲመጡ ማድረግ<br>• አጭር ድርሰት እንዲጽፉ ማበረታታት<br>• ማብራሪያ |

ግምገማ፡-

- አርአያ የሆነ ሰው የህይወት ታሪክ አዳምጠው መልሰው መተረክ መቻላቸውን ማረጋገጥ
- መፍትሄ በሚሹ ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ችግር ፈቺ ንግግር ማድረጋቸውን መገምገም
- አጭር ልብወለድ አንብበው በመገንዘብ ለሚቀርብላቸው ጥያቄዎች ምላሽ መስጠታቸውን ማረጋገጥ
- ስሞች ላይ ቅጥያ ምዕላዶችን በመጨመር ቅፅሎችን መመስረታቸውን መፈተሽ
- አወንታዊና አሉታዊ ዓ.ነገሮችን ለይተው በመገንዘብ ዓ.ነገር መመስረታቸውን መመርመር

አማርኛ እንደ ሁለተኛ ቋንቋ መርሐ ትምህርት 8ኛ ክፍል

## ሁለተኛው ወሰነ ትምህርት

ምእራፍ ሰባት፡- ኩተት 12 ክፍለ ጊዜያት

**የሚጠበቅ ውጤት**ተማሪዎች የዚህን ምዕራፍ ትምህርት ከተማሩ በኋላ፡ምንባቡን አንብበው ፍሬ ሀሳቡን ይናገራሉ፤በበጎ ተግባር ላይ ይነጋገራሉ፤የአካባቢያቸውን የስራ ባህል የተመለከተ አመዛዛኝ ድርሰት ይጽፋሉ፤አጭር ልቦለድ አንብበው ዋና ገፀባህሪያትን ይለያሉ፤የቃል ክፍሎችን ይለያሉ፤የአረፍተ ነገር ክፍሎችን ይለያሉ።

| የማድመጥና የመናገር ብቃት፣የሕይወት ክህሎት እንዲሁም የቃላትና የስዋሰው ችሎታ | የማንበብና የመጻፍ ብቃት እንዲሁም የስነ ጽሁፍ ችሎታ | የመማር ማስተማር ክንውኖችና ስልቲች |
|---|---|---|
| • የቅድም ማድመጥ ጥያቄዎችን መስራት<br>• ድር ቢያብር የሚለውን ምንባብ በጥሞና ማንበብ<br>• ስለ አካባቢያቸው ማህበራዊ ህይወት መወያየት<br>• ስለትምህርት ቤታቸው በጎ አድራጎት ክበብ መወያየት<br>• የውይይታቸውን ዋና ሀሳብ ለክፍል ጓደኞቻቸው በቃል ማቅረብ<br>• የቃል ክፍሎችን አጭር ማስታወሻ ማንበብ<br>• የቃል ክፍሎችን መለየት<br>• የአረፍተ ነገር ክፍሎችን መለየት | • የቅድመ ማንበብ ጥያቄዎችን መስራት<br>• ሱስና መዘዙ የሚለውን ምንባብ በለሆሳስ ማንበብ<br>• የድህረ ማንበብ ጥያቄዎችን መስራት<br>• አመዛዛኝ ድርሰት መጻፍ<br>• የአጭር ልቦለድ ምንነት መጥቀስ<br>• የአጭር ልቦለድ ባህሪያትን መለየት<br>• አጭር ልቦለድ ማንበብ<br>• ገፀባህሪያትን መለየት<br>• የታዩ ለውጦችን መመርመር | • የቅድመ ማንበብ ጥያቄዎችን ማሰራት<br>• ሱስና መዘዙ የሚልውን ምንባብ በለሆሳስ ማስነበብ<br>• የቅድመ ማድመጥ ጥያቄዎችን ማሠራት<br>• ድር ቢያብር የሚለውን ምንባብ በቃል ማስደመጥ<br>• ተማሪዎች እንዲሰሩ/ እንዲወያዩ ማድረግ<br>• ተማሪዎች ሲወያዩ/ሲወያዩ ምልከታና ድጋፍ ማድረግ<br>• እርማትና ግብረ መልስ መስጠት |

ግምገማ

- ተማሪዎቹ “ ሱስና መዘዙ ” የሚለውን ምንባብ በለሆሳስ አንብበው በምንባቡ ሊተላለፍ የተፈለገውን ዋና ሀሳብ መናገራቸውን ማረጋገጥ፤
- “ ድር ቢያብር ” የሚለውን ታሪክ አድምጠው ስለ ማህበራዊ ህይወት፣ ስለ መተባበርና ስለ ደቦ መወያየት መቻላቸውን መከታተል፤
- የራሳቸውን ማህበራዊ ሚና ማብራራታቸውን መከታተል፤
- ስለ ትምህርት ቤታቸው በጎ አድራጎት ክበብ መወያየታቸውን መከታተል፤
- ስለ አጭር ልቦለድ ምንነትና ባህሪያት መናገር መቻላቸውን ማረጋገጥ፤
- አጭር ልቦለድ አንብበው ዋና ዋና ገፀ ባህሪያትን መለየት መቻላቸውን ማረጋገጥ፤
- የአካባቢያቸውን የሥራ ባህል የተመለከተ አመዛዛኝ ድርሰት መጻፍ መቻላቸውን ማረጋገጥ፤
- በፃፉት አመዛዛኝ ድርሰት አፃፃፍ ላይ ሲወያዩ መከታተል፤
- የቃል ክፍሎችንና የአረፍተ ነገር ክፍሎችን መለየት መቻላቸውን ማረጋገጥ፤
- የሰዋስው ህግ የጠበቁ አረፍተ ነገሮችን መመስረት መቻላቸውን ማረጋገጥ ነው።

አማርኛ እንደ ሁለተኛ ቋንቋ መርሐ ትምህርት ስምንተኛ ክፍል

ሁለተኛው ወሰነ ትምህርት　　　　　　　　　　　የተሰጠው ክ/ጊዜ 6 ክ/ጊዜ

ምእራፍ ስምንት፡-ወራሾቹ

የሚጠበቀው ወጤት፤ተማሪዎች ይህን ትምህርት ከተማሩ በኂላ፡-የተራኪ ጽሑፍ አላባውያንን ለይተው ይገልጻሉ ፤በልዩነትና ብዝሀነት ላይ ጉዳይ ያዳመጡትን ጭብጥ ያንጸባርቃሉ፣በፍጥነት ሃሳብ አፍልቀው ይናገራሉ፤በፈጣን የንባብ ስልት ያነባሉ፣የጽሕፈት ሂደትን ተከትለው ይጽፋሉ፡፡

| የማድመጥና የመናገር ብቃት፣የሕይወት ክህሎት እንዲሁም የቃላትና የስዋሰው ችሎታ | የማንበብና የመጻፍ ብቃት እንዲሁም የስነ ጽሁፍ ችሎታ | የመማር ማስተማር ክንውኖችና ስልቲች |
|---|---|---|
| • የተራኪ ጽሑፍ አላባውያንን ለይተው መግለጽ<br>• በልዩነትና ብዝሀነት ላይ ጉዳይ ያዳመጡትን ጭብጥ ማንጸባረቅ፣<br>• በፍጥነት ሃሳብ አፍልቀው መናገር፤<br>• በፈጣን የንባብ ስልት ማንበብ፣<br>• የጽሕፈት ሂደትን ተከትለው መጻፍ፡፡ | • የተራኪ ጽሁፍ አላባውያንን መለየት<br>• በፈጣን የንባብ ስልት መረጃ ማግኘት<br>• የጽሕፈት ሂደት ተከትሎ መጻፍ | • የታሪክ ካርታ መጠቀም<br>• የንባብ ስልት ልምምድ<br>• የመምህር መር የጽህፈት ልምምድ |

ግምገማ

- ስለ ተራኪ ጽሑፍ አላባውያን መረዳታቸውን በሚሰጡት መልስ ማረጋገጥ
- የማዳመጥ ጥያቄዎችን በትክክል መመለሳቸውን ማረጋገጥ
- በተሠጣቸው ርእስ ላይ በንቃት መወያየታቸውንና ተሳትፎ ማድረጋቸውን መከታተልና ግብረ መልስ መስጠት፡፡
- ስላነበቡት ነገር የተረዱትን በመጠየቅ መረዳታቸውን ማረጋገጥ
- አጻጻፍ ስርዓትን ተከትለው መጻፋቸውንና ማረማቸውን መከታተል፡፡

አማርኛ እንደ ሁለተኛ ቋንቋ መርሐ ትምህርት ስምንተኛ ክፍል

ሁለተኛው ወሰነ ትምህርት                    የተመደበው ክ/ጊዜ 9 ክ/ጊዜ

ምእራፍ ዘጠኝ ፡- ዓባይ

የሚጠበቁ ውጤቶች ፡- ተማሪዎች የዚህን ምዕራፍ ትምህርት ከተማሩ በኂላ፡- ተራኪ ጽሑፍ አዳምጠው ጥያቄዎችን ይመልሳሉ፤ በተሳጣቸው ረእሰ ጉዳይላይ ንግግር ያደርጋሉ፤ አያያዦችን ተጠቅመው አረፍተ ነገር ይመሰርታሉ፤ ድምጻቸውን ከፍ አድርገው ግጥም በዜማ ያነባሉ፤ ግጥም አንብበው መልእክቱን ይናገራሉ፤ ግጥም አንብበው ወደ ዝርው ይቀይራሉ፡፡

| የማድመጥና የመናገር ብቃት፣የሕይወት ክህሎት እንዲሁም የቃላትና የስዋሰው ችሎታ | የማንበብና የመጻፍ ብቃት | የመማር ማስተማር ክንውኖችና ስልቶች |
|---|---|---|
| • ባዳመጡት ጽሁፍ መሰረት መልመጃዎችን መስራት<br>• የቅድመ ማዳመጥ ጥያቄዎችን መመለስ<br>• አያያዦችን በተገቢ ቦታቸው በማስገባት አረፍተ ነገሮችን ማሟላት<br>• አያያዦችን ተጠቅመውአረፍተ ነገሮችን መመስረት | በመማሪያ መጽሀፋቸው ላይ የቀረበውን ጽሁፍ አንብበው ፡-<br>• መልእክቱን ማሰላሰል<br>• ጥንድ በመሆን መወያየት<br>• የተስማሙበትን ሀሳብ ለመምህር መናገር<br>• የቀረበላቸውን ግጥም በዜማ ያነባሉ፡፡<br>• ያነበቡትን ግጥም ለሚመለከቱ ጥያቄዎች በጽሁፍ ምላሽ ይሰጣሉ፡፡<br>• የግጥሙን መልእክት በዝርው ይገለጻሉ፡፡<br>• የግጥሙን ስልተ ምት ተክትለው ያነባሉ፡፡<br>• ግጥም አንብበው መልእክቱን ይናገራሉ፡፡<br>• ባዳመጡት ጽሑፍ መሰረት ጥያቄዎችን መመለስ | በመማሪያ መጽሀፋቸው ላይ ያለውን ጽሁፍ አንብበው መልእክቱን፡- በግል እንዲያሰላስሉ ፣ጥንድ በመሆን እንዲወያዩና የተስማሙበትን ሀሳብ ነክፍል ውስጥ እንዲናገሩ ማድረግ |

ግምገማ፦

- ተራኪ ጽሁፍ አዳምጠውለሚቀርቡላቸው ጥያቄዎች ምላሽመስጠታቸውን ማረጋገጥ፤
- በተሰታቸው ርእሰ ጉዳይ ላይ ንግገር ማድረግ መቻላቸውን መገምገም፤
- አያያዞችን በመጠቀም አረፍተ ነገሮችን መመስረታቸውን ማረጋገጥ፤
- የግጥምን ስልተ ምት ተከትለው በዜማ ማንበብ መቻላቸውን መፈተሽ፤
- ግጥም አንብበው መልእክቱን መናገር መቻላቸውን መመርመር፤
- የግጥሙን መልእክት በዝርው ጽሁፍ ማቅረብ መቻላቸውን ማረጋገጥ፡፡

አማርኛ እንደ ሁለተኛ ቋንቋ መርሐ ትምህርት ስምንተኛ ክፍል

ሁለተኛው ወሰነ ትምህርት የተሰጠው ክ/ጊዜ 10 ክ/ጊዜ

ምእራፍ አስር ፡- ሀብታሙ ሰው

የሚጠበቅ ውጤት፤ ተማሪዎች ከዚህ ትምህርት በኋላ ፡-የጓደኞቻቸውን ሀሳብ ያዳምጣሉ፤ሚና በመውሰድ ጭውውት ያደርጋሉ፤በተለያዩ ሀሳቦች ላይ ይከራከራሉ፤የምሳሊያዊ አነጋገሮችን ሃሳብ ያስረዳሉ፤ተረቶችን በትረካዊ ዘዴ ያወራሉ፡፡

| የማድመጥና የመናገር ብቃት፣የሕይወት ክህሎት እንዲሁም የቃላትና የስዋሰው ችሎታ | የማንበብና የመጻፍ ብቃት እንዲሁም የስነ ጽሁፍ ችሎታ | የመማር ማስተማር ክንውኖችና ስልቶች |
|---|---|---|
| • የጓደኞቻቸውን ሀሳብ ማዳመጥ፡፡<br>• ሚና በመውሰድ መጫወት፡፡<br>• በተለያዩ ሀሳቦች ላይ መከራከር፡፡<br>• የምሳሊያዊ አነጋገሮችን ሃሳብ ማስረዳት፡፡<br>• ተረቶችን በትረካዊ ዘዴ ማውራት፡፡ | • የምሳሌያዊ አነጋገርችን መጠቀም<br>• ተረትን በትረካዊ ስልት ማንበብ<br>• የተረትን አላባውያን መለየት | • በቡድን ውይይት<br>• በትረካዊ ስልት |

ግምገማ

- ሰለ ተራኪ ጽሑፍ አላባውያን መረዳታቸውን በሚሰጡት መልስ ማረጋገጥ
- የማዳመጥ ጥያቄዎችን በትክክል መመለሳቸውን ማረጋገጥ
- በተሠጣቸው ርእስ ላይ በንቃት መወያየታቸውንና ተሳትፎ ማድረጋቸውን መከታተልና ግብረ መልስ መስጠት፡፡
- ስላነበቡት ነገር የተረዱትን በመጠየቅ መረዳታቸውን ማረጋገጥ
- አጻጻፍ ስርዓትን ተከትለው መጻፋቸውንና ማረማቸውን መከታተል፡፡